*የሚያዘው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለምዕመናን የግል ሕይወታቸውም ጠቃሚ በመሆኑ ነው። ብዙዎች ለእግዚአብሔር ተጠያቂዎች መሆናቸውን ያለምንም ጥያቄ እምነው ይቀበላሉ። "አባታችን ነው፤ ፍጹም አምላክ ነው፤ በሕይወታችን የፈቀደውን ለማድረግ ሙሉ መብት አለው፤ ያለአንዳች አድልዎ መፍረድ ይችላል" ይላሉ። ለምድራዊ ሰው ግን ራሳቸውን ተጠያቂ ለማድረግ ፈቃደኞች አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች፣ "ለእግዚአ ብሔር እንጂ ለማንም አልገዛም" ሲሉ ይሰማሉ። እንዲህ የሚሉት ቀደም ሲል በሕይወታቸው "መንፈሳዊ መሪ ነን" በሚሉ ሰዎች የተጎዱ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ለመንፈሳዊ መሪዎች ራሳችንን ተጠያቂዎች ማድረግ እንዳለብን ቃሉ ያስተምረናል።*

## ምዕራፍ ፫

# ጥሪን መጠበቅና የማሳደግ ኃላፊነት

*"...ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር..."*(ሮሜ 12፥8)

ቤተ ክርስቲያን ስለምትከተለው የአመራር ሥልትና እንዲሁም መሪዎቿ ከእግዚአ ብሔር የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚፈጽሙ በቂ የሆነ መረዳት ለማግኘት፣ በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚፈጠሩትን አንዳንድ ችግሮች በቅድሚያ ማወቅ ይጠቅማል። በምዕራቡ ዓለም፣ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ ለማወቅ ብዙ ጥናቶችና ምርምሮች ተደርገዋል። ምርምሩን ካደረጉት ምሁራን መካከል አንደኛው *"ቶድ ሃንተር"* የተባሉ የአንድ ቤተ እምነት መሪ ሲሆኑ፣ በጥናታቸው ካገኙት ውጤት ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ በታች ጠቅሰናል፦

- በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጣቸው ራዕይ ምን እንደሆነ በትክክል መግለጽ የሚችሉት ከመቶ መጋቢዎቹ ውስጥ እሥሩ ብቻ ናቸው።

- በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነው ከሚያገለግሉት ውስጥ፣ "የመሪነት ስጦታ አለኝ" የሚሉት፥ ከመቶ አምስቱ (5%) መጋቢዎች ብቻ

ናቸው። አብዛኛዎቹ የመጋቢነት ጥሪ የሌላቸው፥ እንዲሁም የሥነ መለኮት ትምህርት ተምረው ራሳቸውን ለአገልግሎት ያላዘጋጁ ናቸው።

- ከመቶ መጋቢዎች ውስጥ ዘጠና አምስቱ (95%)፥ ከሚያገለግሉት ሕዝብ መካከል የመሪነት ስጦታ ያላቸውን አማኞች መለየት፣ አብልጥኖ ለአገልግሎት ማብቃት (ማሰለፍ)፣ ኃላፊነት የማከፋፈል ችሎታ ያላቸው አይደሉም።
- ከመቶ ሰባ አምስቱ (75%) መጋቢዎች ዕቅድና ግብ የማውጣት ችሎታ የሌላቸው በመሆኑ፣ ግልጽ የሆነ መመሪያ የሌላቸው፣ ያለአግባብ ራሳቸውን በጣም የሚያደክሙ ናቸው።[12]
- በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚያገለግሉ መጋቢዎች (የቤተ ክርስቲያን መሪዎች) አቋምስ ምን ይመስል ይሆን? የኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን አቋም ለመገምገም የተደረገ ጥናትም ሆነ ምርምር ባይኖርም፣ ጎልቶ የሚታዩትን ችግሮች (ድካሞች) ለመጠቆም ይህን ያህል አስቸጋሪ አይደለም።
- በአሁኑ ጊዜ የአንድ ኮርፖሬሽን (ዓለማዊ ድርጅት) መሪ ከመሆን ይልቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የበለጠ አስፈሪ እየሆነ በመምጣቱ፣ የመሪነት ችሎታ እያላቸው ከኃላፊነት የሚሸሹ ክርስቲያኖች ቁጥር እየበዛ መጥቷል።
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቡድን መከፋፈል፣ በምዕመናን መካከል ወገን ለይቶ መጋጨት፣ እንዲሁም ፍርድ ቤት መካሰስ በአሁኑ ጊዜ የተለመደ ሆኗል።
- ስጦታም ሆነ ችሎታ ሳይኖራቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚሆኑት ክርስቲያኖች ቁጥር ጨምሯል።
- "ቤተ ክርስቲያን የምሄደው፥ መንፈሳዊ ትምህርት አገኛለሁ ብዬ ሳይሆን ቀባሪ እንዳላጣ ብዬ ነው" የሚሉት ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል።

ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ የተጠራችበትን ኃላፊነት እንደሚገባው ለመፈጸም አቅም ያነሳት መሆኗን ስንመለከት፣ አንዳንድ ጥያቄዎች በአዕምሯችን ውስጥ መመላለሳቸው አይቀርም።

[12] Todd Hunter, "Successful Pastors: Are The Really Different" Equipping the Saints (Spring 1988).



*ቤተ ክርስቲያን የአመራር ችግር የሚያጋጥማት መሪዎቿ መንፈሳዊነት የጎደላቸው በመሆናቸው ይሆን?*

*በምዕመናኑና በመሪዎች መካከል ግጭት የሚበዛው ቤተ ክርስቲያን መፈሳዊነት የሌለውን የዓለምን የአመራር ንድፈ-ሀሳብ (Leadership Theory) በመከተሏ ይሆን?*

*ቤተ ክርስቲያን በቡድን የምትከፋፈለው አማኞች መንፈሳዊነት የጎደላችው ወይም አስቸጋሪ ባሕሪ ያላቸው በመሆኑ ይሆን?*

መጠኑና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ሁላችንም አንዳንድ የመሪነትን ኃላፊነት ቀምሰን ስላለፍን፣ በመሪነት ቦታ ላይ መቀመጥ ምን ያህል ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ እናውቃለን። በመሪነት ሥፍራ ላይ የሚቀመጡ ሰዎች፣ በሚሰጡት አገልግሎት፣ በሚወስኗቸው ውሳኔዎች፣ በበጎ ወይም በክፉ የሌሎችን ሕይወት የመንካት ዝንባሌ አላቸው። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ የግል ሕይወቱን ምንም ያህል በጥበብና በማስተዋል የሚመራ፣ አገልግሎቱን በቅንነትና በታማኝነት የሚፈጽም ሰው ቢሆን፣ በትዕግሥት የተሞላ፣ ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም የሚያስኖር መልካም ጠባይ ያለው ሰው ቢሆን፣ እንዲሁም ለሚያደርገው ነገር ሁሉ በጌታ ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለበት አውቆ በጥንቃቄ አገልግሎቱን የሚፈጽም ቅን አገልጋይ ቢሆን እንኳን፣ የራሱ የሆኑ እንቅፋቶችና ችግሮች ያጋጥሙታል።

እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ዘመናት፣ በሰዎች መካከል ክብሩን ለመግለጽ፣ ዓላማውን ለመፈጸም ሲፈልግ፣ በቅድሚያ ከእርሱ ጋር የሚተባበሩትን፣ ራሳቸውን ለእርሱ ፈቃድ ያስገዙትን፣ እንዲሁም የተሰጣቸውን የአገልግሎት ጥሪ ተቀብለው ሌሎችን ለመምራት ፈቃደኞች የሆኑትን፣ እንደ ልቡ የሚሆኑለትን ሰዎች ፈልጎ ያስነሳ ነበር። ለመሪነት የሚጠራቸው ሁሉ ፍጹምነት የሌላቸው፣ የራሳቸው የሆነ ድካም ያለባቸው ቢሆኑም፣ ከድካማቸው ዓላማውን እንዲያስፈጽሙ ልዩ ማስተዋልና አቅም (ጉልበት) ሰጥቶ ይጠቀምባቸው እንደ ነበረ ከታሪካቸው ማኅደር መገንዘብ እንችላለን። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ ለማውጣት ሲያስብ፣ ሕዝቡን ሊመራ የሚችል ትሁት የሆነ ልብ፣ ብርቱ መንፈስ የነበረውን ሙሴን አስቀድሞ መጥራትና ለመሪነት ማዘጋጀት ነበረበት። ሙሴ ብርቱ ጎን ብቻ ሳይሆን፣ ደካማ ጎንም የነበረው ሰው መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አልሸሸገም። ሙሴ ትሁት ልብ፣ ቀና መንፈስ የነበረው ሰው መሆኑን ያወቀው ጌታ ግን ከነድካሙ ለክብሩ ተጠቀመበት። የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ የሚያስፈጽሙ መሪዎች ጥንት ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዘመንም ያስፈልጋሉ። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛ ጥሪና እንዲሁም ብቃት ባላቸው መሪዎች እንድትመራ የእግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ ነው። ቤተ ክርስቲያን የምታስተላልፈውን የደህንነት መልዕክት ዓለም እንድትሰማ፣ መንፈሳዊ የሆኑ፣ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው የሰጡ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚከተሉ፣ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በሙሉ ልብ መፈጸም

የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጓታል። *"መንፈሳዊ የሆኑ"* ስንል፣ *ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ያላቸው ማለታችን ነው።* ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች፣ ምንም ያህል የማስተዳደርም ሆነ የመምራት ዕውቀትና ችሎታ ቢኖራቸው እንኳን፣ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ መምራት እንደማይችሉ ግልጽ ነው። ባለፉት ዘመናት ብቻ ሳይሆን፣ እኛ ባለንበት በአሁኑ ዘመንም መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ብቃትና ፍላጎት ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎች በብዛት አይገኙም። "ምክንያቱ ምን ይሆን?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ ምክንያቶችን ለማሳየት ሞክረናል።

ኢየሱስ በምድራዊ የአገልግሎት ዘመኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደሆነች ሲገልጽ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት አማኝ ሁሉ ራሱን ዝቅ አድርጎ ሌላውን በትህትና የሚያገለግልበት ኅብረት (ማህበረሰብ) እንደሆነ ያስተምር ነበር። *"አገልጋይ"* ወይም *"ባሪያ"* የሚለው ቃል፣ በየትኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ የዝቅተኛነት እንጂ፣ የትልቅነት ደረጃ ወይም የማዕረግ ስፍራ ስላልሆነ፣ እውነተኛውን የአገልግሎት ጥሪ ከእግዚአብሔር ያልተቀበለ ሰው፣ ይህን የአሽከርን (የባሪያን) ሥፍራ ይዞ ለማገልገል የሚፈልግ ሰው አይኖርም። ኢየሱስ ግን አገልጋይ (ባሪያ) የሚለውን ቃል የተጠቀመበት የትልቅነት እንጂ፣ የዝቅተኛነት ደረጃ እንደሆነ አድርጎ አይደለም። ጳውሎስም የኢየሱስን ሀሳብ በመያዝ በዚህ ሕብረት ውስጥ ያሉትን የገላትያ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን *"...አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል"* (ገላት 5፥13) በማለት ይመክራቸዋል። በዚህ ዘመን ያለነው አማኞችም የምንሰጠው የፍቅር አገልግሎት አድጎና ተስፋፍቶ ዓለምን በሙሉ መድረስ የሚችለው ራሳችንን ዝቅ አድርገን ማገልገል ስንችል ነው። የሚያሳዝነው ግን በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአገልግሎትን ጥሪን የተቀበሉት፣ ወይም አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ የሚታዩት በጣም ጥቂት አማኞች መሆናቸው ነው። አገልግሎታችንን በምን ዓይነት መንፈስ ሆነን መፈጸም እንዳለብን ኢየሱስ ሲገልጽ፣ ***"...ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፤ የሁሉ ባሪያ ይሁን"*** ይላል (ማር. 10፥43-44)። እንደ ኢየሱስ አባባል፣ *"ታላቅ' መሆን አገልጋይነት፣ ፊተኛ መሆን የሌሎች ባሪያ መሆን"* ከሆነ፣ እውነተኛ የሆነ የሕይወት ለውጥ የሌላቸው ሰዎች ይህን እውነት ተቀብለው ሲኖሩበት አይችሉም። ራስን በተመቻቸ ሁኔታ ላይ ማስቀመጥ ሥጋ የለበሰ ሰው ሁሉ ፍላጎት ስለሆነ፣ እውነተኛ ጥሪ የሌለው መሪ (አለቃ)፣ "አገልጋይ" ወይም "አሽከር" ለመሆን ፈቃደኛ ሆኖ ለአገልግሎት ለመሰለፍ ፈቃደኛ አይሆንም። እግዚአብሔር ለመሪነት የሚመርጣቸው ሰዎች፣ እውነተኛ የሆነ የሕይወት ለውጥ ያላቸው ከሆኑ፣ ኃላፊነቱን የሚቀበሉት "አለቃ" ለመሆን ሳይሆን፣ ባሪያ (አገልጋይ) ለመሆን ነው።

ቤተ ክርስቲያን ብርቱ በሆኑ፣ በሕይወታቸው የክርስቶስ ውበት በሚታይባቸው መንፈሳዊ መሪዎች የምትመራ ከሆነ፣ በብዙ አቅጣጫ ዕድገት ታሳያለች። ብቃት የሌላ



ቸው መሪዎች የሚመሯት ከሆነ ግን፣ ብዙ ግጭትና መከፋፈል ይደርስባታል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር *"ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው"* ይላል (ዘፍ. 1፥27)። ጾታቸው ይለያይ እንጂ፣ አንዱ ከሌላው እንዲበልጥ ወይም እንዲያንስ አድርጎ አልፈጠራቸውም። በሁለቱ ጾታዎች መካከል የነበረው አቋም ሁኔታውን የለወጠው፣ ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ነው። ሔዋን ያልተፈቀደላትን በመንካቷ እግዚአብሔር ***"...ፍላጎትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤ እርሱም የበላይሽ ይሆናል"*** (ዘፍ. 3፥16) አላት። ይሁን እንጂ፣ የክርስቶስ ወንጌል ***"በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ"*** (ገላት. 3፥28) በማለት እኩልነቷን ያውጃል። "አንድ ናችሁ" ሲል፣ "ሁላችሁም በተግባር፣ በሙያ ተመሳሳይነት አላችሁ" ማለቱ አይደለም። ጳውሎስ ይህንን አሳብ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ ***"ነገር ግን ይህን እንድታውቁ እወዳለሁ፤ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፤ የሴትም ራስ ወንድ ነው፤ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር ነው"*** (1 ቆሮ. 11፥3) ይላል። ጳውሎስ ይህን ሲል "ወልድ ከአብ ያነሰ ነው" ማለቱ እንዳልሆነ እርግጠኞች ነን። ይህን ያለው ሰውን በመቤዠት ተግባር ላይ አብና ወልድ ያላቸውን የተለያየ አገልግሎት ለመግለጽ እንደሆነ እርግጠኞች ነን። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ አማኞች አገልግሎታቸው የተለያየ ይሁን እንጂ በምንም ዓይነት አንዱ ከሌላው ይበልጣል ማለት አይደለም። በዚህ ዓይነት በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ በመሪነት ሥፍራ፣ በማስተዳደር ኃላፊነት ውስጥ ያሉ ሰዎች አገልግሎታቸው ከሌሎች ምዕመናን የተለየ ይሁን እንጂ በማዕረግ ከሌሎች ይበልጣሉ ማለት አይደለም።

## 1. መንፈሳዊ መሪ ከኃላፊነቱ ውስጥ አንደኛው ክፍል ማስተዳደር ነው

መንፈሳዊ መሪ የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ማስተዳደር በርከት ያለውን ጊዜውንና ጉልበቱን የሚጠይቀው እንደሆነ ማወቅ አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ማስተዳደር" የሚለው አሳብ *"መንፈሳዊነት"* ያለው አገልግሎት መስሎ የማይታያቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች አይጠፉም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተዘረዘሩት ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንደኛው *"የማስተዳደር"* ስጦታ ነው። መንፈሳዊነት ባይኖረው ኖሮ መንፈስ ቅዱስ *"የማስተዳደር"* ስጦታን ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት ለአንዳንድ አማኞች ባልሰጠም ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ሲያደፋፍር፣ ***"...ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር..."*** (ሮሜ 12፥8) ይላል። ማንኛችውንም ዓይነት ስጦታዎች መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች ያከፋፍላል እንጂ አማኝ "ይሄ ለእኔ ይገባኛል" ብሎ መርጦ የሚወስደው ስጦታ አይደለም። ስጦታው "ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽበት" እንጂ ስጦታው የተሰጠው አገልጋይ እንዲታወቅበት ወይም እንዲከበርበት አይደለም። የማስተዳደር ስጦታን የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ይሁን እንጂ የማስተዳደር ስጦታ

ያላቸው አማኞች ሁሉ የሚጠቀሙበት የአስተዳደሩ ሥልት የሁሉም አንድ ዓይነት ይሆናል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥

- ◆ አንዱ ሌሎችን ማነቃቃት ሲችል፣ ሌላው ደግሞ አማኞችን ማደራጀት የሚችል ይሆናል።
- ◆ አንዱ በሰዎች ዙሪያ መሥራት ያለ የሚለው ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ብቻውን ሆኖ መሥራትን ይመርጣል።
- ◆ አንዱ ብዙ የሚናገር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ብዙ የማይናገር ይሆናል።

ይህን ዓይነቱን ልዩነት መረዳት የሚያስፈልገን፣ የእያንዳንዱ የአስተዳደር ስልት (ዓይነት) በመለያየቱ ብቻ *"ይሄኛው ጥሩ አስተዳዳሪ ነው፤ ያኛው ግን ጥሩ አስተዳዳሪ አይደለም"* በማለት ማበላለጥ (ማወዳደር) የማይገባ መሆኑን ለመግለጽ ነው። ለመሆኑ አስተዳደር ምንና ምንን ያጠቃልላል?

- ◆ አስተዳደር መመሪያ መስጠትን፣
- ◆ ሰዎችን ማስተዳደርን፣ ማነቃቃትን፣
- ◆ መመሪያና ግብ ማውጣትን፣
- ◆ ኃላፊነትን ለሌሎች ማከፋፈልን፣
- ◆ የራስንም ሆነ ሌሎች የሚሠሩትን ሥራ መከታተልና መገምገምን ያካትታል።

"ማስተዳደር" ሰንል ተግባርን እንጂ "ሥልጣንን" አያሳይም። መንፈሳዊ መሪ የማስተዳደር ችሎታው ብዙ የሚቀረው ቢሆንም እግዚአብሔር ልክ እንዳለ ሲጠቀምበት እንደሚችል መረዳት አለበት።

"መሪነት" (*Leadership*) ምንድነው? "መሪ" የሚለውን ቃል ስንሰማ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው አሳብ ምን ይሆን? የአገር መሪ፣ የኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የመንግሥት ባለ ሥልጣን የሆነ ሰው ነው። የአመራር ችሎታቸውና ፍልስፍናቸው የተለያየ ይሁን እንጂ ሂትለር፣ ጂም ጆንስ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ዊንስተን ቸርችል፣ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ማህተመ ጋንዲ በዘመናቸው ታዋቂ መሪዎች ነበሩ። ዓለማውያን "መሪነት" ምን እንደሆነ የራሳቸው የሆነ መረዳት፣ እንዲሁም የመሪነት "ንድፈ-ሀሳብ" (ቲዮሪ) አላቸው። ከመንፈሳዊ መሪነት በብዙ አቅጣጫ ይለያል። "መሪነትን" የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መልክ ይገልጹታል። ለምሳሌ አሥር ምሁራንን "መሪነት ምንድነው?" ብለን ብንጠይቃቸው፣ አሥሩም የተለያየ መልስ እንደሚሰጡን እርግጠኞች ነን። "ዋረን ቤኒስና በርት ናኦስ" (*Warren Bennis & Burt Naus*) የተባሉ ሁለት ጸሐፊዎች፣ "ሊደርስ–ስትራቲጂስ ፎር ቴኪንግ ቻርጅ" (*Leaders: Strategies*



*for Taking Charge*) በሚለው መጽሐፋቸው "መሪነት" ለሚለው ቃል 850 ዓይነት ገለጻ እንዳገኙ ገልጸዋል። "መሪነትን"፥

- ◆ አንዱ "ሕዝቡን የመቀስቀስ ሂደት ነው" ሲለው፥
- ◆ ሌላው ደግሞ "ሕዝቡንና ድርጅቱን ወደሚፈለግበት ግብ ወይም ደረጃ እንዲደርስ ማድረግ ነው" ይለዋል።
- ◆ "መሪነት" መመሪያ መስጠት፣ የሚመሩትን ሕዝብ ማነቃቃትን፣ ግብ ማበጀትን፣ ብቃት ላላቸው ሰዎች ኃላፊነት መስጠትን፣ ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሰዎች የሥራ ክንውን መመዘንን ያካትታል።[13]
- ◆ አንዱ "...መንገድ መምራት፣ ቀድሞ ሠርቶ በማሳየት መምራት...ማመልከት ማለት ነው" ይለዋል።
- ◆ ሌላው ደግሞ "...በምሳሌነት፣ በተፈጥሮ ችሎታው ወሳኝ የሆነ ሚና የሚጫወት ማለት ነው" ይለዋል።

መንፈሳዊ የሆነ "የመሪነት ንድፈ-ሀሳብ (ቲዮሪ) ከዓለማዊው ይለያል። መንፈሳዊ መሪውን ከዓለማዊው መሪ የተለየ የሚያደርገው ዋና ምክንያት፣ መሪው መንፈሳዊነት ያለው መሆኑ ነው። መንፈሳዊነት የሌለው መሪ የአመራር ብቃት ቢኖረው እንኳን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክል መምራት አይችልም። መንፈሳዊ መሪ ከዓለማዊው መሪ የተለየ የሚያደርገው፣

(1) መንፈሳዊ መሪ፣ መንፈሳዊ ሰዎችን የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታቸው እንዲፈጽሙ፣ እንዲሁም በሚኖሩት የክርስትና ሕይወት ዓለምን መንካት እንዲችሉ ያዘጋጃል።

(2) መንፈሳዊ መሪ በራሱ ጥበብና ችሎታ ከመደገፍ ይልቅ፣ በአመራሩ እንዲያግዘው በመንፈስ ቅዱስ ይደገፋል። በሚመራቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ የሚያመጣው መሪው ሳይሆን፣ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያውቃል።

(3) መንፈሳዊ መሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለበት ያውቃል። ስለሆነም በጥንቃቄና በፈሪሃ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

(4) መንፈሳዊ መሪ የሚሰበው (የሚነካው) አማኝ የሆነውን ሰው ብቻ ሳይሆን፣ የማያምነውንም ጭምር ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ዮሴፍና ዳንኤል ናቸው።

[13] Morris, H. Charles. The Christian Leader: Leadership Role, Publishers Association of the Philippines, 1980.

*(5) መንፈሳዊ መሪ ያለው አጀንዳ የእግዚአብሔር ነው። መንፈሳዊ መሪ ችግር የሚያጋጥመው፣ የእግዚአብሔርን አጀንዳ ትቶ የራሱን አጀንዳ ሲከተል ነው።*

*(6) መንፈሳዊ መሪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ዓላማ (አጀንዳ) ያደርሳል።*

ቢወደውም ቢጠላውም፣ መንፈሳዊ መሪ የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት። በየትኛውም የአመራር ተቋምና የሥራ መስክ ውስጥ መሪዎችና ተመሪዎች አሉ። ትክክለኛ ያልሆነ የአመራር ስልት በመከተልና፣ እንዲሁም ችሎታ ያለው እውነተኛ መሪ በማጣት ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በዓለማዊ ድርጅት ውስጥ ሰፊው (ተመሪው) ሕዝብ ካለበት አሰቸጋሪ ሁኔታ ወጥቶ የሚገባውን ያህል ወደ ፊት መሄድ እቅቶት ሲበሳጭና ተስፋ ሲቆርጥ ማየት የተለመደ ነው። መሪዎችም ራዕያቸውንና አመራራቸውን ተቀብለው መሄድ የሚፈልጉ ተመሪዎች በማጣታቸው የራሳቸው የሆነ ብስጭትና ተስፋ መቁረጥ አሳቸው። *ሄኒሪና ሪቻርድ* በሕብረት ሆነው በጻፉት መጽሐፋቸው፥

> *"ዓለም ጥሩ መሪዎችን ለማግኘት ይጓጓል። ፍሬያማ የሆነ መሪ ሕብረተሰቡ የሚያጋጥመውን ፈታኝ የሆኑ ችግሮችን የሚፈታ ሆኖ የሚታይበት ጊዜ አለ። በፖለቲካ፣ በሃይማኖት፣ በንግድ ዓለም፣ እንዲሁም በትምህርት መስክ፣ አለቸጋሪ የሆኑባቸውን ሁኔታዎች መቋቋም የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ችግሩ የመሪዎች እጥረት ብቻ ሳይሆን፣ ሰፊው ሕዝብ (ተመሪው)፣ መሪ በተባሉት ሰዎች ላይ እምነት ያጣ በመሆኑ ጭምር ነው" ይላሉ።*[14]

*"አስተዳደር"* የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው ሦስት ጊዜ ብቻ ሲሆን፥ አንደኛው፥ በ1 ቆሮ. 12፥28 ላይ *"...የማስተዳደር ስጦታ ያላቸው..."* የሚሰው ነው። በግሪክ ቋንቋ በተጻፈው ብሉይ ኪዳን (ሰፕቱጀንት ግን፣ ብዙ ሥፍራ እንደተጠቀሰ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይጠቁማሉ። *"አስተዳደር"* የሚለው የግሪኩ ቃል "ኩበርነሰስ" (Kuberneseis)[15] ሲለው፣ ቀጥተኛ ትርጉሙ፣ በመርከብ ላይ ያለውን እንቅስቃሴ መምራት ማለት ሲሆን፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ ቃል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ሲዘረዝር "ማስተዳደር" የሚለውን ቃል ለመግለጽ ተጠቅሞመበት እናያለን። አዲስ ኪዳን "መሪ" የሚለውን እሳብ የሚያየው፣ በጎ የሆነውን ነገር ለሌሎች የሚያደርገውን ሰው ነው። በጎ የሚያደርገውም ራሱን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን በማገልገል ነው። ሲያስተዳደርም (ሲመራ) "ባርያነቱን" ወይም "አገልጋይነቱን" እንጂ "ጌታነቱን" እያንጸባርቅም። ጳውሎስ ይህን እሳብ በመያዝ ስለ ራሱ ሲናገር፣ *"...ብዙዎችን እመስል ዘንድ ራሴን ለሰው ሁሉ ባሪያ አደርጋለሁ"* ይላል (1 ቆሮ. 9፥19)። ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበትን አገልግሎቷን እንደሚገባው ለመፈጸም እንድትችል፣ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሌሎችን መምራት ወይም ማስተዳደር የሚችሉ መንፈሳዊ መሪዎች ያስፈልጓታል። መንፈሳዊ መሪን፣ "ፍሬያማ መሪ" ከሚያሰኙት ነገሮች መካከል አንደኛው፣ *የአስተዳደር ችሎታው* እንደ ሆነ ግልጽ ነው። ብዙ ጊዜ *"አስተዳደር"* የሚለው ቃል ብዙዎቹን ያስፈራል። መሪው በሚወስነው ውሳኔ፣ በሚወስዳቸው አንዳንድ እርምጃዎች፣ ከሚመራቸው ሰዎች መካከል አንዳንዶቹን ቅር ሊያሰኝ ስለሚችል፣ "ከሰው ጋር ያጋጩን ይሆናል" በማለት የመሪነት ስጦታ ቢኖራቸውም እንኳን "መሪ" ለመሆን አይደፍሩም። ይሁን እንጂ፥ አማኞች ሁሉ አገልግሎታቸውን እንደሚገባ መፈጸም እንዲችሉ፣ የግድ አንድ ሰው ኃላፊነቱን ወስዶ የመሪነቱን ወይም የማስተዳደሩን ሥራ መሥራት አለበት። ቤተ ክርስቲያን ፍሬያማ እንዳትሆን ከሚያደርጓት ምክንያቶች መካከል መንፈሳዊ መሪ ማጣት ብቻ ሳይሆን፣ የመምራት (የማስተዳደር) ስጦታው ሳይኖራቸው፣ የራሳቸውን ጥቅም በመፈለግ ብቻ የማስተዳደርን ኃላፊነት በመውሰዳቸው ጭምር ነው። ጥሪውም ሆነ ብቃቱ ሳይኖራቸው በመሪነት ሥፍራ ላይ የተቀመጡ ሰዎች፣ ያለቦታቸው መሆናቸው ለእነርሱ ምናልባት ግልጽ ሆኖ ባይታያቸው፥ በሌሎች ዘንድ ግን በቀላሉ ተለይተው ይታወቃሉ።

እንዳንድ ሰዎች ብቃት ሳይኖራቸው በመሪነት ሥፍራ መቀመጣቸው በሌሎች ዓይን ብቻ የሚታይ ሳይሆን፣ እውነተኞች ከሆኑ፣ ራሳቸውም ብቃት እንደሌላቸው ሊገነዘቡት ይችላሉ። ያለችሎታቸው በመሪነት ሥፍራ የተቀመጡ እንዳንድ ሰዎች፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ሲያቅታቸው፣ በተለያየ ምክንያትና ከተለያየ አቅጣጫ ግጭት ሲበዛባቸው፣ *"መሪ መሆን አይገባኝም፤ ወይም የተቀመጥኩት ያለቦታዬ ነው"* በማለት ፈንታ፣ ድክማቸውን ለመሸፈን ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። *"ሥራ በዛብኝ፥ ኃላፊነቱ ከሚከፈለኝ ደሞዝ ጋር ተመጣጣኝ አይደለም"* በማለት የተለያየ ምክንያት በመሳጠት ሲያማርሩና ሲበሳጩ ይሰማሉ። ሥራውና ኃላፊነቱ ከችሎታቸው በላይ ከመሆኑ የተነሳ በወቅቱ መሠራት ያለበትን ነገር ወደ ጎን በመግፋት ችላ ብለውት ያልፉታል። በዚህ ዓይነት ያልተሠሩ ሥራዎች እየበዙ ሲመጡ፣ ሁኔታውን ተገንዝበው መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ፣ "ባለኝ የሥራ ብዛት ምክንያት ሥራውን ሁሉ ሠርቼ ለመጨረስ ጊዜው አይበቃኝም" በማለት የማያጠግብ ምክንያት ሲሰጡ ይሰማሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ኃላፊነታቸውን መወጣት የማይችሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለመሪነት የሚያበቃ ችሎታ እንደሌላቸው ሰዎች ሁሉ ያወቁባቸው ስለሚመስላቸው፣ ራሳቸውን ለመከላከል በሚያደርጉት ጥረት ቀረብ ካሏቸው ሰዎች ሁሉ ጋር በቀላሉ ይጋጫሉ። በዚህ ምክንያት በአካባቢያቸው ለሚገኙት ሰዎች ሁሉ አስቸጋሪ ሰዎች ይሆናሉ። በቀላሉ የሚጨነቁ፣ በሥጋትና በፍርሃት የተሞሉ፣ ደስ እያላቸው በማገልገል ፈንታ እያጉረመረሙ የሚያገለግሉ ይሆናሉ።

[14] Blackaby, Henry & Richard. Spiritual Leadership, Broadman & Holman Publishers, Nashville, TN, 1960.
[18] Gangel, O. Kenneth. Lessons in Leadership From The Bible, BMH Books, Winona Lake, Indiana, 1980.

ቤተ ክርስቲያን ጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ከሌሏት፥ የተጠራችበትን ዓላማ ለመፈጸም፥ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት፥ በዓለም ውስጥ ያሉትን ነፍሳት በወንጌል ለመድረስ፥ እንዲሁም ክብር ለሚገባው እግዚአብሔር ክብር መስጠት አትችልም። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ውስጥ የአመራር ችግር እንዳለ የሚያመለክቱ አንዳንድ መልካም ያልሆኑ ሁኔታዎች መታየት ይጀምራሉ። ይኸውም፥

*(1) ትክክለኛ የሆነ ዕድገት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጎልቶ አይታይም።*

*(2) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ መለያየትና መከፋፈል፥ ጠብና ግጭት በተደጋጋሚ ይታያል።*

*(3) የአገልጋዮች መለዋወጥ ብዙ ይታያል። ዛሬ ያለው አገልጋይ ነገ አይኖርም።*

*(4) በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በአመራራቸው ደስ ባለመሰኘት ብዙዎች ቤተ ክርስቲያኑን ጥለው ይሄዳሉ። የቀሩትም በአገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን ፈቃደኞች አይሆኑም።*

*(5) በሚሰጡት አገልግሎት ፍሬ አይታይም።*

## 2. የአስተዳደር ችሎታ ያለው መንፈሳዊ መሪ ማጣት ቤተ ክርስቲያንን ይጎዳል

የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ በሚያምጽበት ወቅት አልፎ አልፎ ይቀጣቸው የነበረው፥ መሪ በማሳጣትና እንዲሁም ብቃት በሌላቸው መሪዎች እንዲመሩ በማድረግ ነበር። ይሄም በኢሳያስ ትንቢት ውስጥ ተገልጿል። *"ልጆችን መሪዎቻቸው አደርጋለሁ፤ ያልበሰሉ ሕጻናትም ይገዟቸዋል"* ይላል (ኢ.ሳ. 3፥4)። የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉዳት ላይ የሚወድቀው፣ የሚመራው ሰው በማጣት ብቻ ሳይሆን፥ ትክክል ያልሆኑ መሪዎች ሊመሩትም ጭምር ነው። እውነተኛ የሆኑ መሪዎች ሲጠፉ፥

- የመሪነቱን ሥፍራ የሚይዙት ጥቅም ፈላጊዎች፥ ምንም ዓይነት ልምምድ የሌላቸው፥ በአዕምሮአቸው ያልበሰሉ፥ ተንኮለኞች፥ ለመንጋው የማይራሩ፣ የመሪነቱን ሥፍራ መያዝ ይጀምራሉ።
- ስጦታውም ሆነ ጥሪው የሌላቸው ሰዎች መሪ ሲሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጤናማ ያልሆኑ አንዳንድ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እንደሚችሉ የታወቀ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን የባረከ መሆኑን የሚገልጽበት አንደኛው መንገድ፥ ትክክለኛና ብቃት ያላቸው መሪዎችን ለሕዝቡ ሲሰጥ ነበር። ዛሬ በተለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ግጭት በብዛት የሚታይበት፣



ችግራቸው ከምዕመናኑ አካባቢ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን፥ ያለቦታቸው፥ ያለጥሪያቸው በመሪነት ሥፍራ የተቀመጡ ሰዎች በሚፈጥሯቸው ችግሮች ምክንያት ነው። ቤተ ክርስቲያንን ለመምራትና ለማስተዳደር የተጠሩና የተመሰከረ ፀጋ ያላቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የት ሄዱ? በአዕምሯቸው የበሰሉ፣ በመንፈሳዊ ዕውቀት የዳበሩ፥ ከእግዚአብሔር ጥበብን የተቀበሉ፥ ቤተ ክርስቲያንን ሊመሩ የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ጨርሶ የሉም ማለት ነው? ወይስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ለመሆን ያለውን ከፍተኛ ትግልና ውጊያ በመፍራት ሁሉም ዳር የተቀመጡ በመሆናቸው ይሆን? ይሄ ጥያቄ ሰፊ ምርምርና ጥናት እንዲሁም ውይይት የሚጠይቅ ነው። በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቃት ያላቸው የመሪዎች እጥረት ጎልቶ እንዲታይ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ሦስቱን ለመጥቀስ እንወዳለን። እነርሱም፥

### 2.1. በቂ የሆነ የአመራር ስጦታ ያላቸው አማኞች ወደ አገልግሎት አለመግባት

ሚሲዮናውያን ወንጌልን ሰበኩልን፤ ከጌታ ጋር አስተዋወቁን። ለዚህ ከፍተኛ አገልግሎታቸው ምስጋናችን ትልቅ ነው። ይሁን እንጂ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እንደሚገባው አላስተማሩንም። በአንድ ጥሩ መንፈሳዊ መሪ ሥር ሆነን ቤተ ክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ ስትመራ እያየን አላደግንም። ጥፋቱ የሚሲዮናውያን ብቻ አይደለም። አንዳንዶቻችን እንዲያስተምሩን ዕድሉን ብቻ ሳይሆን፣ በቂ ጊዜም አልሰጠናቸውም። ሳናድግ "አደግን" ብለን ትተናቸው ወጣን። የራሳችንን ቤተ ክርስቲያን መሰርተን መሪዎች ሆነን ማገልገል ጀመርን። ጊዜው የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ዘመን ስለ ነበረ ትኩረታችን በነፍሳት መዳን ላይ እንጂ፥ የዳኑትን እየኮተኮቱ በማሳደግ፥ ያደጉትን ለአገልግሎት በማብቃት ወይም በማስታጠቅ ላይ አልነበረም። ለእኛ የቤተ ክርስቲያን አመራር ማለት "ከፕሮግራም ማውጣት" ያለፈ አልነበረም። *"ዕሁድ አከሌ ይሰብካል፤ አከሌ ስብሰባ ይመራል፤ መዘምራን ይዘምራሉ"* በማለት ፕሮግራም እናወጣለን። የተደለደሉት ሰዎች በወቅቱ ተዘጋጅተው በመቅረብ የተሰጣቸውን አገልግሎት ይፈጽማሉ። ምዕመናኖቻችን የምንመግባቸው መንፈሳዊ ምግብ ምን ያህል እንዳሳደጋቸው የምንለካበት ሚዛን ወይም የምናውቅበት መንገድ አልነበረንም። የቤተ ክርስቲያኖቻችንን ዕድገት የምንለካው ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጣው የሕዝብ ብዛት ወይም ቁጥር፥ እንዲሁም በስብሰባዎቻችን ሞቅታና በምናካሂዳቸው ኮንፍራንሶች ብዛት ነበር። እኛም ራሳችን ችሎታ ባለው መንፈሳዊ መሪ ሥር ሆነን የተገለገልን ባለመሆናችን፥ ከእኛ ሥር ያሉትንም ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ወይም አመራር ለማስተማርም ሆነ በተግባር ለማሳየት ችሎታም ሆነ ጊዜው አልነበረንም። ስለዚህ በአሁኑ ዘመን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ አንዳንድ ችግሮች ሲከሰቱ ብናይ ይህን ያህል ሊደንቀን አይገባም። በአሁኑ ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን

መሪዎች እኛ ከነበረን የበለጠ የመማርና የማወቅ ዕድል አላቸው። ሌላው ቢቀር ለመማር ፈቃደኞች ቢሆኑ፥ እኛ ካበላሸናቸው ነገሮች መማር ይችሉ ነበር። ይሁን እንጂ ለመማር ፈቃደኞች አይመስሉም።

የቤተ ክርስቲያን አመራርን በሚመለከት ነጥብ ላይ አንድ ሌላ ችግር አለ። ጥንት የእኛ ችግር የአስተማሪዎች ማጣት ሲሆን፥ የአሁኑ ችግር ግን የአስተማሪዎች መብዛት ነው። የአስተማሪዎች መብዛት ችግሩ ምንድነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ ያሉትም ሆኑ እንዲሁም ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ እየሄዱ "የመሪዎች ሥልጠና እንሰጣለን" የሚሉት ቁጥራቸው እየጨመረ ሲሄድ ስናይ ያሳስበናል። አሳሳቢ የሆነብንም የአስተማሪዎቹ ቁጥር መብዛቱ ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጠና ለመስጠት እነዚህ ሰዎች ብቃት አላቸው ወይ? የሚሰጡት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ? በማለት ነው። መሪ ሆነው ሳያውቁ፣ ወይም በመሪነት ሥፍራ ተቀምጠው ራሳቸው ሳይለማመዱ "መሪዎችን እናሰለጥናለን" ማለታቸው፣ ሳይማሩ አስተማሪዎች በመሆናቸው ለቤተ ክርስቲያን ጤናማ የሆነ ነገር መስጠታቸው ያጠራጥረናል። ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ሆና ማደግ የምትችለው፥ ጤናማ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያልሆነ ወይም ትክክለኛ የሆነ ዶክትሪን ባላቸው መንፈሳዊ መሪዎች የምትመራ እንደሆነ ብቻ ነው። ሥልጠና ሰጪዎች ራሳቸው በቂ ትምህርት የሌላቸው ከሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ የሃይማኖት ልምምድ ያላቸው፥ ትክክል ያልሆነ ዶክትሪን የሚከተሉ ከሆነ፥ ወጣት መሪዎችን በእንግዳ ትምህርት የሚበርዙ በመሆናቸው፥ ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ የሚያደርሱት ጉዳት ስለሚያመዝን፥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል።

መሪ እንድንሆን ስንጠራ ብቃታችንን በመጠራጠር ብናመነታ ሊደንቀን አይገባም። እግዚአብሔር ሰዎችን ለመሪነት ሲጠራ፣ ኃላፊነቱን መቀበል ሲያመነቱ የሚታዩት ዛሬ ብቻ ሳይሆን፣ ከጥንትም ጀምሮ የነበረ በመሆኑ አይደንቀንም። ሙሴ፣ ጌዲዮን፣ ኤርምያስ፣ አስቴር፣ ወዘተ. እግዚአብሔር ሲጠራቸው እንዳመነቱ እናውቃለን። ሙሴን እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራው፣ *"ወደ ፈርዖን የምሄድና የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማነኝ?"* አለው (ዘጸአት 3፥11)። ሙሴ የተጠራጠረው የራሱን ብቃት ብቻ አልነበረም። የላከውን አምላክ የእስራኤል ልጆች የሚቀበሉት ስላልመሰለው፣ *"የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ልኮኛል' ስላቸው 'ስሙ ማነው?' ቢሉኝ ምን እላቸዋለሁ?"* አለው (ዘጸ. 3፥13)። ሙሴ ሌላ የፈራው "ባያምኑኝስ፣ ቃሌን ባይቀበሉስ፣ እግዚአብሔር አልተገለጠልህም ቢሉኝስ?" ብሎ በማሰብ ነው (ዘጸ. 4፥1)። ለጥያቄው ሁሉ እግዚአብሔር አስፈላጊውን መልስ ቢሰጠውም፣ ችሎታው በጣም ስላጠራጠረው፣ ኃላፊነቱም በጣም ስላስፈራው፣ እግዚአብሔርን *"ጌታ ሆይ! ቀድሞም ሆነ አንተ ከባሪያህ ጋር ከተነጋገርህ ወዲህ ከቶ አንደበተ ርቱዕ ሰው አይደለሁም። እኔ ኮልታፋና ንግግር የማልችል ሰው ነኝ..."* (ዘጸ. 4፥10)— *"ጌታ ሆይ! እባክህ ሌላ ሰው ላክ አለው"* (ዘጸ. 4፥13)። *"በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ በሙሴ ላይ ነደደ..."* (ዘጸ. 4፥14) ይላል። ሙሴ መሪ ለመሆን ያመነታበት ምክንያት ከዚህ በፊት ግብጽ በነበረበት ወቅት የራሱ ሰዎች ስላልተቀበሉት ይሆናል። ጌዲዮንም ከሙሴ የተለየ አልነበረም። *"እግዚአብሔር ወደ እርሱ ዞሮ ብሎ 'ሂድ ባለህ ኃይል እስራኤላውያንን ከምድያማውያን እጅ ነጻ እንድታወጣ የምልክህ እኔ አይደለሁምን?"* (መሳ. 6፥14) ሲለው፣ ጌዲዮን መሪ የመሆን ችሎታውን ስለተጠራጠረ *"ጌታ ሆይ! የእኔ ጎሣ ከምናሴ ነገድ እጅግ ደካማ ነው፤ ከቤተሰቤም እኔ የመጨረሻ ነኝ፤ ታዲያ እንዴት እኔ እስራኤልን ላድን እችላለሁ?"* (መሳ. 6፥15) አለው። እግዚአብሔር የተጠራበትን አላማ የሚያስፈጽምበትን ኃይልና ጥበብን ሳይሰጥ፣ ወይም ሳያስችል ማንንም ለመሪነት አይጠራም። እግዚአብሔር ኤርምያስን ገና በማህጸን ውስጥ ሳይጸነስ ጀምሮ ለአገልግሎት እንዳለበው ሲነግረው፣ *"በማሕፀን ሳልሠራህ ዐውቅሁህ፤ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፤ ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን ሾምሁህ"* አለው (ኤር. 1፥5)። ኤርምያስ ግን ችሎታውን ተጠራጥሮ *"ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እንዴት እንደምናገር አላውቅም፤ ገና ሕጻን ልጅ ነኝና"* አለው (ኤር. 1፥6)። መንፈሳዊ ብስለት ያለው ማንም አማኝ፣ ከእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ ሲደርሰው፣ ጥሪውን የሚቀበለው ራሱን ዝቅ በማድረግ እንጂ ባለው ዕውቀትና ችሎታ ተደግፎ አይደለም።



መንፈሳዊ መሪዎች ከላይ የተቀበሉትን እንጂ ከራሳቸው የሆነ ኃይል እንደሌላቸው እንዲሁም የሰውን ባዶነት ሊያሟላ የሚችል መለኮታዊ ምንጭ ከየት እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። እግዚአብሔር የጠራቸው ከእርሱ ያገኙትን እንዲያከፋፍሉ እንጂ ራሳቸው እንዲያመርቱ አይደለም። በአንድ ወቅት ኢየሱስን ተከትሎ የሄደው 6 ሺ ሕዝብ ምድረ በዳ ውስጥ ፈሰሶ ይታይ ነበር። ኢየሱስ ሕዝቡን በማስተማር ረጅም ጊዜ በመውሰዱ፣ የጊዜውን መምሸት የተገነዘቡ ደቀ መዛሙርቱ፣ ያንን ሁሉ ሕዝብ በዚያ ምድረ በዳ መመገብ እንደማይችሉ በመገንዘብ፥ መፍትሄ ይሆናል ብለው የሚያስቡትን ምክር ለኢየሱስ አቀረቡለት። *"በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው 'ይህ ቦታ በረሓ ነው፤ ቀኑም መሽቶአል፤ ስለዚህ ሕዝቡ በአቅራቢያ ወዳሉት መንደሮች ሄደው ምግባቸውን እንዲገዙ አሰናብታቸው"* አሉት (የማቴ. 14፥16)። በርህራሄ የተሞላው ጌታ ግን ባዶቻቸውን ሊሸኙአቸው የፈለጉትን ደቀ መዛሙርት፣ *"እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ እነርሱ እንዲሁ ሊሄዱ አይገባም"* አላቸው። በዚያን ወቅት ኢየሱስ *"እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው"* ሲላቸው፣ ደቀ መዛሙርቱን "አምራቾች ሁኑ" ያላቸው መስሏቸው ነበር። ጭንቀት የሆነባቸው፣ የሌላቸውን ለመስጠት በማሰባቸው ነበር። በምድረ በዳ የዚያን ሁሉ ሕዝብ ፍላጎት ማሟላት የሚችለው እግዚአብሔር ራሱ ብቻ ነው። ደቀ መዛሙርቱ አገልግሎታቸው ማከፋፈል እንጂ ማምረት አለመሆኑን በወቅቱ አልተገነዘቡትም ነበር። የብዙዎቻችን ችግር ብዙ ጊዜ የሌለንን ለመስጠት መሞከራችን ነው። የእኛ ድርሻ፥ ከራሳችን ማመን

ጨት ሳይሆን፣ ማመንጨት ከሚችለው ጌታ ተቀብለን፣ መንፈሳዊ ረሀብ ላለባቸው ሕዝቦቹ ማከፋፈል ብቻ ነው።

## 2.2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ጦርነት ፈርተው የሚሸሹ አማኞች መብዛት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪዎች እጥረት ሊኖር የቻለበት ሌላው ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ጦርነት ፈርተው ከቤተ ክርስቲያን የሚሸሹ ሰዎች ቁጥር መብዛት ነው። ብዙዎች ጌታን የማገልገል ጥማት አላቸው። እግዚአብሔር በስጦታቸው የተፈጥሮ ስጦታ፥ መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ ባሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ይፈልጋሉ። ለማገልገልም የሚፈልጉት "ጥቅም እናገኝበታለን1 እንከበርበታለን" ብለው በማሰብ ሳይሆን፥ ለጌታ ባላቸው ፍቅር ምክንያት መስዋዕት ቢያስከፍልም፥ "ለመክፈል ፈቃደኞች ነን" ብለው ነው። ይሁን እንጂ፥ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ አገልግሎትን በሚመለከት ምክንያት የሚካሄደውን ከፍተኛ ጦርነት፥ ያለውን እሽቅድምድም፥ ያለውን የእርስ በርስ መጠላለፍ ሲመለከቱ፥ በእኛም ላይ ተመሳሳይ የሆነ ችግር ደርሶብን ከጉዳት ላይ እንወድቅ ይሆን? በማለት ዳር ሆነው መመልከቱን ይመርጣሉ። የተማሩ፥ ችሎታ ያላቸው፥ ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸው፥ "አገልግሎትን ለጥቅም ማዋል ትክክል አይደለም" ብለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች "ለአገልግሎት ብዬ ከማንም ጋር መጋጨት አልፈልግም" በማለት፣ ከአገልግሎት ሸሽተው የተቀመጡ በመብዛታቸው፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪዎች እጥረት ይታያል።

## 2.3. በጦርነቱ ቁስለኛ ሆነው ከአገልግሎት የሚወጡት ቁጥራቸው መጨመር

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪዎች እጥረት ሊኖር የቻለበት ሌላው ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየጊዜው በሚፈጠሩት ልዩ ልዩ ጦርነቶች ምክንያት ቆስለው ከአገልግሎት የሚወጡ ሰዎች ቁጥር መብዛት ነው። በተለያየ አገልግሎት ውስጥ ገብቶ ማገልገል የሚያስከፍለውን ከፍተኛ ዋጋ በደንብ ሳይረዱ ወደ አገልግሎት የሚገቡ አማኞች አሉ። በተመደቡበት ሥፍራ አገልግሎታቸውን በቅንነት ለመፈጸም ሲሯሯጡ፥ አንዳንድ ይሆናል ብለው ያልጠበቁት ጤናማ ያልሆኑ ሁኔታዎች ያጋጥሟቸዋል። ለጥቂት ጊዜ ታግሰው ሲያቅታቸው፣ አገልግሎታቸውን እየተዉ ይወጣሉ። በአዲስ ኪዳንም ሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የተጠራችበትን የወንጌል ተልክ ለመፈጸም፣ በብዙ ተቃውሞና ችግር ውስጥ እንዳለፈች እናውቃለን። በታሪክ ብቻ ሳይሆን፣ በእኛም ሕይወት ውስጥ አጋጥሞን አይተናል። ሁኔታዎች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ወቅት በትግላቸው አሸናፊዎች ሆነው መቆም እንዲችሉ እግዚአብሔር ጸጋውን



እንዲያበዛላቸው ወደ ጌታ መጮኽ እንዳለባቸው ቢያውቁም፣ ተስፋ ቆርጠው ከአገልግሎት ብቻ ሳይሆን፣ ከቤተ ክርስቲያንም የሚሸሹ ክርስቲያኖች ጥቂቶች አይደሉም። በሐዋርያት ዘመን አንዳንድ የአስተዳደር ችግር ሲፈጠር ተሰብስበው ለችግሩ መፍትሄ በመፈለግ ችግራቸውን ያቃልሉት ነበር (የሐዋ. 6)። የዶክትሪን መለያየት በመካከላቸው ተፈጥሮ ሲለያያቸው ሲሞክር፣ ተሰብስበው ልዩነታቸውን ያስታርቁ ወይም ያስተካክሉ ነበር (የሐዋ. 15)። በአሁኑ ዘመን ግን መጋጨት እንጂ ዕርቅ ሲሆን ስለማይታይ፣ ብዙዎች ታግሰው በመቀጠል ፈንታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው ጦርነት ቆስለው፣ ከቤተ ክርስቲያን ሸሽተው ይኖራሉ። ይሄም መንፈሳዊ መሪዎችን ያሳጣን ሌላው ምክንያት ነው።

## 3. በሥርዓት ማስተዳደር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው

"መሪነት" (Leadership) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ይህም ማለት በዓለም ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ መንፈሳዊነት ባለው ሕብረት ውስጥም "መሪና ተመሪ" እንዲኖር መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፈዋል። የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪነትን ደረጃ ወይም ሥፍራ የያዘው ሰው፥ ሌሎች በመሪነቱ አምነው እንዲከተሉት ቢጠይቅ፥ ራሱን ማተለቁ ወይም እምባ ገነን ማድረግ የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች አይጠፉም። መንፈሳዊ መሪዎች በዓለም ውስጥ እንዳሉት መሪዎች፣ በራሳቸው ፈቃድ ደስ ያላቸውን እንደሚያደርጉት አይደሉም። መንፈሳዊ መሪዎች አመራራቸው ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት፥ የሚመሩት ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዓላማ ለመፈጸም እንዲችል እንዴት ማስተባበር እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መመሪያ ያላቸው ናቸው። "መሪነት" መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ያልተገነዘቡ አንዳንድ ክርስቲያኖች፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ሁላችንም እኩል ስለሆንን ማንም ሌላውን ይህን አድርግ፥ ወይም አታድርግ በማለት ትዕዛዝ መስጠት የለበትም" ብለው የሚያስቡ እንዳሉ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር ከራሱ ሕዝብ ጋር የነበረውን እንቅስቃሴ የሚያሳየው ታሪክ እንደሚያስረዳው፥ ዓላማውንና ፈቃዱን ይፈጽም የነበረው፥ መሪ አድርጎ በመረጣቸው ወይም በሾማቸው ሰዎች አማካኝነት ነበር።

አብርሃምን ከዑር አውጥቶ ከነአን ሲልከው፥ ሙሴን ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት እንዲያወጣ መሪ አድርጎ ሲሾመው፥ ሕዝቡን ከነአን እንዲያስገባ ኢያሱን ከሙሴ በኋላ ሲጠራው፥ ለረጅም ጊዜ ሕዝቡን እንዲያስተዳደሩ መሳፍንትንና ነገሥታትን፥ ቀጥሎ ነብያትን፥ በመጨረሻም በአዲስ ኪዳን ዘመን ቤተ ክርስቲያንን እንዲጀምሩና እንዲመሩ ሐዋርያትን ሲያስነሳ፥ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም እርሱ ራሱ በመረጣቸው መሪዎች እንደተጠቀመ ወይም ይሠራ እንደነበረ መረዳት እንችላለን።

እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚፈልገውን ዓላማ ለመፈጸም ሲያስብ ብቻውን የፈለገውን መሥራት ቢችልም፥ ሁልጊዜ በቅድሚያ ሕዝቡን ሊመራ የሚችለውን ሰው እንደሚፈልግ ቀደም ሲል ገልጸናል። ይህን ዓይነቱ የእግዚአብሔር አሠራር በአዲስ ኪዳንም ዘመን የቀጠለ በመሆኑ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች መኖራቸው ከእግዚአብሔር አሠራር ውጪ እንዳልሆነ እንረዳለን። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑም "መሪዎችን" የሚያስቀምጥ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እርሱ ራሱ በመሠረተው መሠረት ላይ እንዲያገለግሉ፥ ሕዝቡን እንዲመሩ ሙሉ ሥልጣን ለመጀመሪያ የሰጠው ለሐዋርያት ነው። ጳውሎስ *"...በሐዋርያትና በነቢያትም መሠረት ላይ ታንጻችኋል"* (ኤፌ. 2፥20) ይላል። ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያትና በነብያት ትምህርት ከተመሠረተች በኋላ፥ ሽማግሌዎችና ዲያቆናት የቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ መሪዎች እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ሽማግሌ" የሚለው ቃል ለማገልገል ዕድሜ ወሳኝ ነው ማለት አይደለም። ጳውሎስ *"...ስጦታችን ማስተዳደር ከሆነ በትጋት እናስተዳድር..."* (ሮሜ 12፥8) ሲል፥ "ማስተዳደር" ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ መሆኑን እናያለን። ለዚህ ነው የራሱን ቤት ማስተዳደር የማይችል ሰው ሽማግሌ መሆን እንደሌለበት ጳውሎስ የገለጸው (1 ጢሞ. 8፥5)። እግዚአብሔር ቤቱን እንዲያስተዳድሩ የመረጣቸው ሰዎች፥ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሥልጣን እንደሚገባው እንዲጠቀሙ፥ ሌሎችም መሪዎቻቸውን እንዲታዘዙና እንዲያከብሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል (1 ጢሞ. 5፥17)።

## 4. የአስተዳደር (የአመራር) ዓይነቶች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ የአስተዳደር ወይም የአመራር ስልቶች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን "በዚህ ዓይነት የአስተዳደር ስልት መመራት አለባት" ብሎ በግልጽ ስለማይናገር፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ትክክል የመሰላቸውን ወይም አመቺ ነው ብለው የሚሉትን የአስተዳደር ስልት ይከተላሉ። ጎልተው ከሚታዩት የአስተዳደር ዓይነቶች መካከል ጥቂቶቹን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 4.1. "አውቶክራሲ" (Autocracy) - ገደብ የሌለው ሥልጣን ባለው፥ አንድ ሰው የሚመራ

*"አውቶክራቲክ"* የሆነ የአመራር ሥርዓት፥ አንድ ሰው ብቻ በአስተዳደሩ ውስጥ ገደብ የሌለው ከፍተኛ ሥልጣን ሲኖረው ነው። ይሄ "አንዱ ሰው" በተለያየ ስም ሊጠራ ይችላል–*ጳጳስ፥ መጋቢ (ፓስተር)፥ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ* ሊሆን ይችላል። ገደብ የሌለውን ዓይነት ሥልጣን የሚይዘው ጥሩ ወይም መጥፎ፣ ቅን ወይም ክፉ፣ እምባገነን ወይም ትሁት የሆነ መሪ ሊሆን ይችላል። አውቶክራቲክ የሆነ የቤተ ክርስቲያን የአመራር ሥርዓት ከሚከተሉት ቤተ እምነቶች መካከል አንደኛው የሮማ ካቶሊክ ቤተ እምነት



ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉት የካቶሊክ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ፣ ሮም ባለው ሊቀ ጳጳስ ሥር ናቸው። ይህን ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን አመራር ለምን እንደሚከተሉ ምክንያት ሲሰጡ፥ *"የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለመጠበቅ ነው"* ይላሉ። ይሁን እንጂ፥ እንዲህ ዓይነቱ አመራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ቤተ ክርስቲያን በምን ዓይነት የአመራር ሥርዓት ውስጥ መሆን እንዳለባት መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ያለ መመሪያ ስለማይሰጥ፥ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸው የሆነ የአስተዳደር ሥርዓት እንዳላቸው የታወቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፥ በቤተ ክርስቲያን አመራር ሥልጣን ላይ ያሉትን *"...የሚያስተዳድሩ..."* (1 ጢሞ. 5፥17፥ ሮሜ 12፥8) ሲላቸው፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምዕመናኑ የበላይ ጠባቂዎች ወይም አስተዳዳሪዎች እንዲሆኑ ሥልጣን ያላቸው መሆናቸውን ያሳያል። ይሁን እንጂ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን "እምባገነን" በሆነ በአንድም ሆነ በጥቂት ሰዎች እንድትመራ እግዚአብሔር አይፈቅድም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ ሥልጣን በተጠማ በአንድ እምባገነን ሰው እንድትመራ ባይፈቅድም፥ በአሁኑ ጊዜ በዚህ ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የሚሞክሩ መሪዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። አንድ ሰው ለብቻው ገደብ የሌለውን ዓይነት ሥልጣን መያዝ የሚፈልገው፣ በሚመራው ቤተ ክርስቲያን ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዲኖረው፣ የፈቀደውን ለማድረግ ነጻነት እንዲያገኝ ነው። አሠራራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊነት እንዳለው ለማስመሰል፣ "ቤተ ክርስቲያናችን የምትከተለው 'የመጋቢ አመራር ሥርዓት' (Pastoral Leadership) ነው" ይላሉ። ያልተረዱት ግን "በመጋቢ የአመራር ሥርዓት" መሆን ማለት፣ "አንድ ሰው ገደብ የሌለው ሥልጣን ይይዛል" እንዲሁም መሪው ለማንም ተጠያቂነት ሰሌለው የፈለገውን ማድረግ ይችላል ማለት አይደለም። ይህን ዓይነቱ የአመራር ሥልት ከሚታይበት ድካም አንደኛው፥ ያ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለብቻው ለመምራት የሚሞክረው ሰው፥ የሚቆጣጠረው ስለሌለው፣ ወይም በማንም ዘንድ ተጠያቂነት ስለማይኖረው፣ የፈቀደውንና የመሰለውን ስለሚያደርግ፣ ራሱንም ሆነ የሚመራቸውን ሰዎች ሊጎዳ የሚችል መሆኑ ነው። እንዲህ ዓይነቱ እምባገነን መሪ በተለያየ ምክንያት በመንፈሳዊ ሕይወቱ ቢያዳልጠው፥ እንዳይወድቅ ደግፎ የሚያቆመው ሰው አይኖረውም።

"አውቶክራቲክ" በሆነ አመራር ሥር የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት፣ የአስተዳደሩን ሙሉ ሥልጣን አንድ ሰው ብቻውን ይዞ ለመምራት ሲሞክር ይታያል። ያ ብቻውን የሚመራው አንድ ሰው፣ መጋቢ (ፓስተር)፥ የሽማግሌዎች ሊቀ መንበር፥ ወይም ዋና ሰብሳቢ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያኒቷን ማስተዳደር የሚሞክረው በሲ.ኢ.ኦ. "CEO" ሞዴል ይሆናል። ይኸውም፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከናወኑትን እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከላይ ሆኖ የሚመራው፥ ማንኛውንም ነገር የሚቆጣጠረው አንድ ሰው ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠረው ወይም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚወሰኑትን ውሳኔዎች ሁሉ የሚወስነው ያ አንዱ ሰው ብቻ ነው። እርሱ ካልፈቀደ፥ የእርሱ ፊርማ ከሌለበት ምንም ነገር አይሠራም፤ ሁሉም ነገር ቀጥ ብሎ ይቆማል። በብሉይ

ኪዳን ዘመን፥ አንድ ሰው ገደብ የሌለው ሥልጣን ይዞ ሲያስተዳድር ወይም ሲመራ በግልጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው፥ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት አውጥቶ እየመራ ወደ ተስፋይቱ ምድር፥ ወደ ከነአን እንዲያደርስ በእግዚአብሔር የተሾመው ሙሴ ነበር። የሙሴ ችግር ካለማወቅ የመጣ እንጂ፥ የሥልጣን ጥማት ኖሮት፣ ወይም አምባገነን ለመሆን ፈልጎ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይህን ዓይነቱ አመራር ይጎዳ የነበረው ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን፥ ራሱን ሙሴንም ጭምር ነበር። *"በማግሥቱም ሙሴ በሕዝቡ መካከል ያለውን ጠብና ክርክር በዳኝነት ለማየት ተቀመጠ፤ ሕዝቡም በዙሪያው ቆመው ሥራ በዝቶበት ከጠዋት እስከ ማታ ቆየ"* (ዘጸ. 18፥18) ይላል። እዚህ ላይ፣ እስራኤላውያን የተጣሉበትን ምክንያት ሲያቀርቡለት ሰምቶ ለመዳኘት ጥበብና ሥልጣን አለው ብለው የሚያምኑትን ሙሴን ለማነጋገር በየቀኑ ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ተሰልፈው የሚጠብቁ ብዙ ሰዎች እንደነበሩ እናውቃለን። በዚያን ወቅት ከጥዋት እስከ ማታ ሙሴ ለብቻው የሚለፋበትን ሥራ አንዳንድ ሰዎች ተመርጠው ኃላፊነት ቢሰጣቸው ሊሠሩት እንደሚችሉ በዚያን ወቅት አልተረዳም ነበር። ይህን ሁኔታ አይቶ በሙሴ የአስተዳደር ዕውቀት ያልተደሰተው፥ የትሮ የተባለው የሚስቱ አባት፤ *"ለህዝቡ የምታደርገው ይህ ሁሉ ድካም ምንድን ነው? ሕዝቡ አንተን ለማነጋገር በመፈለግ ከጠዋት እስከ ማታ በዙሪያህ ቆመው ይህን ሁሉ ጉዳይ በዳኝነት ለማየት ስለምን ብቻህን ትቀመጣለህ?"* ብሎ ጠየቀው (ዘጸ. 18፥14)። ሙሴም ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጥ *"እኔ ይህን ሁሉ የማደርግበት ምክንያት ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ወደ እኔ ስለሚመጡ ነው፥ ሁለት ሰዎች ተጣልተውም ወደ እኔ ቢመጡ የትኛው ወገን ትክክል እንደሆነ ለማሳወቅ የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ እነግራቸዋለሁ"* አለ (ዘጸ. 18፥15-18)።

ሙሴ የተከተለው የአመራር ሥልት ትክክል አለመሆኑን የትሮ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ሙሴ ይከተል የነበረውን የአስተዳደር ስህተት አይቶ ዝም በማለት ፈንታ *"ይህ የምታደርገው ነገር ሁሉ ትክክል አይደለም፤ አንተን ራስህንም ሆነ ሕዝቡን በከንቱ ታደክማለህ፥ ብቻህን ሆነህ ይህን ሁሉ ለመሥራት ይከብድሃል"* አለው (ዘጸ. 18፥17-18)። ሙሴ ሥራውንና ኃላፊነቱን ለሌሎች በማከፋፈል ፈንታ ሥራውን ሁሉ ለብቻው ለመሥራት መሞከሩ ራሱን ማድከሙ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎችም በአስተዳደር ሙያ እንዳያድጉ ዕድል መከልከሉ ነበር። የአስተዳደር ችሎታ በተፈጥሮ የሚገኝ ብቻ ሳይሆን፣ በትምህርትና በመለማመድም የሚገኝ ነው። አንዱ እማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታው "አስተዳደር" ቢሆን እንኳ፣ ስጦታውን በተግባር ላይ በማዋል አገልግሎቱን የማዳበር ኃላፊነት አለበት። የትሮ ለሙሴ ምክር ለመስጠት ሲነሳ፣ የሚሰጠው ምክር እግዚአብሔር ከሚናገረው ውጪ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነበር። *"እነሆ እኔ አንድ ነገር ልምከርህ፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል፤ ሕዝቡን ወክለህ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብህና ጉዳያቸውንም በፊት ማቅረብህ ትክክል ነው"* አለው (ዘጸ. 18፥19)። ይህን ሲል፣ "እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንዲሆን አንድ ምክር ልስጥህ" ማለቱ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በሙሴ ውስጥ ይናገር እንደ ነበረው በየትሮም ውስጥ ይናገር ነበር። አንዳንድ



ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ የሚያስቸግራቸው መሪዎች፥ "ማንም እኔን እንዲህ አድርግ ሲለኝ የሚችል የለም" ብለው ስለሚያምኑ ከማንም ምክርም ሆነ አስተያየት ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም። ሙሴ ግን በጣም ትሁት መሪ ስለነበረ፥ የየትሮን ምክር ተቀብሎ በሥራ ላይ አዋለ። እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት ባረከው እንጂ "የሰው ሀሳብ ለምን ተቀበልክ?" በማለት አልወቀሰውም።

ሙሴ ሕዝቡን የመዳኘትን ኃላፊነት እንዲወስዱ ሌሎችን በኃላፊነት ላይ ሲያስቀምጥ፤ እግዚአብሔር ከሰጠው ኃላፊነት መሸሹ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር የሰጠውን ኃላፊነት በተሻለ መንገድ መሥራቱ፥ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ በአስተዳደር ሙያ እንዲዳብሩ ዕድል መስጠቱ ነበር። አንዳንዱን ሥራ ለአንዳንድ ሰዎች በኃላፊነት ይሰጥ እንጂ እርሱ ማድረግ ያለበትን ትልቅ ሥራ ወይም ኃላፊነት ግን ችላ አላለም ነበር። የትሮ ሙሴ ሊያደርግ የሚገባውን ሥራ ሲገልጽለት፤ *"አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ልታስተምራቸው፥ እንዴሁም እንዴት መኖርና ምን ማድረግ እንደሚገባቸውም ልትገልጥላቸው ይገባል"* አለው (ዘጸ. 18፥20)። ሙሴ ማስተማር ብቻ ሳይሆን፤ ለሥራው ይገባሉ ብሎ ያሰባቸውን ሰዎችንም የመምረጥም ኃላፊነትም ነበረበት። *"ሙሴም የየትሮን ምክር ሁሉ ተቀብሎ በሥራ ላይ አዋለው። ከእስራኤላውያንም ሁሉ መካከል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መረጠ፥ እነርሱንም የሺ አለቆች፤ የመቶ አለቆች፤ የኀምሳ አለቆችና የዐሥር አለቆች አድርጎ በሕዝቡ ላይ ሾማቸው"* (ዘጸ. 18፥24-25)። ሙሴ ሥራውን ለሌሎች ያከፋፍል እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተጠያቂነትና ኃላፊነት ግን ሊያስተላልፍ አይችልም። ውክልና የሰጣቸው ሰዎች ቢበቁና ሥራውን ቢያበላሹ፥ "እግዚአብሔር ሆይ! የእኔ ጥፋት አይደለም። ያበላሹት ውክልናውን የሰጠኋቸው ሰዎች ስለሆኑ፣ እኔ ከተጠያቂነት ነጻ ነኝ" ማለት አይችልም።

ሙሴ ውክልናውን የሰጣቸው (የሾማቸው) *"ከእስራኤላውያን መካከል ችሎታ ያላቸውን ሰዎች"* መርጦ እንጂ ዝም ብሎ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ችሎታ የሌላቸውን በኃላፊነት ላይ ማስቀመጥ ሥራውን መበደል ይሆናል። የትኛውን ሥራ ማን ቢሠራ ጥሩ ውጤት እንደሚያመጣ አውቆ ተገቢዎችን ሰዎች በተገቢው ሥፍራ ለማስቀመጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ለመሪው አስፈላጊውን ጥበብንና ማስተዋልን ይሰጠዋል። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች (ፓስተሮች) ሥራውን ሁሉ ብቻቸውን ሠርተው መጨረስ እንደማይችሉ ሲረዱ፥ የአገልግሎታቸው ተባባሪዎች እንዲሆኑ የሚመርጧቸው ሰዎች በችሎታቸው፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ብርቱ የሆኑትን፥ ኃላፊነት መቀበል የሚችሉትን ሳይሆን፥ *"ወዳጄ ነው፤ ይደግፈኛል፤ የሚቃወሙኝን ሁሉ ከኋላ ቆሞ ይቃወምልኛል፤ ... በችሎታቸው ከእኔ የተሻሉ ባለመሆናቸው ሥልጣኔን ይወስዱብኛል"* ብለው የማይፈሩቸውን ሰዎች ብቻ ነው። በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚጎዳው፥ ምዕመናን እንደሚገባው የማይገለገሉት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮችና ጭቅጭቆች ሲፈጠሩ የምናየው፣ ከምክንያቶቹ መካከል ከላይ የገለጽነው ሁኔታ አንደኛው ነው። የትሮ ሙሴ የሚመርጣቸው ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ሲነግረው፤

*"...እነርሱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ፤ እምነት የሚጣልባቸውና በጉቦም የማይደለሉ ሰዎች መሆን አለባቸው"* አለው (ዘጸ. 18፥21)።

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራውን ሁሉ ለሌሎች አከፋፍለው፣ እነርሱ ግን እጆቻቸውን አጣምረው የሚቀመጡ፥ እንቅልፋቸውን የሚለጥጡ፥ ባለጸጋ ናቸው ከሚሏቸው ሰዎች ቤት እየዞሩ የሚበሉ እንዳሉ የታወቀ ነው። ሙሴ ሥራውን ያከፋፍል እንጂ፥ የራሱ የሆነ የሥራ ድርሻ እንዳለው ዮትር ሲገልጽለት *"...ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ከባድ ጉዳይ ወደ አንተ ያምጡት፥ እነርሱ በዚህ ዐይነት ሸክምህን ቢካፈሉልህ ሥራው ይቀልልሃል። በዚህ ዐይነት ብትሠራና ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ራስህን በከንቱ ኢታደክምም፥ ሕዝቡም በቀላሉ ጉዳያቸው እየተፈጸመላቸው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ"* አለው (ዘጸ. 18፥22-23)። አንድ ሰው ብቻውን "ገደብ የሌለው ሥልጣን" የሚይዝበት ምክንያት ምን ይሆን?

1ኛ) አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ሥራ ሁሉ እነርሱ ካልሠሩት የሚበላሽ ስለሚመስላቸው ብቻ ነው። ምክንያታቸው ከቅን ልብ የመጣ ሊሆን ይችላል። ኃላፊነቱን የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ስለሆነ፥ ሌላው ለመሥራት ሞክሮ ቢያበላሸው፥ ተጠያቂነት አለብን ብለው ስለሚያስቡ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱን በር ለመክፈት እንኳን ኃላፊነቱን ለሌላ ሰው ቢሰጡና፥ ያ ሰው በሰዓቱ ተገኝቶ ባይከፍት ብዙ ነገር ይበላሻል ብለው ስለሚፈሩ፥ ቀደም ብለው በመሄድ የቤተ ክርስቲያኑ በር ይከፍታሉ።

2ኛ) የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥራ ስሌሎች ቢያከፋፍሉና ሌሎች ጥሩ አድርገው ከሠሩት፥ እነርሱ የማይፈለጉ የሚያደርጋቸው ስለሚመስላቸው ነው። ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ኃላፊነትን ለማንም አይሰጡም። ቢሰጡ እንኳን ችሎታ ላለው ሳይሆን፥ ችሎታ ለሌለው ሰው ብቻ ነው። እነርሱ በማይገኙበት ጊዜ እንዲሰብኩ ዕድል የሚሰጧቸው ሰዎች እንኳን፥ "እኔን ያስንቁኛል" ብለው በመፍራት፥ ዕድል የሚሰጡት፥ ጥሩ መስበክ ለሚችሉት ሳይሆን፥ ችሎታና በቂ ልምምድ ለሌላቸው ነው። ይህን ዓይነቱ አሳብ ቀና ልብ ካለው ሰው የሚወጣ አይደለም።

## 4.2. "ኦሊጋርኪ" (Oligarichy) -ገደብ የሌለው ሥልጣን በያዙ ጥቂት ሰዎች የሚመራ

ሌላው ዓይነት ሞዴል ደግሞ *"ኦሊጋሪኪ" (Oligarichy)* የሚለው ነው። "ኦሊጋርኪ" ከሁለት ቃል የወጣ ነው። እንደኛው *"ኦሊጎ" (Oligo* ሲሆን፥ ትርጉሙም "ጥቂት" ማለት ነው። ሁለተኛው፥ *"አርኪ" (Arche)* ሲሆን ትርጉሙም "አገዛዝ" ማለት ነው። ስለዚህ *"ኦሊጋርኪ"* ማለት *"የጥቂቶች የአገዛዝ ሥርዓት"* ማለት ነው። *"ኦሊጋርኪ"* የአስተዳደሩ ሙሉ ሥልጣን በጥቂት ሰዎች ሲያዝ ነው። በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ከሆነ የተወሰኑ ወይም ጥቂት *"ሽማግሌዎች"* የአመራሩን ሙሉ ሥልጣን ሲይዙ ነው። እነዚህ ሙሉ ሥልጣን የሚይዙት ሽማግሌዎች፣ ቁጥራቸው እንደየቤተ ክርስቲያኑ ይለያል። ኦሊጋርኪ *ከአውቶክራቲክ* ሞዴል የሚለየው፥ ገደብ የሌለው ሥልጣን የሚይዘው አንድ ሰው በመሆን ፈንታ፣ ከአንድ በላይ የሆኑ የተወሰኑ ሰዎች የሚይዙ መሆናቸው ነው። አሁንም የቤተ ክርስቲያኒቱን እቅጣጫ የሚወስኑት፣ ገደብ የሌለው ሥልጣን የሚይዙት ጥቂት "ሽማግሌዎች" ናቸው። እነርሱ ካልፈቀዱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ነገር መደረግ አይቻልም። የአንድ ሰው አምባገነንነት ከአስፈራን፥ ይኼኛው ዓይነት አመራር የበለጠ ሊያስፈራራንና ሊያሳስበን ይገባል። እነዚህ ገደብ የሌለውን ሥልጣን የሚይዙት ሽማግሌዎች ለመሆኑ በመሪነት ሥፍራ ላይ የሚያስቀምጣቸው ማን ነው? በምዕመናኑ የተመረጡ ወይም ቤተ ክርስቲያኑን መጀመሪያ የተከሉ እነርሱ ይሆኑና ብቃት ቢኖራቸውም፣ ባይኖራቸውም ራሳቸውን ሽማግሌዎች ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያኒቱን ያስተዳድራሉ። ሙሉ ሥልጣን ይዘው በማንኛውም ነገር ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ። መጋቢውን ይቀጥራሉ፥ ካልተስማማቸው ከሥራ ያባርራሉ። ይህን ዓይነት አመራር የሚያስከትለውን ችግር መረዳት ይህን ያህል ከባድ አይደለም።

ሽማግሌዎች እንዴት እንደሚመረጡ፥ ምን ዓይነት አቋም ያላቸው ሰዎች ሽማግሌ መሆን እንደሚችሉ በግልጽ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ቢሆንም፣ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌ ሆነው የሚመረጡት መንፈሳዊ ብስለታቸው፥ የቆዩ ክርስቲያኖች መሆናቸው፥ ሕይወታቸውን በቅድስና መምራታቸው ታይቶና ተመዝኖ ሳይሆን፥ ያላቸው ትምህርትና እውቀት፥ በሚሠሩበት መሥሪያ ቤት ያላቸው የሥራ ልምምድ፥ የአስተዳደር ችሎታቸው፥ እንዲሁም ያላቸው ሥልጣን ታይቶ፣ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱ ሀብታም ነጋዴዎች መሆናቸው ታይቶ ነው። እንደነዚህ ዓይነቶች ከተመረጡ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የሚሞክሩት የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መንገድ ሳይሆን፥ እነርሱ በተለማመዱት የአስተዳደር ስልትን በመከተል ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷን ገንዘብ ለአገልግሎት በመጠቀም ፈንታ ባንክ ገንዘብ የሚያጠራቅሙ ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት አመራር ውስጥ ስትሆን ትልቅ ችግር ሊያጋጥማት እንደሚችል የታወቀ ነው። ሌላው ችግር ደግሞ ሽማግሌዎቹ ገደብ የሌለው ሥልጣን ከያዙ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ እንደ "ቅጥር ሠራተኛ" ብቻ ይታይና፥ መጋቢው (ፓስተሩ) ለቤተ ክርስቲያኒቱ እግዚአብሔር የሰጠውን ራዕይ ተከትሎ በማገልገል ፈንታ ሽማግሌዎች የሚሰጡትን መመሪያ እየተከተለ ብቻ የሚያገለግል አገልጋይ ይሆናል። ይሄም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትን አያመጣም።

## 4.3. ዲሞክራሲ (Democracy) በሕዝብ የሚመራ

ሌላው በጣም የተለመደው ሞዴል *"ዲሞክራሲ" (Democracy)* የተባለው ነው። "ዲሞክራሲ" ከሁለት ቃል የወጣ ነው። እንደኛው "ዲሞስ" (Demos) ሲሆን፥ ትርጉሙም

"ሕዝብ" ማለት ነው። ሁለተኛው፥ "ክራቲስ" (Kratis) ሲሆን ትርጉሙም "አመራር" ማለት ነው። ዲሞክራሲ ማለት "በሕዝብ የሚመራ" ማለት ነው። የሕዝብ መብት፥ የሕዝብ ድምፅ፥ የሕዝብ አገዛዝ ማለት ነው። በቤተ ክርስቲያን "ዲሞክራሲ" ሲባል፥ በዛ ባለው ምዕመን የሚመራ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ገደብ የሌለውን ሥልጣን የሚይዘው ምዕመናን ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማንኛውም ዓይነት ውሳኔ የሚወሰነው በድምጽ ብልጫ ነው። በድምጽ ብልጫ የሚወሰን ከሆነ፥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ መጠየቅ፣ መመርመር፣ እንዲሁም ፈቃዱን ለማወቅ መጸምና መጸለይ አያስፈልግም። ይህን ዓይነቱ የአገዛዝ ወይም የአስተዳደር ሥርዓት ቀላል ይምሰል እንጂ ብዙ ጭቅጭቅ የሚፈጥር ነው። ምዕመናኑ መጋቢ ቀጥረው ያስመጣሉ። መጋቢው ተቀጣሪ ስለሆነ ሕዝቡ እንዲያደርግ የሚፈልገውን ሁሉ ያደርጋል። ካልተስማማቸው አሁንም በድምጽ ብልጫ ያሰናብቱታል። መጋቢው ቅጥር ሠራተኛ እንጂ የቤተ ክርስቲያን መሪ አይደለም። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ዕድሜ እንዲኖረው ከፈለገ፥ ምዕመናኑን የግድ ሁልጊዜ ማስደሰት አለበት። ሌላው ቀርቶ ስብከቱ የሚቆረቁራቸው ከሆነ፥ *"ስብከትህ ኃይለኛ ነው፥ ታስተካክል እንደሆን አስተካክል"* ተብሎ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል። መጋቢው እያንዳንዱን ምዕመን መጎብኘት ብቻ ሳይሆን፥ ቤት በቀየሩ ቁጥር ዕቃቸውን የማጓጓዝ ኃላፊነት ያለበት የሚመስላቸውም እንደማይጠፉ ግልጽ ነው። ተለማምጦ ካልኖረ ሥራውን በቀላሉ ያጣል። በዚህ ዓይነት የሚያገለግለው መጋቢ፣ ሌላ ምርጫ ስለሌለው፣ አገልግሎቱን የሚቀበለው እንደ ዕለታዊ ሥራ (ፕሮፌሽን) እንጂ ከእግዚአብሔር ጥሪ አግኝቶ እንደሚያገለግል ተሰምቶት አይደለም። በሕዝቡ የተመረጡትም ሽማግሌዎች አመራሩ በእነርሱ ቁጥጥር ውስጥ እንዲሆን የሚያደርጉት "መጋቢው ከአስተዳደር ሥራ ነጻ ሆኖ በአገልግሎቱ ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርግ ነው" ይላሉ። ይሁን እንጂ አግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑ በዚህ ዓይነት መንገድ እንድትመራ ፈቃዱ አይደለም።

## 4.4. ቲዮክራሲ (Theocracy) ሥልጣኑ የእግዚአብሔር ሲሆን

ሌላው በጣም የተለመደው ሞዴል *"ቲዮክራሲ" (Theocracy)* የተባለው ነው። "ቲዮክራሲ" ከሁለት ቃል የወጣ ነው። አንደኛው "ቲዮስ" (Theos) ሲሆን፥ ትርጉሙም "እግዚአብሔር" ማለት ነው። ሁለተኛው፥ "ክራትየን" (Kratien) ሲሆን ትርጉሙም "አመራር" ማለት ነው። ቲዮክራሲ ማለት "በእግዚአብሔር የሚመራ" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን በንጉሥ አገዛዝ ሥር ከመሆናቸው በፊት፣ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር የሚኖሩ ሕዝቦች እንደ ነበሩ ይታወቃል። ንጉሣቸው ወይም መሪያቸው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነበር። ከአህዛብም የሚለዩበት አንደኛው፥ በእግዚአብሔር አመራር ሥር የሚኖሩ ሕዝቦች በመሆናቸው ነበር። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የመራው፣ እርሱ ራሱ በመረጣቸው ነብያትና እንዲሁም በተለያዩ መሳፍንት አማካኝነት መሆኑን እናውቃለን። እስራኤላውያን ለጥቂት ጊዜ በእግዚአብሔር አመራር



ሥር ከቆዩ በኋላ፥ ያ በቂ ስላልመሰላቸው በአካባቢያቸው የነበሩትን አገሮች የአስተዳደር (የአመራር) ሥርዓት ከተመለከቱ በኋላ፣ የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ሳሙኤል ዘንድ ቀርበው *"...በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው እኛን የሚመራን ንጉሥ አንግሥልን"* ብለው ጠየቁት (1 ሳሙ. 8፥5)። ጥያቄያቸው ሳሙኤልን እንዳስቆጣው የተመለከተ ጌታ *"ሕዝቡ የሚሉህን ነገር ሁሉ ተቀበል፤ እነርሱ የናቁት አንተን አይደለም፤ በእነርሱ ላይ ነግሼ እንዳልኖር የናቁት እኔን ነው"* አለው (1 ሳሙ. 8፥7)። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር የእስራኤል ሕዝብ በጠየቁት መሠረት የሚመራቸው ንጉሥ ሰጣቸው። ይሁን እንጂ፥ እምባገነን የሆኑ መሪዎቻቸው እስጨንቀው ሲገዟቸው፥ "ንጉሥ ይሾምልን" ብለው መጠየቃቸው ትክክል እንዳልነበረ ለመገንዘብ ጊዜ አልፈጀባቸውም።

ዛሬም ቤተ ክርስቲያን፣ ከክርስቶስ የተሰጣትን መመሪያ ችላ ብላ የሰውን መመሪያ ስትከተል፣ ሳታውቀው እምባገነን በሆኑ መሪዎች እጅ ትወድቃለች። በዚህ ምክንያት የወንጌል ተልዕኮዋን እንደሚገባው መፈጸም ያቅታታል። እግዚአብሔር ገዢ በሆነበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ሁሉም እንደ ስጦታው ያገለግላል እንጂ አንድ ሰው ገደብ የሌለውን ዓይነት ሥልጣን ይዞ የፈቀደውን አያደርግም። ራሱን ከሌሎች የበለጠ አድርጎ የሚመለከት ስለሌለ፣ በመካከላቸው እውነተኛ ሕብረትና አንድነት ይታያል። የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት *ምሁር ጂ. ኤች. ላድ (G. H. Ladd)* በሐዋርያት ዘመን *አንድ ዓይነት የተወሰነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መዋቅር ስላልነበረ፥ የቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮት የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅርን አይጨምርም። መጽሐፍ ቅዱስ 'የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በዚህ ዓይነት መዋቅር ውስጥ መሆን አለበት' ስለማይል ማንኛውም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚስማማውን የራሱን የአስተዳደር መዋቅርና መመሪያ ማውጣት ይችላል"* ይላሉ።

በሐዋርያት ዘመን የምናያት የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን፣ ገና በማደግ ሂደት ላይ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያንን ነው። ስለዚህ የበለለች ወይም ያደገችው ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቷ ነች በማለት ሁሉም የሚስማማበት ወይም የሚደግፈው የቤተ ክርስቲያን አቋም አልነበረም። ቤተ ክርስቲያን እንደተቋቋመች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥልጣን በሐዋርያት እጅ ነበር። ሽማግሌዎች የተጠቀሱት በኋላ በኢየሩሳሌም ነው። *"መዋጮም አድርገው በበርናባስና በሳኦል እጅ ወደ ሽማግሌዎች ላኩ..." (የሐዋ. 11፥30)።* *"የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሾሙላቸው..."* (የሐዋ. 14፥23) ይላል። ቆየት ብሎ ደግሞ ከሐዋርያት መካከል ጴጥሮስና ዮሐንስ ራሳቸውን ሽማግሌዎች ብለው ሲጠሩ እናያለን (2 ዮሐ. 1፥- 3 ዮሐ. 1፥- 1 ጴጥ. 5፥1)።

# 5. ሌሎች የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ዓይነቶች

አብያተ ክርስቲያናት በዘመናት የተለያየ የአስተዳደር ሥልት ይከተሉ እንደነበረ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል። መጽሐፍ ቅዱስ "ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት

መመራት አለባት" የሚል መመሪያ በግልጽ ስለማይሰጥ፥ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የሚወደውን ዓይነት የአስተዳደር ሥልት ይከተል ነበር። ይሁን እንጂ፥ ትክክል ያልሆነ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በመከተላቸው ምክንያት በብዙ ችግር ውስጥ ያለፉ አብያተ ክርስቲያናት እንደነበሩ የታወቀ ነው። በ16ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ስቤተ ክርስቲያን ተሀድሶ ምክንያት የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፣ አንዳንድ የተበላሹ የአመራር ሥልቶቹን በግልጽ ጠቁመዋል። ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን የአስ ትዳደር ሥልት የራሱ የሆነ ብርታትም ሆነ ድካም ነበረው። ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ሥልጣን ያለው "መጋቢ-ሽማግሌ" (Pastor-Elder) ከሆነ፣ የተሰጠው ሥልጣን ምን ዓይነት ነው? ሥልጣኑ እስከምን ድረስ ነው? የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በማን እጅ መሆን አለበት? የሚል ጥያቄ በየጊዜው መነሳቱ አልቀረም። እርግጥ ነው ሙሉ ሥልጣኑ ያለው የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በክርስቶስ ላይ ነው። ይሁን እንጂ፤ ቁስ አካል በሆነው ዓለም ውስጥ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስተዳድር ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። በአሁኑ ጊዜ ጎልተው የሚታዩ ሦስት ዓይነት የቤተ ክርስቲያን የአመራር ወይም የአስተዳደር ስልቶች አሉ።

## 5.1. የጳጳስ አስተዳደር (Episcopalian)

በኤጲስ ቆጶስ የአስተዳደር ሥልት ውስጥ፣ ቤተ ክርስቲያንን እንዲመራ ወይም እንዲያስተዳድር ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ጳጳስ (ኤጲስ ቆጶስ) ነው። ይህን ዓይነት አመራር የሚከተሉ ቤተ እምነቶች እንግሊካን፤ (Anglican) ኤጲስ ኮፖሲያን (Episcopolina) ሜተዲስት (Methodist) የሮማ ካቶሊክና የግሪክ አርቶዶክስ ቤተ እምነቶች ናቸው። አንዳንድ ክፍሎች ይህን ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አመራር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈላጊውን ሥርዓት ለማስያዝ ይጠቅማል ብለው ይመኑ እንጂ ይህን ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አመራር በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ አናይም። ስሙ የመጣው "ኤጲስ ቆጶስ" (episkopos) ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን፤ ትርጉሙም "የበላይ ተቆጣጣሪ (overseer) ማለት ነው። ኤጲስ ኮፓል (episcopai) የሚለው ቃል "የእንግሊኡ ሳክስን" ቃል ሲሆን፣ የመጣውም "ኤፒስኮፖስ" (episcopus) ከሚለው የላቲን ቃል ነው።[16] ጳጳሳት፣ ሌሎች ጳጳሳትን፤ ካህናትንና (ፕሪስቢትረስ) ዲያቆናትን ይሾማሉ። በሮማ ካቶሊክ እምነትና ባህል ጳጳሳቱ ከሐዋርያት ዘመን ጀምር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣነው ይላሉ። ሉተር የሮማ ካቶሊክን እምነትና አሠራር በተቃወመበት ጊዜ ይህን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አመራርና አሠራር እንደ ነበራቸው ጠቅሷል። የሜቶዲስት ቤተ እምነት ግን "ጳጳስ" ይኑራቸው እንጂ፤ ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው ብለው አያምኑም። የኤፒስኮፖሊያንን አመራር የሚደግፉ ክፍሎች፣ የእምነት አቋማቸውን

---

[16] Ed Hayes, The Church, World Publishing, Nashville, TN 1999.



በሚመለከት ነጥብ ላይ ስመወያየት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኢየሩሳሌም በተሰበሰቡበት ወቅት፣ ያዕቆብ ስብሰባውን የመራ በመሆኑ፣ ያዕቆብ "የመሪዎች መሪ" ወይም "ጳጳስ" ነበር በማለት እንደ ምሳሌ አድርገው ይጠቅሱታሉ። በሐዋርያት ዘመን በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዳንድ ችግር ተፈጥረው ኢየሩሳሌም ውስጥ በተሰበሰቡበት ጊዜ ስብሰባውን የመራው ያዕቆብ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (የሐዋ. 15)። ጳውሎስም ያዕቆብን እንደ ቤተ ክርስቲያን ምሰሶ አድርጎ የሚመለከተው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በወቅቱ ያዕቆብ የነበረውን ሥልጣን የተቀበለው ይመስላል። *"ዋና መስለው የሚታዩት መሪዎች ያዕቆብና ጴጥሮስ፤ ዮሐንስም እግዚአብሔር ይህን ልዩ አገልግሎት እንደ ሰጠኝ በተረዱ ጊዜ..."* (ገላት. 2፥9) ይላል። በእርግጥ እየሩሳሌም በነበረችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያዕቆብ እንደ መሪዎች መሪ ሆኖ ይታይ ነበር። ይሁን እንጂ በካቶሊክ ቤተ እምነት ውስጥ ጳጳሱ ያለውን ዓይነት ሙሉ ሥልጣንና ኃይል አልነበረውም።

ይህን ዓይነት አስተዳደር የሚከተሉ፣ ጳጳሱን የሚያዩት እንደ ዋና መጋቢ (ፓስተር) አድርገው ነው። ከካህኑና (ከቄሱ) ከዲያቆናቱ ጋር፣ ሁሉም የራሱን ኃላፊነትና አገልግሎቱን እንደያዘ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ይጠብቃሉ። ኃላፊነታቸውም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መሾም፣ የአዳዲስ የቤተ ክርስቲያናት የምረቃ ሥነ ሥርዓት መፈጸም ነው። ከተሃድሶ በኋላ "ጳጳስ" የሚለውን የሹመት ማዕረግ ዴንማርክ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን፣ ፊንላንድና ሮማንያ ያሉት ሉተራውያን አብያተ ክርስቲያናት ይጠቀሙበት ነበር። ይሁን እንጂ፤ ሁሉም ሹመቱ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው አይሉም። "የኤፒስኮፖሲያን" ከሌሎች ቤተ እምነቶች ተለይተው የሚታወቁበት ዋና አቋማቸው፣ "የጳጳሳት ሥልጣን ርክክቦሽ" (Succession of bishops) ነው። ይህን ዓይነቱ አሳብ ግን አዲስ ኪዳን ውስጥ የትም ቦታ ተጠቅሶ አናነብም። ሉተርም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ዓይነቱን አመራር በኃይል የተቃወመ መሆኑ ይታወቃል። ኤፒስኮፖሲያን የአማኞችን ካህንነት ወይም አገልጋይነት አይቀበልም። ይኼም አንደኛውና ትልቁ ድካሙ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"..የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ምእመናንን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት ነው..."* (ኤፌ. 4፥12) ቢልም፣ እያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳለውና በአገልግሎት መሳተፍ እንደሚችል አያምኑም።

"መጋቢ፤ ሽማግሌ፣ ጳጳስ" –እነዚህ ስሞች አንድ ዓይነት እንደሆኑ፣ እንዲሁም ተመሳሳይ የሆነ ሥልጣን እንዳላቸው የሥነ መለኮት ምሁራን ይጠቁማሉ። ይህ እውነት ከሆነ፣ "በጳጳስ" የሚመራ የተለየ አስተዳደር ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። በደረጃ የተከፋፈለ የሥልጣን መዋቅር በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልነበረም። ይህን ዓይነቱን አስተዳደር የሚደግፉ ቤተ እምነቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሱት ቃል ምን ይሆን? አንደኛው፤ 1 ተሰሎ. 5፥12-13 ላይ ያለው፤ *"ወንድሞች ሆይ! በእናንተ መካከል በሥራ የሚደክሙትን በጌታ ኢየሱስ አለቆቻችሁንና መካሪዎ*

*ቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሩአቸው እንለምናችኋለን፥ በሥራቸው ምክንያትም ለእነርሱ ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ይኑራችሁ…"* የሚለውን ነው። ሁለተኛ፣ 3 ዮሐ. ቁ. 9 ላይ ያለው፤ *"…ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የሚፈልገው ዲዮትራፊስ ሐሳቤን አልተቀበለም"* የሚለው ነው። ሦስተኛው ዕብ. 13፥17 ላይ ያለው *"ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ በሥልጣናቸውም ሥር ሁኑ፥ ምክንያቱም እነርሱ የሚጠየቁበት ኃላፊነት ስላለባቸው ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ፥ እናንተ ብትታዘዙአቸው፤ እነርሱ ሥራቸውን በደስታ ያከናውናሉ፥ ያለበለዚያ ሥራቸውን በሐዘን ይሠራሉ፥ ይህም እናንተን የሚጠቅም አይሆንም"* የሚለው ነው። እነዚህን ጥቅሶች መሠረት በማድረግ የሚደመድሙት፤

*(1) በተራ ምዕመናንና በካህናት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዳለ፤*

*(2) ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ የሆነ የአስተዳደር መዋቅር እንደሆነ፤*

*(3) የጳጳስነት ሥልጣኑን የያዘው ሰው በዚህ ሥልጣን ላይ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ እንደሚቆይ ነው።*

ይህንንም የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በመጥቀስ ነው። የኤጲስ ቆጶሱ ሥልጣን እንደ፤ በሐዋርያት የተመሠረተ ስለ ሆነ ሥልጣኑ እስከ መጨረሻው መቀጠል አለበት ይላሉ። እርግጥ ነው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመምራት ሥልጣን አላቸው፤ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን መዕመናን መሪዎቻቸውን መደገፍ አለባቸው። ይሁን እንጂ በካህናቱና በምዕመናኑ መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊነቱን አያሳይም።

## 5.2. በሽማግሌዎች የሚመራ አስተዳደር፤ (Presbyterianism)

ሁለተኛው ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በሽማግሌዎች "ፕሪስቢተርስ" (Presbyters) የሚመራው ነው። "ሽማግሌ" የሚለው ቃል የመጣው፣ "ፕሬስቢትሮስ" (presbyteros) ከሚለው የግሪክ ቃል ነው። በአሁኑ ዘመን "ፕሬስቢቴሪያን" እየተባለ የሚጠራው ቤተ እምነት፣ አመራሩ በአራት ደረጃ የተከፋፈለ አካል (hierarchy) አለው። ይኸውም—ስብሰባ (session)፥ ፕሬስቢትሪ (presbytery)፥ ሲኖድ (synod)፥ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤ (general assembly) በማለት ይታወቃሉ። "ስብሰባ" ሲል፣ ካህናትና ክህነትነት የሌላቸው፣ ሕዝቡን የሚወክሉና በሕዝብ የተመረጡ ሽማግሌዎችን ያጠቃልላል። "ፕሬስቢትሪ" ደግሞ ካህናትን፣ የሽማግሌዎች ተወካዮችንና ሕዝቡን ያጠቃልላል። "ሲኖድ" ደግሞ በሌሎች አጥቢያ ውስጥ ያሉትን ሽማግሌዎችንና ተወካዮችን ያጠቃልላል። "አጠቃላይ ጉባኤ" በዚህ ጉባኤ ላይ እንዲገኙ ከየአጥቢያው የተመረጡ ሰዎች በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰቡበት፣ አጠቃላይ ቤት እምነቱን የሚመለከት ውሳኔ



ሰጪዎች ናቸው። በሽማግሌዎች መመራት የሚለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ በጆን ካልቪን የተጀመረ ሲሆን፣ እርሱም የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ መዋቅር ላይ የተመሠረተ ነው። ጆን ካልቪን፣ መጋቢዎች (ፓስተሮች)፣ ሽማግሌዎች፣ አስተማሪዎችና ዲያቆናት በማለት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በአራት ክፍል ይከፍለዋል። ለዚህም የሚጠቅሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፣ ሮሜ 12፥8፥- 1 ቆሮ. 12፥28፥- 1 ጢሞ. 5፥17 ናቸው። የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ቢኖርም፣ የአገሪቱ "መሪ ሃይማኖት" (State Religion) የሆነበት፣ ስኮትላንድ ብቻ ነው። በአሜሪካ ውስጥ የፕሬስቤቴሪያን ቤተ ክርስትያናት በእምነትም ሆነ በአመራር እርስ በርሳቸው የተለያዩ ናቸው። የፕሬስቢተርያንን ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን የሚደግፉ፣ ያለውን ሥርዓት፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የሚኖረውን የተወሰነ ሥልጣን፣ አገልጋዮች (ካህናት) ሊኖራቸው የሚገባ ከፍተኛ ብቃት ይጠቅሳሉ። አገልጋዮች (ካህናት) የሚመረጡት በምዕመናን ሲሆን፥ ድካም ወይም ጉድለት ሲታይባቸውም የሚገስጹት እንደ ማንኛውም ምዕመን፣ በምዕመናን ጉባኤ ነው። የክህነት ማዕረግ የተሰጣቸው፣ በሙሉ ጊዜ አገልግሎታቸውን መፈጸም ይችላሉ። እንደ ማንኛውም ተራ ምዕመን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የሚገሰጹት በምዕመናኑ ነው። ይሁን እንጂ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በአማኞች እጅ መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም መጥቀስ አይችሉም።

አንድ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ፣ በሌላው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናይም። በሐዋርያት ዘመን በኢየሩሳሌም ሽማግሌዎችና ዲያቆናት አጠቃላይ ስብሰባ ያድርጉ እንጂ ያንን የመሰለ ስብሰባ በሌላ ጊዜ ተደርጎ አናይም። "የእምነት አንድነታቸው" በተናጋበት ወቅት፣ ሁኔታውን መስመር ለማስያዝ እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የራሱን ሽማግሌና ዲያቆን መርጦ በእምነታቸው ጥያቄ የፈጠረባቸውን ነገር ያስፈቱበትን ደብዳቤያቸውን አስይዘው፣ ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ ስብሰባው እንዲሄዱ እንዳደረጉ እናውቃለን (የሐዋ. 15፥22)። በዚያን ወቅት ሐዋርያት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ሥልጣን ይኑራቸው እንጂ ሽማግሌዎች ከራሳቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ልዩ የሆነ ሥልጣን ኖሯቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ አናነብም። ሽማግሌዎች እንደ ሥጦታቸው ይኸውም፣ "የሚያስተምሩና የሚያስተዳድሩ" በማለት በሁለት ክፍል ይከፍሏቸዋል። *"ቤተ ክርስቲያንን በደንብ የሚያስተዳድሩ፤ ይልቁንም የሥራቸን ቃል በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር ይገባቸዋል"* (1 ጢሞ. 5፥17) ይላል። የሚያስተምረው ሽማግሌ "መጋቢው" (ፓስተሩ) ነው። የሚያስተዳድሩት ደግሞ የተቀሩት ሽማግሌዎች ናቸው። "መጋቢ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደር ውስጥ መግባት የለበትም" ይላሉ። ይህን ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን አመራር የሚከተሉ "ፕሬስቢቴርያን" የተባለው "ቤት እምነት" ነው። ሽማግሌዎች እንደ ዲያቆናቱ የሚመረጡት ከምዕ

መናኑ መካከል ነው። እንደ ጆን ካልቨን አባባል ከሆነ፣ አስተማሪ የሆኑት ሽማግሌዎች ግን ከእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው መሆን አለባቸው ማለታቸው ነው። የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ግን ጥሪም ሆነ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የማያስፈልጋቸው መሆናቸውን ያምናሉ።

እንዲህ ዓይነቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የራሱ የሆነ ችግር አለበት። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የብቁነታቸው ዝርዝር መግለጫ የተሰጠው የሁለቱ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣኖች ብቻ ነው። ይኸውም *"የመጋቢ-የሽማግሌ-የጳጳስ"* ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ *"የዲያቆን"* ብቻ ነው። በሽማግሌዎች መካከል ልዩነት እንዳለ፥ ይኸውም አንደኛው ክፍል እንዲያስተምር፣ ሌላው ክፍል ደግሞ እንዳያስተምር የሚል አሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በጻፋቸው መልዕክቶቹ ውስጥ ሽማግሌ የሚሆኑት "ለማስተማር ብቃት ያላቸው፣" መንጋውን ከሀሰተኛ አስተማሪዎች መጠበቅ ወይም መከላከል የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው ገልጿል። *"በደንብ የሚያስተዳድሩ"* እንዲሁም *"በማስተማር የሚደክሙ"* ሲል፣ ሁለት የተለያዩ ክፍሎችን መጥቀሱ አይደለም። ሽማግሌዎች ሁሉ ያስተዳድራሉ፤ እንዲሁም ሽማግሌዎች ሁሉ ያስተምራሉ። ይሁን እንጂ ሁሉም "በደንብ አያስተዳድሩም" እንዲሁም "ሁሉም በማስተማር አይደክሙም።" ይህንን ሀሳብ የሚደግፍ በ1ኛ ተሰሎ. 5፥17 ላይ ተጠቅሷል–***"ወንድሞች ሆይ በእናንተ መካከል በሥራ የሚደክሙትን በጌታ ኢየሱስ አለቆቻችሁንና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እንድታከብሩአቸው እንለምናችኋለን"*** ይላል። በመሠረቱ ቃሉን በማስተማር የሚደክመው "መጋቢ-ሽማግሌው" ስለሆነ፣ የበለጠ ክብር የሚገባው እርሱ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል።

በሽማግሌዎች የሚመራ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ የሚያስተዳድሩና የሚያስተምሩ ሽማግሌዎች ሁለቱም ወገን እኩል መሆን አለባቸው የሚሉ አሉ። በፕሬስቢቴሪያን አካባቢ ለረጅም ጊዜ በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ክርክርና ጭቅጭቅ አስነስቷል። ሽማግሌዎችን ሁሉ "ጳጳስ፣ መጋቢ፣ አስተማሪና አስተዳዳሪ" ተብለው መጠራታቸውን የሚቃወሙ አሉ። ሽማግሌዎችን በሁለት በመከፈል ፈንታ እንደ አንድ ክፍል ካየናቸው፣ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ለመስበክ፣ ለማስተማር፣ ሥልጣን ይኖራቸዋል። ይህን አይነቱ አሠራር ጥንት ከነበረው ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጪ ያደርገናል ብለው የሚቃወሙ ክፍሎች አሉ። ይህንን አሳብ የሚቃወሙት፣ የሚያስተዳድረው ሽማግሌ ተራ ምዕመን ወንጌልን ለመስበክ የተጠራ አይደለም ይላሉ። በዚህ ችግር ምክንያት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዱ ሽማግሌ ከሌላው ሽማግሌ የሚበልጥ ሥልጣን የሚኖረው አይሆንም ብለው ይደመድማሉ።

በአገልግሎት ውስጥ የተሳካ ውጤት ለማምጣት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ይጠይቃል? ሰው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ባይኖረውም፣ ከእግዚአብሔር በተቀበለው የተፈጥሮ



ችሎታው ማገልገል አይችልም? ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው፤ *"...የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ፈጽም..."* ይላዋል (2 ጢሞ.4፥5)። ጢሞቴዎስ ወንጌላዊም ባይሆን፣ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ እንዲፈጽም መንፈሳዊ አባቱ ሲመክረው እናያለን። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና የተፈጥሮ ችሎታ ልዩነታቸው ምንድነው? እርግጥ ነው፣ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሥራት የሚቻለው፣ በተፈጥሮ ችሎታ ላይሠራ ይችላል። የማስተማር ስጦታ ከእረኛነት ሥጦታ ጋር የተያያዘ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል (ኤፌ. 4፥11፣- 1 ጢሞ. 3፥2፣- ቲቶ 1፥9)። የማስተማር ስጦታ ስመሆኑ ምንድነው? ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን ሕያው ቃል (የእግዚአብሔር ቃል) መለኮታዊ የሆነ መረዳት አግኝቶ፣ ለሌሎችን ማስተማር መቻል ነው። "የማስተማር ስጦታ" ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ዕውቀት ማግኘት ማለት ሳይሆን፣ ቃሉን እንደሚገባው ተረድቶ ሌሎችን ማስተማር የሚያበቃ ችሎታን ማግኘት ነው።

## 5.3. በምዕመናን ጉባኤ (Congregationalism) የሚመራ አስተዳደር

*"ኮንግሪጌሽናሊዝም"* ማንኛውም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ሥልጣን ኖሮት፣ የውጪ ተጽዕኖ ሳይኖርበት፣ በራሱ መሪዎች የሚመራ የአመራር ሥልት ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ሁሉ አማኞች ከሆኑ፣ "እንደ እግዚአብሔር ካህን" ይታያሉ። ይህን ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን አመራር የሚቀበሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ራሥ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ፣ በአስተዳደሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ዲሞክራቲካዊ በሆነ መንገድ ተሳታፊነት አላቸው ይላሉ። በምዕመናን የሚመራ አስተዳደር ማለት ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር ሙሉ ሥልጣኑን የያዘው የምዕመናን ጉባኤ ነው ማለት ነው። ይሄ ሥልጣን የመጣው የአካሉ ራሥ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ፣ መላው አካል መጽሐፍ ቅዱስ በሚያዘው ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድራል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሁለት ዓይነት ሥልጣን ብቻ አለ። ይኸውም አንደኛው ክፍል፣- መጋቢዎች (ሽማግሌዎች) ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ክፍል ዲያቆናት ናቸው። መጋቢ ሆኖ ለመሾም ከእግዚአብሔር ጥሪ ማግኘት እንጂ የጸጋ ስጦታዎች አያስፈልጉትም። "የምዕመናን ጉባኤ" ማለት፤ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን ችሎ የሚተዳደር (autonomous) ነው። ለሚያስተላልፈው ውሳኔ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነው ከክርስቶስ በቀር ሌላ የሚቆጣጠረው ባለ ሥልጣን የለም። ይህም ማለት ለሚደረጉት ውሳኔዎች ሁሉ የጉባኤው አባላት በሙሉ መሰብሰብ አለባቸው ማለት አይደለም። ውሳኔ እንዲያስተላልፉ ሥልጣን ወይም ውክልና የሚሰጣቸው መሪዎች ይኖራሉ። ምርጫ በሚደረግበት ወቅት አባሉም ሆነ መጋቢው (ጋብቱሩ) እኩል ድምጽ ይኖራቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር፣ አማኞችን ማገልገል፣ የቤተ ክርስቲያን ራሥ የሆነውን ክርስቶስ መታዘዝ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትሰጣቸው አገልግሎቶች ናቸው። አጠቃ

ላይ መሠረታዊ ደንቦችን ሳይለቅ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉት አገልግሎቶችና አገልጋዮች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን አሳብ መረዳት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያን የቆመችው ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይደለም። መሪዎች የቆሙት ግን የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ ለመፈጸም ነው። ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷ ሁለት ክፍል ያለው ነው። አንደኛው፥ ውስጥ ያሉትን አማኞች ማገልገል ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ ዓለም ውስጥ ያሉትን በወንጌል ለመድረስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት የአገልግሎት ቢሮዎች (ሥጦታዎች) ይኸውም፥ ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች፣ እንዲሁም ዲያቆናት (ኤፌ. 4፥11፥ የሐዋ. 6፥3) መኖራቸው ቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዳላት ያሳያል። ዲያቆን የነበሩትን ፊሊጶስንና እስጢፋኖስን እንደ ምሳሌ አድርገን ብንወስዳቸው፣ አገልግሎታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ የወንጌል ሰበካ አገልግሎትን ጭምር ይሰጡ እንደ ነበር መረዳት እንችላለን። እነዚህ የአገልግሎት ስጦታዎች ለአማኞች ለምን እንደሚሰጡ ሲገልጽ፣ *"...የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ ይህም የሚሆነው ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወደሆነው ፍጹምነት ደረጃ እስክንደርስ ነው"* ይላል (ኤፌ. 4፥12-13)።

ምዕራፍ ፬

# መንፈሳዊ ጤንነት

"ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ እኔ ራሴ ውድቅ ሆኜ እንዳልቀር፣ ሰውነቴን እየጎሰምሁ እንዲገዛልኝ አደርገዋለሁ" (2 ቆሮ. 9፥27)።

"ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ..." (የሐዋ. 6፥3)።

መጽሐፍ ቅዱስን ገለጥ አድርገን ስናነብ፣ በተለይ የአንዳንድ የመንፈሳዊ መሪዎችን የሕይወት ታሪክ ስናጠና፣ መንፈሳዊ ትግል ያለብን እኛ ብቻ እንዳልሆንን እንገነዘባለን። ታሪካቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ከሰው የተለየ ልዩ ኃይል ያላቸው ባይሆኑም፣ እግዚአብሔር ከነድካማቸው ለዓላማው እንደተጠቀመባቸው እንረዳለን። እኛ ያለንን ዓይነት ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ያላቸው በመሆናቸው፣ ልክ በአሁኑ ጊዜ እንዳሉት መንፈሳዊ መሪዎች በተለያየ ኃጢአት ተሸንፈው ሲወድቁ እናያቸዋለን። አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሁራን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያንን ከሚያዳክሟት ምክንያቶች ማከከል አንደኛውና ትልቁ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ *"ደቀ መዝሙርነት የጠፋ በመሆኑ ነው"* ይላሉ። እንደ ምሁራን ገለጻ *"ደቀ መዝሙርነት" ሁሉን ነገር ትቶ ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ መከተል ማለት ነው።* ደቀ መዝሙርነት የጠፋው ከተራው ምዕመን ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ ሕዝቡን በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲያሳድጉ ኃላፊነት በተሰጣቸው መንፈሳዊ መሪዎችም መካከል ነው። የሕዝቡን መንፈሳዊ ረሀብ አይተው እንደሚገባው በመመገብ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔ

ርን ፈቃድ በማስቀደም ፈንታ የራሳቸውን ፈቃድና ፍላጎት ለመፈጸም ሲሯሯጡ ማየት ለብዙዎቻችን አዲስ ነገር አይደለም። የመሪዎችን ጽኑ የሆነ መንፈሳዊ አቋም ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ብዙዎቹ የተገነዘቡት አይመስሉም። መንፈሳዊ መሪዎች ያሉበት የክርስትና ሕይወት፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ ሁልጊዜ ራሳቸውን በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥጋ የለበሱ ሰዎች በመሆናቸው፣ እንደማንኛውም ሰው የራሳቸው የሆነ ድካም፣ እንዲሁም የራሳቸው የሆነ ልዩ ልዩ ፈተና አለባቸው። ብርቱ ሆነው የሚታዩበት ጊዜ አለ፤ ደካማ ሆነው የሚታዩበትም ጊዜ አለ። አስተዋይ የሚሆኑበት ጊዜ አለ፤ ሁልጊዜ ግን አያስተውሉም። ደፋር ሆነው የሚገኙበት ጊዜ አለ፤ ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ደፋሮች አይደሉም። ደስተኞች የሚሆኑበት ጊዜ አለ፤ ሁልጊዜ ግን ደስተኞች አይደሉም። በሰላም የተሞሉ ናቸው፤ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ እንደማንኛውም ሰው በአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ የሚያልፉበት ጊዜ አለ። በግል ሕይወታቸው ውስጥ በሚያጋጥማቸው ፈተና፣ በአገልግሎታቸው ውስጥ በሚሰማቸው ከፍተኛ ውጥረት (ግፊት)፣ እንዲሁም የሚያገለግሉትን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት ከአነርሱ አቅም በላይ ሲሆንባቸው፣ በአገልግሎት ውስጥ ያለውን እውነተኛ ደስታ እንደሚያጡ ግልጽ ነው። በዓለማዊ ድርጅት ውስጥ ያሉ መሪዎች በኃላፊነት ሥራቸው ፍሬያማ እንዲሆኑ፣ በአመራራቸው ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ውጥረት ማርገብ እንዲችሉ፣ ደካማ ሆነው በተገኙበት አቅጣጫ እገዛ ሊያደርጉላቸው የሚችሉ ልዩ ልዩ መንገዶችን ይፈለግላቸዋል። ይኸውም፣ የሥነ ልቦና ምክር የሚያገኙበትና፣ የአስተዳደር ምሁራን ካዘጋጁት ሴሚናር ተካፋይ የሚሆኑበት መንገድ ይመቻችላቸዋል።

## 1. መንፈሳዊ መሪዎች የግል ሕይወታቸውን መመርመር አለባቸው

*"አሁን የምሠራውን ሥራ ለመሥራት የተነሳሁበት ዋና ምክንያት ምንድነው? በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውስጥ ገብቼ የማገለግልበት ዋናው ምክንያቴ ምንድነው? ሌላ ሥራ ማግኘት ስለማልችል ለራሴ ሥራ መፍጠሬ ነው? የምሠራው ሥራ ከሌላው ዓይነት ሥራ ቀላል ሆኖ ስላገኘሁት ነው? ብዙ ሳልለፋና ሳልደክም ብዙ ገንዘብ፣ ታዋቂነትና ክብር ስለሚያስገኝልኝ ነው?"* በማለት እውነተኛውን ምክንያታቸውን ለማወቅ ራሳቸውን ጠይቀው መረዳት አለባቸው። መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ለነዚህ ጥያቄዎች ለራሳቸውም ሆነ ለሚያገለግሏቸው ሰዎች እውነተኞች ሆነው ትክክለኛውን መልስ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። መልስ ሳይሰጡባቸው ችላ ብለው፣ ወደ ጎን ገፍተው ሊተዉአቸው የሚገቡ ጥያቄዎች አይደሉም። ወደ አገልግሎት የገቡበት ምክንያት ትክክል ካልሆነ፣ እንዲያገለግሉት ኃላፊነት የተሰጣቸውን ሕዝብ ደስ ብሏቸው እንደሚገባው ማገልገል አለመቻላ



ቸው ብቻ ሳይሆን፣ ራሳቸውንም በከንቱ ያደክማሉ። በአገልግሎት ውስጥ ትግልና መከራ ሲያጋጥማቸው፣ "በዚህ ዓለም ትግል ቢበዛብኝም ግዴለም! ትርፌ ከላይ ነው" በማለት እንዳይጽናኑ፣ እግዚአብሔር ጠርቶ የላካቸው ስላልሆኑ፣ መጨረሻ ላይ ከፊቱ ሲቀርቡ የሚቀበሉት ደሞዝ ወይም ሽልማት እንደማይኖራቸው ማወቅ አለባቸው። *"ተጠርቼ ወደ አገልግሎት የመጣሁ ስላልሆንኩ፣ መጨረሻ ላይ በሰጠሁት አገልግሎት ሽልማት ባላገኝበትም ግድ የለም፣ ሥራው ከባድ ስላልሆነ፣ ለምድራዊ ኑሮዬ ጠቅሞኛል (ተስማምቶኛል)"* የሚሉ ከሆነ እንደማንኛውም የዕለት ሥራ መሥራት ይችላሉ። ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነው የሚያገለግሉ፣ ሁሉም እውነተኛ ጥሪ ኖሯቸው የመጡ ሳይሆኑ፣ በአንዳንድ አጋጣሚ ምክንያት ሥፍራውን ያገኙ ስለሆኑ፣ በአገልግሎታቸው ይህን ያህል አጥጋቢ የሆነ ፍሬ ባይታይባቸው ሲደንቀን አይገባም።

እኔና እናንተ በሕይወታችን የወሰንናቸው ትላልቅም ሆኑ ትናንሽ ውሳኔዎች፣ ሁሉም የራሳቸው ምክንያት አላቸው። የተወለድንበትንና ያደግንበትን አገር ጥለን፣ ዘመዶቻችንና ወዳጆቻችንን ትተን ሰው አገር መኖር የመረጥነው እንዲሁ ሳይሆን፣ ምክንያት ኖሮን ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪ፣ ወደ አገልግሎት ለምን እንደመጣ ብቻ ሳይሆን፣ በተሰለፈበት አገልግሎት ውስጥ በኃይል እንዲሠራ የሚቀሰቅሰው ምክንያት ምን እንደሆነ ራሱን መጠየቅና መመርመር አለበት። በሙሉ ጊዜ ማገልገል የመረጠው *"ብዙ ገንዘብ...የተመቻቸ ኑሮ...ዝናና ክብር አገኝበታለሁ..."* በማለት ይሆን? በሥራው ከፍተኛ ትጋት የሚያሳየው፣ በሚያደርገው ነገር ሁሉ መቅደም፣ አንደኛ መሆን፣ ከሌሎች ሁሉ ተሽሎ ለመገኘት ነው? "ታዋቂ አገልጋይ" በመባል እንዲታወቅ ነው? ምክንያቶቹ ከላይ የገለጽናቸው ከሆኑ፣ ትክክለኛ ዓላማ ያለው፣ በአገልግሎቱ የእግዚአብሔር ልብ ደስ የሚሰኝበት ሰው እንዳልሆነ እንገነዘባለን። የአገልግሎቱ ዋና ምክንያት ገንዘብ፣ የማዕረግ ስም፣ ዝናና ታዋቂነትን ለማግኘት፣ በሌሎች ዓይን ትልቅ ሆኖ ለመታየት ከሆነ፣ ልቡ ያረፈው በአገልግሎት ላይ ሳይሆን በሚያገኘው ጥቅም ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ እየኖረ ስለሆነ፣ እውነተኛ የሆነ የሕይወት ለውጥ ያስፈልገዋል። ክብርና ዝናን የተጠሙ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ትኩረት የሚያደርጉት ፍላጎታቸው የሚሟላበትን መንገድ እንጂ የሚያገለግሏቸው ሰዎች መንፈሳዊ ጉስቁልና ላይ አይደለም። እንዲህ ዓይነቶቹ መንፈሳዊ መሪዎች የሚሰጡት አገልግሎትም ሆነ የሚወስዱት ውሳኔ ርህራሄና ፍቅር የጎደለው ሆኖ ብናገኘው ሲደንቀን አይገባም። እግዚአብሔር በመሪነት ሥፍራ ያስቀመጣቸው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያገለግሉ እንጂ ሥልጣናቸውን በመጠቀም በአደራ የተሰጣቸውን ሕዝብ እንዲያስጨንቁ አይደለም።

"በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሽኩቻዎች፣ ትግሎች የሚካሄዱበት ምክንያት ምን ይሆን?" በማለት ብዙዎች ይጠይቃሉ። ለትግሉና ለሽኩቻው አንደኛውና ትልቁ ምክንያት፣ በተወሰኑ ሰዎች መካከል የሚታይ የቦታ ወይም የሥልጣን ትግል ነው። ብዙዎች ከመጠን በላይ ላይና ታች የሚሉት የጌታ ፍቅር እንገብግቧቸው፣ "ለጌታ

ምን ልሥራለት?" ብለው አይደለም። የነፍሳት መጥፋት ቆርቁሯቸው፣ "የጠፉትን ልመልስ" ብለው እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይሄ ካልሆነ፣ እውነተኛው ምክንያታቸው ምንድ ነው? ድብቅ የሆነ ምክንያት ወይም ዓላማ ይኖራቸው ይሆን? ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲለፉ፣ በአገልግሎት ውስጥ ላይና ታች ሲሉ የሚታዩት፣ ያን ሁሉ ድካም ለምን እንደሚደክሙ እውነተኛውን ምክንያታቸውን ማወቅ የሚችል ሥጋ የለበሰ ሰው ይኖር ይሆን? ኤርምያስ የሰውን ልብ ማወቅ እንደማይቻል ሲገልጽ፣ *"የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነው፤ ፈውስም የለውም፤ ማንስ ሊረዳው ይችላል?"* አለ (ኤርም. 17፥9)። የልባችንን እውነተኛ አቋም ማወቅ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ስለ መንፈሳዊ መሪዎች ትክክል ያልሆነ አመለካከት ያላቸው አንዳንድ የዋህ ሰዎች ጥንት ብቻ ሳይሆን፣ በዘመናችንም አሉ። መድረክ ላይ ሆነው ሲሰብኩ፣ እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ጭነው ሲጸልዩ የሚያዩዋቸው ሰዎች፣ ከራሳቸው የመነጨ ልዩ የሆነ ኃይል ያላቸው ሰዎች አድርገው የሚመለከቷቸው እንዳሉ እርግጠኞች ነን። በጸሎትና በመመሰጥ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ የሆነ የተቀራረበ ግንኙነት ያላቸው፣ በመለኮታዊ ቅባት የተቀቡ፣ ለመለአክት ብቻ የሚሰጠው ልዩ ኃይል ለእነርሱ እንደተሰጣቸው አድርገው የሚመለከቷቸው አሉ። ጳውሎስና በርናባስ በበልስጥራና በደርቤ ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ በእግሩ ሄዶ የማያውቀውን አንድ ሽባ ሰው ጳውሎስ "ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!" ሲለው ተነስቶ ሲራመድ ያዩት ሰዎች በመደነቅ በሊቃኦንያ ቋንቋ *"አማልክት በሰው ተመስለው ወደ እኛ ወርደዋል!"* በማለት ሊሰግዱላቸው እንደፈለጉ እናስታውሳለን። ጳውሎስና በርናባስ ግን ያለአግባብ የተለጣቸውን ክብር በመቀበል ፈንታ ልብሳቸውን ቀድደው፣ *"እናንተ ሰዎች፤ ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? እኛም እኮ እንደ እናንተው ሰዎች ነን"* አሏቸው (ሐዋ. 14፥15)። እነዚህ "አገልጋይ አድናቂዎች"፣ ጳውሎስንና በርናባስን ከሰማይ የወረዱ አማልክት አድርገው በመመልከት ፈንታ ቀረብ ብለው ቢያዩዋቸው፣ እንደ ማንኛውም ሥጋ ለባሽ ሰው የራሳቸው የሆነ ድካም ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን ይረዱ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ታላቅ የጌታ አገልጋይ ቢሆንም፣ ያለው ችሎታም ሆነ ብቃት ከራሱ የመጣ እንዳልሆነ አልሸሸገም።

"ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በራሳችን ብቃት ከእኛ የምንለው አንዳች ነገር የለንም" ይላል (2 ቆሮ. 3፥5)።

ማንኛውም አገልጋይ በራሱ ድካም የተሞላ፣ እንደማንኛውም ሰው የመውደቅ ዝንባሌ ያለው ሰው መሆኑን ምን ጊዜም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። መንፈሳዊ መሪ በየቀኑ እንደማንኛውም ሰው ችግሮች፣ ልዩ ልዩ ትግሎችና ፈተናዎች ያጋጥሙታል። ጳውሎስ እነዚህን ሁኔታዎች ሲገልጽ፥

"በየአቅጣጫው ብንገፋም አንንኮታኮትም፤ ግራ ብንጋባም ተስፋ አንቆርጥም፤ ብንሰደድም ተጥለን አንቀርም፤ መትተው ቢጥሉንም አንጠፋም" ይላል (2 ቆሮ. 4፥8-9)።



መንፈሳዊ መሪዎች ግፊት፣ ስደት፣ ግራ መጋባት እንደ ማንኛውም ሰው ይደርስባቸዋል። ስሌሎች አይምሰል እንጂ ሥጋና ደም የለበሱ ደካማ ሰዎችም ናቸው። ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲገልጽ፥

"የኢየሱስ ሕይወት በሰውነታችን እንዲገለጥ፥ የኢየሱስን ሞት ዘወትር በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን። የኢየሱስ ሕይወት ሟች በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ፣ እኛ ሕያዋን የሆንን ሁልጊዜ ስለ ኢየሱስ ለሞት ዐልፈን እንሰጣለንና" ይላል (2 ቆሮ. 4፥10-11)።

መንፈሳዊ መሪዎች እንደማንኛውም ሰው የሚታመም፣ የሚያረጅና የሚሞት አካል ያላቸው ስለሆኑ፣ ሁልጊዜ ለአደጋ የተጋለጡ መሆናቸው የማያጠራጥር እውነት ነው። በሕይወታቸው የሚደርስባቸው ግጭቶችና ግፊቶች ሁሉም በግልጽ የሚታዩ አይደሉም። ስውር የሆነ ባህሪ ያላቸው፣ ውስጥ ውስጡን እያኰመው የሚጥሉ ናቸው። ሥጋ ለባሽ ሰዎች በመሆናቸው፣ በየጊዜው ለሚገጥሟቸው ግፊቶችና ፈተናዎች "እሺ!" ብለው እጃቸውን የመስጠት ዝንባሌ አላቸው። መንፈሳዊ መሪዎች በእነዚህ ግፊቶችና ፈተናዎች ተሰናክለው ወጥመድ ውስጥ መግባት ይችላሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ መሪዎችን ከውድቀት ራሳቸውን ለመጠበቅ፣ ሁልጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ራሳቸውን በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው።

## 2. መንፈሳዊ መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ መሆን አለባቸው

መንፈሳዊ መሪዎች፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን አደራ እንደሚገባው መፈጸም እንዲችሉ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያስፈልጋቸዋል። በተፈጥሮው የመሪነት ችሎታ ቢኖራቸው እንኳን ያለመንፈስ ቅዱስ ሙላት፣ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ መሆን አይችሉም። በሐዋርያት ዘመን በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማንኛውም አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው አማኞች ሁሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል። በአንድ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶች ችላ በመባላቸው ምክንያት በአማኞች ዘንድ ማጉረምረም ስለ ተፈጠረ፣ ያንን ችግር ለማቃለል ሐዋርያት አማኞቹን ሰብስበው ዲያቆናትን መርጠው እንዲያቀርቡ አዘዟቸው። ምን ዓይነት ሰዎች መምረጥ እንዳለባቸው የሰጧቸው መመሪያ፣ *"በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉትን"* የሚል ነበር። መርጠው በሐዋርያት ፊት ያቀረቧቸው ሰዎች፣ እነርሱ ራሳቸው *"በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል"* ያሉትን ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው በሌሎች *"የተመሰከረላቸውን"* ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞሉ፣ ብሩህ አዕምሮ፣ የማስተዳደር ችሎታ፣ ጥሩ ዕቅድ አውጪዎች፣ ተናግረው የማሳመን ችሎታ ያላቸው፣ በብዙ ሕዝብ ዘንድ መታወቃቸው፣ የሞራል ሰዎች፣ "ሀቀኛ አቋም" የሚታይባቸው መሆናቸው ብቻ ለመንፈሳዊ መሪነት ብቁ አያደርጋቸውም። የሚሰጣቸው ኃላፊነት (ሥራ) መንፈሳዊ ባሕሪ ያለው በመሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ሥጋዊ ለሆኑ

ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመሩ በምንም ዓይነት ኃላፊ አድርጎ ስለማይሾም (ስለማይመርጥ)፣ መንፈሳዊ መሪዎች የግድ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ መሆን አለባቸው። ከዚህ ውጪ መሪዎቻቸውን የሚለኩበት ሌላ መለኪያ ሲያበጁ፣ መንፈስ ቅዱስን ከቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ማስወጣታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛውን ሥፍራ መከልከላቸው ነው።

በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፣ ሐዋርያት በሰጡት መመሪያ መሠረት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰባት ሰዎች መርጠው በሐዋርያት እግር ፊት አቀረቧቸው። ሐዋርያትም ጸልየው እጆቻቸውን ጫኑባቸው። አገልጋዮቹ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ስለነበሩ፣ የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት መስጠት ቻለች። "ማዕድ ለማስተናገድ" የተመረጡት ሰዎች ሁሉንም ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ አገልግሎታቸውን መፈጸም ቻሉ። የእግዚአብሔር ቃልም እየበፋ ሄደ፤ ያመኑትም ቁጥር እየጨመረ መጣ። ከተመረጡትም መካከል እስጢፋኖስ ለክርስቶስ ሲል የመጀመሪያው የሞት ጽዋ በመቅመስ የመጀመሪያ ሰማዕት ሆነ። የእርሱም እውነተኛ ጸሎት ለሳኦል (ጳውሎስ) መዳኛ ምክንያት ሆነ። ፊልጶስም ታላቅ ወንጌላዊ ሆኖ በሰማርያ ከፍተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ብዙዎች ወደ ደህንነት መጡ። የሐዋርያት ሥራን ስናነብ፣ በዘመኑ የነበረውን ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚመሩት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እንደነበሩ በግልጽ እናያለን።

- *ኢየሱስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና የተቀባ ነበረ (የሐዋ. 10፥38)*
- *ጴጥሮስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ሲቆም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነው (የሐዋ. 4፥8)*
- *እስጢፋኖስ በድንጋይ ሲወገር በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ፊቱ እንደ ጸሐይ ያበራ ነበር (የሐዋ. 7፥55)*
- *ጳውሎስ አገልግሎቱን ሲጀምር በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ነበር (የሐዋ. 9፥17)።*
- *በርናባስና ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት ተሰዩ (የሐዋ. 13፥2)።*

ከላይ እንደተመለከትነው የቀድሞዎቹ መንፈሳዊ መሪዎች የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወታቸው ካስፈለጋቸው፣ እኛማ ኃጢአትና ፈተና በበዛበት፣ በዚህ በመጨረሻው ዘመን የምንኖር አማኞችማ ምን ያህል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈልገን ይሆን? *በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ራስን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ውስጥ ማዋል ማለት ነው። መንፈሳዊ መሪ አዕምሮው፣ ስሜቱ፣ ፈቃዱና ጉልበቱ መንፈስ ቅዱስ እንዲጠቀምበት ራሱን ሙሉ በሙሉ የሰጠ መሆን አለበት። መሪው በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በሕይወቱ ይታያል። መንፈስ ቅዱስ የመሪውን የተፈጥሮ ስጦታ በመቀደስ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት እንዲኖረው ያደርገዋል። ሕይወታችንን በመንፈስ ቅዱስ* ቁጥጥር ውስጥ ሳናደርግ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል" ብንል፣ ማስመሰላችን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የለም። ኤ. ደብልዩ. ቶዘር እንዲህ ይላል፥



- "የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን እየፈለግን፣ በሕይወታችን ግን የግዴለሽነትና የኃጢአት ኑሮ የምንኖር ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስን እናሳዝናለን። የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን የሚሻ አማኝ የተደበቀ ኃጢአት በሕይወቱ መኑሩን መመርመር ያስፈልገዋል። ከእግዚአብሔር ሕልውናና ባሕሪ ጋር የማይስማማውን ማንኛውንም ዓይነት ኃጢአት፣ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጠለት ከሕይወቱ ፈጽሞ ማስወገድ አለበት። እግዚአብሔር የሚጠላውን ክፉ ነገር ችላ ብሎ ማለፍ የለበትም።"[17]

## 3. መንፈሳዊ መሪዎች ሕይወታቸውን በቅድስና መምራት አለባቸው

ኃጢአት መንፈሳዊ መሪን አይፈራም። ታላላቅ ናቸው የሚባሉትን መንፈሳዊ መሪዎች ሁሉ የሚደፍር ስለሆነ፣ መንፈሳዊ መሪዎች ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ለኃጢአት እጃቸውን ያልሰጡ፣ ሰይጣን ሳቀረበላቸው ፈተና ያልተሸነፉት ሁሉ፣ ከቅድስና ውጪ የሆነ ሕይወት እንዲኖሩ የሚገፋፋ ፈተና አይኖርባቸውም ማለት እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። የፍትወት ኃጢአት ቤተሰብን፣ ለረጅም ጊዜ በሙያውና በሥልጣን ላይ የቆየውን ሰው ክብርና ዝና የማጥፋት ኃይል አለው። የሚያስደንቀውና የሚያሳዝነው፣ ይሄ ኃጢአት የብዙዎችን ቤት ሲያፈርስ፣ አገልግሎታቸውን ሲያበላሽ፣ ክጥሩ ኑሮአቸው ሲያፈናቅል ቢታይም፣ ከዚህ ኃጢአት ብዙዎች የማይጠነቀቁ መሆናቸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ***"የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው፤ ደግሞ ኢያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ እንዲያውቅ ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን እንደማያውቁ አሕዛብ በፍትወት ሥጋ ምኞት አይሁን"*** (1 ተሰሎ. 4፥3-5) በማለት ይመክረናል። የክርስትና እምነት "ቅድስና" ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ እምነት ነው። የራስን ሥጋ ሳይቆጣጠሩ ቅድስና ሲኖር አይችልም። ሥጋችን የሥጋን ፍላጎት እርካታ በጣም ይፈልጋል። ስለ ሰው አዕምሮ፣ ስለ ስሜታችን አፈጣጠር፣ ስለ ውስጣዊው ሕይወታችን፣ ስለ ነፍስ፣ ስለ መንፈስ፣ መንፈሳዊነት ስላለው ነገር እያሌ መጽሐፎች ተጽፈዋል። ስለ ቁስአካላዊው ግን የተጻፉ ብዙ መጽሐፍት ግን አናገኝም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጳውሎስ ስለ ቁስአካላችን በመልዕክቶቹ የተለያዩ አሳቦችንና ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን ጽፏል፥

[7] D. J. Fant, A. W. Tozer, Christian Publications, Harrisburg, PA 1964.

- ሰውነታችንን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ አድርገን እንድናቀርብ ይጠበቅብናል (ሮሜ 12፥1)
- ብልቶቻችንን የክፉት መሣሪያ እድርገን እንዳናቀርብ ታዘናል (ሮሜ 6፥12-13)
- ሰውነታችን የክርስቶስ አካል ብልቶች ስለሆነ፣ ሰውነታችን የክርስቶስ እንደሆነ ማወቅ እለብን (1 ቆሮ. 6፥15)
- ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው (1 ቆሮ 6፥19)
- በሰውነታችን እግዚአብሔርን እንድናከብር ይጠበቅብናል (1 ቆሮ. 6፥20)
- ሰውነታችንን በቅድስናና በክብር እንድንይዝ ይጠበቅብናል (1 ተሰሎ. 4፥4)።

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ መመሪያዎችና ትዕዛዞች የተሰጡን ቢሆንም፣ ሥጋችን በቀላሉ ከመሰመር የሚያስወጣን ጊዜ እንዳለ እናውቃለን። ሥጋ እግዚአብሔር ራሱ የፈጠረው ስለሆነ፣ ብቻውን በራሱ "ክፉነት" የለውም። ደካማነቱ ግን ብዙ ዓይነት ፍላጎት ስላለው፣ ፍላጎቱን ለሟሟላት በዙሪያው ባሉ ፈታኝ በሆኑ ነገሮች በቀላሉ የሚሸነፍ መሆኑ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ያለባቸው የሥጋ ድካም በምንና በምን ላይ እንደ ሆነ ለይተው ያውቁ ይሆን? ሕብረተሰቡ በዝሙት መንፈስ በተጥለቀለቀበት በዚህ ክፉ ዘመን፣ ሥጋን ገትቶ (እሸንፎ) በቅድስና መኖር ምንም ያህል የማይቻል ቢመስልም፣ ለሥጋ ፍላጎት "እምቢ!" ብሎ በቅድስና መኖር ይቻላል። ጳውሎስ፣ *"እግዚአብሔር በቅድስና እንደንመላለስ እንጂ ለርኩሰት አልጠራንምና። እንግዲህ ይህን ምክር ንቆ የማይቀበል፣ የናቀው ቅዱስ መንፈሱን የሰጣችሁን እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አይደለም"* ይላል (1 ተሰሎ. 4፥7-8)። ጴጥሮስም በመጀመሪያው መልዕክቱ *"ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኋለሁ። ምንም እንኳ ክፉ እንደምትሠሩ አድርገው ቢያሟችሁም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን ሥራችሁን ዐይተው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ በአሕዛብ መካከል በመልካም ኑሩ"* (1 ጴጥ. 2፥11-12) በማለት ይመክረናል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅድስና በሌለው መንገድ ሕይወታቸውን ለመምራት ቢመርጡ፣ በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት የሚጎዱት እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ የክርስቶስ አካል የሆኑት ክፍሎች ሁሉ ናቸው። በእነርሱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ትነቀፋለች። ሁላችንም የአንዱ አካል ክፍሎች (ብልቶች) ስለሆንን፣ የአንዱ የአካል ክፍል ጉድለት፣ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ይወስናል። ስለዚህ እንዳችን ለሌላው ተጠያቂነት እለብን። ተጠያቂ ላለመሆን ብንመርጥም፣ መሆናችን አይቀርም (1 ቆሮ. 12፥14-27)። የተጠራነው እንድ ላይ በመያያዝ እንድናድግ እንጂ በተናጥል እንድንኖር እይደለም የተጠራነው። ስለዚህ የአንዱ ከመሥመር መውጣት ለሌላው መንፈሳዊ ዕድገት እንቅፋት መሆን ይችላል።



## 4. መንፈሳዊ መሪዎች ከክብር ጥማት ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው

በሁሉ ነገር የመቅደም፣ ከሁሉ በፊት የመሆንና በልጦ የመታየት ፍላጎት ዋና ምንጩ፣ እግዚአብሔር በጣም ከሚጸየፈው የትዕቢት ወይም የትምክህት መንፈስ ነው። ይህን ዓይነቱ መንፈስ ወይም ባሕሪ የሚታይባቸው ሰዎች ተለይተው የሚታወቁበት እንደኛው መንገድ፣ በሚታይባቸው የሥልጣንና የክብር መፈለግ ጥማት ነው። በሰው ሁሉ ዘንድ እንዲታወቁ በእጠገባቸው የሚያልፈው ሁሉ እጅ እንዲነሳቸው የሚፈልጉ ናቸው። ይህን በመሰለ ፍላጎት የተሞሉ ሰዎች ትኩረት የሚሰጡት በሥልጣናቸው ላይ እንጂ ለሌላው በሚሰጡት እገልግሎት ላይ እይደለም። ክብርና ሥልጣን የሚጠሙ ሰዎች፥ የሌላው ሰው ችግርና ብሶት የሚታያቸው እይደሉም። እነርሱ የሚፈልጉትን ሥልጣንና ክብር እስካስገኘላቸው ድረስ በእመራራቸው የሚሰጡት ውሳኔ፣ የሚወስዱት ዕርምጃ ርህራሄ፣ ሀዘኔታና ደግነት የጎደለው ቢሆንም እይቆረቁራቸውም። ኢየሱስ "ራስን ከፍ ማድረግ" ምን ያህል እንደሚጠላ የምንረዳው ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራንን እንዴት እንደ ነቀፋቸው ስናይ ነው። ማንነታቸውንና ድርጊታቸውን ሲገልጽ፣ *"ለመታየት ሲሉ የሚያደርጉትን ሁሉ በሰው ፊት ያደርጋሉ፤ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ፤ የቀሚሳቸውን ዘርፍ ያስረዝማሉ። በግብዣ ቦታ የክብሬታ ስፍራ፣ በምኩራብም የመጀመሪያውን መቀመጫ መያዝ ይወዳሉ። እንዲሁም በገበያ መካከል ሰላምታ መቀበልንና በሰዎች እንደቡት 'መምህር' ተብለው መጠራትን ይሻሉ"* ይላቸዋል (ማቴ. 23፥5-7)። ፈሪሳውያንና የሙሴ ሕግ መምህራን ሰምና ዝና፣ እንዲሁም የክብር መቀመጫ (ስፍራ) በጣም ይወዱ ነበር። እገልጋይ ወይም እሽከር ምን እንደሆነ የተረዱ ሰዎች እልነበሩም። ለመሆኑ አንዳንድ ሰዎች ማዕረግንና ሥልጣንን በጣም የሚፈልጉበት ምክንያት ምን ይሆን?

1ኛ) *የማዕረግ ሥፍራ ወይም ሥልጣን የሚፈልጉ ሰዎች፣ አንደኛው ምክንያታቸው ከሌሎች ልቀው ለመታየት፣ የመጨረሻውን ውሳኔ ለመወሰን ስለሚፈልጉ ነው።* የመጨረሻውን ውሳኔ መስጠት ደስ ይበላቸው እንጂ ያለበትን ኃላፊነትና ተጠያቂነት፣ እንዲሁም ውሳኔያቸው የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ምን ያህል እንደሚነካ የሚገነዘቡ እይደሉም። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ "የእለቅነት" መንፈስ ያለው፣ ራሱን የሚያትልቅ ሳይሆን፣ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ፣ እንዲሁም "የአገልጋይ" ልብ ያለው ሰው ነው። ኢየሱስ በሚገባን ዓይነት ጥሩ አድርጎ ገልጾታል። *"...የአሕዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው፣ ሹሞቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን እንደሚያሳዩ ታውቃላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም። ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን"* አለ (ማር. 10፥ 42-44)።

2ኛ) *ሰዎች የማዕረግ ሰፍራ የሚፈልጉበት ሁለተኛ ምክንያት፣ በሌሎች ላይ የበለጠ ሥልጣን እንዲኖራቸው (ለሰቃ እንዲሆኑ) ነው።* ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ፍላጎት የሚኖራቸው ሰዎች በራሳቸው የማይተማመኑ ናቸው። በሌሎች ላይ የበላይነታቸውን ወይም አለቅነታቸውን ሲያሳዩ፣ ልዩ ዕርካታ ይሰማቸዋል። ይሄም ከትህትና ሳይሆን ከኩራተኛ ልብ የሚፈልቅ ስሜት ነው። ስለ ሌላው ሰው ስሜት ግድ የሚላቸው አይደሉም። ከእነርሱ የተለየ ሀሳብ (አስተያየት) መቀበል አይሆንላቸውም። በራሳቸው ችሎታ የሚተማመኑ መሪዎች ስላልሆኑ፣ "የተሳሳትኩ እንደሆን" ብለው ይፈራል። በሌሎች ላይ ኃይለኛና አምባገነን በመሆን፣ የራሳቸውን የችሎታ ማነስና እንዲሁም ስህተታቸውን ለመደበቅ ይሞክራሉ።

3ኛ) *ሰዎች የማዕረግ ሰፍራ የሚፈልጉበት ሦስተኛው ምክንያት፣ ሰዎች እንዲያከብሯቸውና ስለ እነርሱ ጥሩ ግምት እንዲኖራቸው ነው።* እንዲህ ዓይነቶቹ መሪዎች ብዙ ጊዜ ማገልገል የሚፈልጉት ሀብትና ሥልጣን ያላቸውን፣ እንዲሁም ትልቅ ናቸው ብለው የሚያስባቸውን እየመረጡ ነው። እውነተኛ ያልሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፣ መከበርንና ተቀባይነት ማግኘት የሚችሉት ባላቸው ጽኑ አቋምና ተለዋዋጭነት በሌለው "ገጸባሕሪ" መሆኑን ግን አይረዱም። የግል ሕይወታቸው ጌታን ደስ የማያሰኝ ቢሆንም፣ ባላቸው የሥልጣን ደረጃ ብቻ የሚያከብሯቸው ስለሚመስላቸው፣ ሁልጊዜ የበላይ መሆናቸውን ማሳየት ይፈልጋሉ። ለጊዜው ተቀባይነት ያገኙ ይምሰላቸው እንጂ ከውስጣቸው ግን የማይቀበሏቸው መሆናቸውን አያውቁም። ማዕረግና ክብርን የተጠሙ ሰዎች ባነጋገራቸው፣ ባለባበሳቸው፣ ሌላው ቀርቶ ባረማመዳቸው እንኳን ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ያስታውቃሉ። ከሥራቸው ያሉትን ሰዎች ከመጠን በላይ የሚጫኑ፣ "አክብሩኝ" ባዮች ናቸው። የሚያሳዝነው እንዲህ ዓይነቶቹ ምንም ዓይነት የማዕረግ ሥፍራና ሥልጣን ቢኖራቸውም፣ ሰዎች ስለሚሸሿቸው ሁልጊዜ ብቸኞችና ደስታ የሸሸቻቸው መሆናቸው ነው።

አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የወደቁት ከውጪ በሚመጣ ግፊት ሳይሆን፣ ከውስጣቸው በመነጨ ኃይል ነው። የመውደቂያቸው አንደኛው ምክንያት፣ ትዕቢት (ኩራት) ነው። በምድራዊው ዓለም በሁለት አገሮች ወይም ኃይሎች መካከል በሚካሄደው ጦርነት፥ ሁለት ዓይነት ክፍሎች አሉ። በአንደኛው ክፍል ያሉት ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ወይም ግንባር ገጥመው የሚዋጉ ወታደሮች ናቸው። በሁለተኛው ክፍል ውስጥ ያሉት ደግሞ መሣሪያ የሚያቀብሉ፥ ሥንቅ የሚያዘጋጁ ናቸው። ለጦርነቱ መሳካት ወይም አሸናፊ ለመሆን ሁለቱም ክፍሎች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ሥንቅና መሣሪያ አቀባዮች ከሌሉ፣ ከጠላት ጋር ግንባር ገጥመው የሚዋጉ ወታደሮች ብቻቸውን ተዋግተው ጠላታቸውን ማሸነፍ አይችሉም። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች አሉ። ፊት ለፊት የሚታዩ አገልጋዮች



ብቻ ሳይሆኑ፣ ማንም ሳያያቸው በድብቅ የሚያገለግሉም እንዳሉ የታወቀ ነው። የተሰለፉበት አገልግሎት በሰው ፊት እንዲታዩ የሚያደርጋቸው አገልጋዮች ብዙ ጊዜ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው። በድብቅ፥ ማንም ሳያውቃቸው ከሚያገለግሉት ይልቅ፥ የሚታዩት የበለጠ ፈተናና ችግር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ግልጽ ነው። ለግፊትም ሆነ ለፈተና የተጋለጡ ናቸው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ *"እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁና ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ"* ብሎ ያለው (ያዕ. 3፥1)። *መንፈሳዊ መሪ "ፈጽሞ ስህተት የማይሠራው... የማይወድቀው... እንደ እርሱ ያለ አገልጋይ ጨርሶ የለም..."* የሚል ሙገሳና ሞብጨባ ይሰማል። ያኔ ነው መንፈሳዊ መሪ ከምንጊዜውም የበለጠ መጠንቀቅ ያለበት። ሰዎች የሚሰጡት መልካም አስተያየት እውነት መስሎት ይቀበልና "ማንም እንደ እኔ የለም" በማለት በራሱ መታበይ ይጀምራል። ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምክር ሲያስተላልፍ፥ ለሚያገለግሉት ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም መጠንቀቅ እንዳለባቸው ጠቃሚ ምክር የሰጣቸው። *"መንፈስ ቅዱስ እናንተን የመንጋው ጠባቂ አድርጎ ሾሞአችኋል፤ እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ"* አላቸው (የሐዋ. 20፥28)። ወጣት መንፈሳዊ መሪ የነበረውን ጢሞቴዎስን ሲመክረው፣ *"ለራስህና ለማስተማር ሥራህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ነገሮች ጽና..."* ይለዋል (1 ጢሞ. 4፥16)።

ሰው በደረጃ፣ በሥልጣን ከፍ ሲል፣ በልቡ ትዕቢት እየተሰማው ሊመጣ ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ከዚህ ፈተና ፍጹም ነጻ አይደሉም። እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ነገሮች መካከል አንደኛው ትዕቢት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"እግዚአብሔር በልብ የሚታበዩትን ሁሉ ይጸየፋል፤ እነርሱም ከቅጣት እንደማያመልጡ በእርግጥ ዕወቅ"* ይላል (ምሳሌ 16፥5)። ይሄ ኃይለኛና ከባድ ቃል ነው። እግዚአብሔርን ሁለተኛ ደረጃ ላይ አድርጎ ራስን ዙፋን ላይ ከማስቀመጥ የበለጠ እግዚአብሔርን ቅር የሚያሰኝ ነገር የለም። ሉሲፋርን ከሰማይ ወደ ምድር ተወርውሮ እንዲወድቅ ያደረገው "የእግዚአብሔርን ክብር በመሻማቱ" እንደሆነ እናውቃለን። ትዕቢት የተለያየ መልክና ቅርጽ አለው፤ መንፈሳዊ ትዕቢት ግን የበለጠ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል። ባለን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፣ ወይም በያዝነው መንፈሳዊ ደረጃ መታበይ፣ ስጦታውን ያገኘነው ከእግዚአብሔር መሆኑን መርሳታችን ይሆናል። "ትዕቢት" የተለያየ መልክና ቅርጽ አለው፥

(1) *እኛ እንዲሆንልን የምንፈልገውን ነገር ሌላው ሰው ቢያገኝ፣ እኛ የተመኘነውን ሹመት ሌላ ሰው ቢሾምበት፥ ከእኛ ይልቅ ሌላው ሰው እንደ አዋቂ ቢታይ የሚሰማን ስሜት ምን ዓይነት ነው?*

(2) *እውነተኞች ሆነን ራሳችንን ስንመረምር፥ ድካም በሕይወታችን ብናይ "ድካም አለብኝ" እንላለን? ሌሎች ሰዎችስ ድካማችንን ቢነግሩን የሚሰማን ስሜት ምንድነው?*

(3) *እንዳንድ ሰዎች ነቀፋ ሲወረውሩብን ዓለም በላያችን ላይ የተደፋብን ይመስለናል? ራሳችንን ለመከላከል ሰንል ቶሎ ምክንያት እንሰጣለን? እንዲሁም የነቀፉንን ሰዎች መልሰን እንነቅፋለን?*

ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጣቸው መልሶች ያለንበትን ሁኔታ ማሳየት ይችላል። እውነተኞች ሆነን ሕይወታችንን ጎንበስ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበው ጌታ ጋር ስናነጻጽረው የልባችንን አሰቀያሚነትና ቆሻሻነት አይተን በራሳችን ማፈራችን አይቀርም። ችግሮቻችን ምን ዓይነት ናቸው? ስለራሳችን ከመጠን በላይ እንጨነቃለን? "እግዚአብሔር ስለ እኔ ምን ያስባል? ምን ይላል?" ብለን በመጠየቅ ፈንታ፥ "ሰዎች ስለ እኔ ምን ይሉ ይሆናል?" በማለት ከመጠን በላይ እናስባለን? ሰዎች ከሆንነው በላይ፥ ወይም ያልሆንነውን "ናችሁ" እያሉ በሚሰጡን አድናቆትና ጥሩ አስተያየት (ሙገሳ) ልባችን የተሞላ ይሆን? በ1950 ዓ.ም ገደማ፣ አሜሪካ ውስጥ የነበሩ ታላላቅ ሰባኪዎችና የሚደነቅ የፈውስ ስጦታ አላቸው የሚባሉ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጨረሻቸው ምን ያህል አሳዛኝ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። ሰዎች በሚሰጧቸው ሙገሳ ሚዛናቸውን የሰቀቁ መንፈሳዊ መሪዎች፣ አንዳንዶቹ ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው ሲሞቱ፥ አንዳንዶቹ ደግሞ ሱስ የሚያስይዝ ዕጽ (ድራግ) በመውሰድ፥ መጠጥ በመጠጣት፣ እንዲሁም ሴሰኞች ሆነው ከአገልግሎታቸው እንደ ወጡ ይታወቃል። ችግራቸው ምን ነበር? በሰዎች ዘንድ የሚያገኙት ጭብጨባና ሙገሳ፥ ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ ስለሆነባቸው፥ ታዋቂነታቸው ገጸባህሪያቸውን እንዲያበላሽ ራሳቸውን አጋልጠው በመስጠታቸው ምክንያት ነው።

ሰው በደረጃና በሥልጣን ከፍ ሲል ወይም ሲያድግ፥ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት የተጠራው መንፈሳዊ መሪም እንኳን፥ ኩራቱ (ትምክሕቱ) እያደገ እንደሚመጣ የታወቀ ነው። በጊዜው ካልተቆጣጠረው፥ ለግል መንፈሳዊ ሕይወቱም ሆነ ለአገልግሎት ዕድገቱ ትልቅ እንቅፋት ይሆንበታል። እግዚአብሔር በባሕሪው ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ክብር ሲሻሙበት፥ ወይም ሲከለክሉት አይወድም። ቀናተኛ አምላክ መሆኑን ደጋግሞ ገልጿል። እግዚአብሔርን ትምክህተኛነት (ኩራት) እንደሚያሰቆጣው ሁሉ፥ እውነተኛነት ያለው ትሕትናም በጣም ያስደስተዋል። እግዚአብሔር ያከበራቸውና ያደነቃቸው ሰዎች ሁሉ፣ በትሕትናቸው የተደነቁ ሰዎች መሆናቸውን እናውቃለን። ከነዚህ መካከል አንደኛው ዮሐንስ መጥምቁ ነው። ዮሐንስ መጥምቁን ጎልቶ እንዲታይ ያደረገው በዘመኑ የነበረውን ኃጢአት በድፍረትና በሥልጣን በመቃወሙ፥ በሥልጣን ተሞልቶ ሰዎችን ወደ ንስሀ መጥራቱ ሳይሆን፥ የነበረው የትሕትና መንፈስ ነው። ራሱን ዝቅ፣ ክርስቶስ ግን ከፍ አድርጎ ሲናገር፣ ***"እርሱ ከፍ ከፍ እንዲል እኔም ዝቅ ዝቅ እንድል ያስፈልጋል"*** አለ (የዮሐ. 3፥30)። ይሄም ዮሐንስ መጥምቁ የነበረበት መንፈሳዊ ዕድገት ምን ያህል ግልጽና ጠንካራ እንደነበረ ያሳያል።



መንፈሳዊ መሪ የሚኖረው ትህትና ከመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገቱ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑን ማወቅ አለበት። ጳውሎስ ገና በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ የትሕትና ጸጋ ይታይበት ስለነበረ ***"እኔ ከሐዋርያት ሁሉ ያነስሁና ሐዋርያም ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ፤ ምክንያቱም እኔ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያሳደድሁ ነኝ"*** (1 ቆሮ. 15፥9) ሲል እንሰማዋለን። በአገልግሎት ውስጥ ከገፋ በኋላም ***"ምንም እንኳ እኔ ከቅዱሳን ሁሉ የማንስ ብሆንም ወሰን የሌለውን የክርስቶስን ባለጸግነት ለአሕዛብ እንድሰብክ ይህ ጸጋ ተሰጠኝ"*** ይላል (ኤፌ. 3፥8)። በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ምሕረት ሲናገር ***"ምንም እንኳ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን የሰደብሁና ያሳደድሁ፥ ያዋረድሁም ብሆን፥ እርሱ ምሕረት አደረገልኝ፤ ምክንያቱም ይህን ሁሉ ያደረግሁት ባለማወቅና ባለማመን ስለነበረ ነው"*** ይላል (1 ጢሞ. 1፥15)። የትሕትና ጸጋ በሕይወቱ ውስጥ ይታይበት የነበረ አንድ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው፥ ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ የሚያስተዋውቀው ሰው "ታላቁ ሐኪም" ብሎ ጠራው። ይህ ሰው ማታ እቤቱ ሲገባ በየቀኑ በሚጽፈው ማስታወሻ ላይ እንዲህ ሲል ጻፈ፥

> *"በእነርሱ ዓይን ትልቅ መስዬ ብታያቸው፥ ያለ እርሱ ምንም እንዳልሆንኩ፣ እንዲሁም የራሴን ትንሽነት እንዳይ እግዚአብሔር በጸጋው ረዳኝ። ትንሽም ብሆን ትንሽነቴን ሳይንቅ ይጠቀምብኛል። በእኔ ውስጥም የሚሆነው እርሱ ስለተጠቀመብኝ እንጂ፥ የእኔ ሥራ አይደለም። መጥረቢያ ምን ያህል ትላልቅ ዛፎችን ቆርጦ እንደጣለ እያሰበ ሊታበይ ወይም ሊኩራ አይችልም። ያለዛፍ ቆራጩ መጥረቢያው ብቻውን ዋጋ የለውም። መጥረቢያ አድርጎ የሠራው፥ በደንብ እንዲቆርጥ የሳለው፥ የተጠቀመበት ዛፍ ቆራጩ ነው። ዛፍ ቆራጩ ከእጁ አውጥቶ ቢወረውረው መጥረቢያው የወደቀ አሮጌ ብረት ብቻ ይሆናል። ይህንን እውነት ምንጊዜም እንዳልረሳ ይሁን" አለ።*

መንፈሳዊ መሪ "አለቃ" ሳይሆን፣ አገልጋይ (አሽከር) መሆኑን ተረድቶ ከእግዚአብሔር በአደራ የተቀበላቸውን ሕዝቦች ራሱን ዝቅ አድርጎ የሚያገለግል መሆን አለበት። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች አንደኛ እንጂ፥ "ሁለተኛ" መሆን፥ በልጠው መታየት እንጂ አንሶ መታየት የማይፈልጉ መሆናቸው ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔር በሰጠን የመሪነት ስጦታ መታበይ፥ "የእኛ ነው" የምንለው ማንኛውም መልካም ነገር ከእግዚአብሔር የተሰጠን መሆኑን መርሳት ይሆናል። ክብርና ስም ፈላጊነት ራሱን የሚገልጽበት አንደኛው፥ "እኔ" ባይነት ነው። "እኔ" ባይነት፥ "እዚህ ገብቼ፥ እዚያ ወጥቼ ...ይሄንና ያንን ሠርቼ..." በማለት ያልሆነውን ሆኖ፥ ትንሹን ትልቅ አድርጎ፥ አጋኖና አተልቆ ስለ ራስ ማውራት ነው። ስለተደረገው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት ፈንታ፥ ሁሉንም ከራስ ጋር ማያያዝ ትልቅ "ውሸት" ነው። የተከታዮቹንና የአድናቂዎችን ምስጋናና ጭብጨባ የሚወድ መንፈሳዊ መሪ፥ ራሱን ለመንፈሳዊ አደጋ የሚያ

ጋልጥ ነው። "እኔ" ባይነት ከሚታይባቸው መንፈሳዊ መሪዎች መካከል አንደኛው ጴጥሮስ ነው። አንድ ጊዜ ኢየሱስ *"ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ፤ ትታችሁኝም ትሸሻላችሁ"* (የማር. 14፥27) ሲል፥ ጴጥሮስ "እንዳንክድህ ምን እናድርግ?" ብሎ በመጠየቅ ፈንታ *"...ሌሎች ሁሉ እንኳ ቢክዱህ እኔ ከቶ አልክድህም"* (የማር. 14፥29) አለው። በዚሁ ዓይነት አባባሉ፥ "እኔ ከሌሎቹ ሁሉ እበልጣለሁ" ማለቱ ይመስላል።

ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን የተባሉ አንድ የሥነ መለኮት ምሁር፣ ከአንድ "የመንፈሳዊ መሪዎች ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት" ተጋብዘው፣ የአንድ እስላም ነቢይን ታሪክ ጠቅሰው ለተማሪዎቹ የሚደንቅ ንግግር አደረጉ። ያ ብሩህ አዕምሮ ያለው ነው ተብሎ ይደነቅ የነበረው እስላም ነቢይ፣ ሲያስተምር ሁልጊዜ ፊቱን በሻሽ ሸፍኖ ነበር። ፊቱን በሻሽ የሚሸፍንበት ምክንያት፣ በፊቱ ላይ የሚያንጸባርቀው የክብር ብርሃን ከኃይለኝነቱ የተነሳ ሰዎች ሊቋቋሙት አይችሉም በማለት ነበር። ከጊዜ በኋላ ያ ፊቱን የሚሸፍንበት ሻሽ እያረጀና እየተቀዳደ ሲመጣ፣ ያ ብሩህ አዕምሮ ያለው ነው ተብሎ የሚደነቀው ነቢይ ፊቱን በሻሽ ይሸፍነው የነበረው አስቀያሚነቱን ለመደበቅ እንደነበረ ሕዝቡ መረዳት ቻለ። ሮበርት ሉዊስ ስቲቨንሰን ለወጣቶቹ ለማስተላለፍ የሞከሩት መልዕክት በጥቅሉ፣ ትምህርቱ ምንም ያህል የረቀቀና የተደነቀ ይሁን፣ ድካሙን ለመሸፈን ምንም ዓይነት ዘዴና ብልሃት ይጠቀም፣ አንድ ቀን የዚያ አስተማሪ እውነተኛው ማንነቱ ተገልጾ መታየቱ የማይቀር ነው የሚል ነበር። ዛሬ በመንፈሳዊ መሪዎች የሚታየው አስቀያሚ የሆነው "እኔ ባይነት" (ትዕቢት) ነው? ወይስ የጌታ ኢየሱስ የክብሩ ነጸብራቅ?

የክብር ፍለጋ መንፈስ፣ የመንፈሳዊ መሪዎች አደገኛ ጠላት ነው። ብዙ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎችን በሚያሳዝን ሁኔታ የጣለ ነው። አደገኛነቱም፣ ሳይታወቅበት ቀስ በቀስ እየሰረሰረ ወደ ሰው ልብ ውስጥ በመግባት ብርቱ ነው የሚባለውንም ሰው የሚጥል በመሆኑ ነው። ይህን ዓይነቱ መንፈስ በመንፈሳዊ መሪዎች ሕይወት ውስጥ ራሱን የሚገልጸው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?

## 4.1. በሌሎች ሰዎች ልፋት መከበር ይፈልጋል

በክብር ፍለጋ መንፈስ የተሞሉ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ሌሎች ሰዎች በለፋበትና በደከሙበት ሥራ፣ ለራሳቸው ክብርን፣ ዝናን፣ መታወቅንና ምስጋናን የሚያገኙበትን ብልሃትና ዘዴ ይቀይሳሉ። የሌሎችን ሥራ ዝቅ፣ የራሳቸውን ግን ከመጠን በላይ አትልቆ በማሳየት ክብርን ለማግኘት ይጥራሉ። ስለ ራሳቸው ትልቅነትና አዋቂነት ብዙ ይናገራሉ። ጠቢቡ ሰሎሞን *"ሌላው ያመስግንህ እንጂ የገዛ አፍህ አይደለም፤ ሌላ ሰው ያወድስህ እንጂ የገዛ ከንፈርህ አይሁን"* (ምሳሌ 27፥2) በማለት ስለ ራሳቸው ትልቅነትና አዋቂነት አጋነው የሚያወሩትን፣ ልባቸው በትዕቢት የተሞሉትን ይመክራል። ክብር ፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ሌሎች እስኪያመሰግኗቸው ድረስ አይጠብቁም፤ የራሳቸውን ጥሩንባ (ቀንደ መለከት) ይነፋሉ። የሚሰሟቸው ሰዎች ሲያጋጥማቸው፣ እንደ ምንም



ብለው፣ መንገድ ፈልገው የሠሩትን ወይም ያደረጉትን ነገር ያወራሉ። በዓለማውያን መሪዎች ዘንድ "ትዕቢተኛነት" የሚታየው እንደ መጥፎ ባሕሪ ነው። በመንፈሳዊ መሪዎች ሕይወት የሚታይ ከሆነ ደግሞ ከዚያ የበለጠ ዘግናኝና አሳዛኝ ጠባይ ነው። ልባቸው ክብር ፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ሕዝቡ የለፋበትን፣ እግዚአብሔር ራሱ የበራውን ሥራ እነርሱ የሠሩት አድርገው በመውሰድ ክብርን ለማግኘት ይሞክራሉ። መንፈሳዊ መሪዎች አሽከር (ባርያ) ቢሆኑም፣ ትዕቢት እግዚአብሔር የእነርሱ አሽከር እንደሆነ አድርገው እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። ትልቅነታቸውን ማሳየት እንዲችሉ የጠየቁትን ነገር እግዚአብሔር መልስ የመስጠት ግዴታ ያለበት መስሎ ይሰማቸዋል።

የቤተ ክርስትያን ዕድገት ጥሩ ከሆነ፣ ያንን የመሰለ ዕድገት የተገኘው ጥሩ መሪዎች በመሆናቸው ምክንያት እንደተገኘ አድርገው በመውሰድ አጋነው ያወራሉ። እግዚአብሔር በጸጋው "ይህን አደረገ" በማለት ፈንታ፣ "እኔ ይህን አደረግሁ" ሲሉ፣ የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳቸው መውሰዳቸው እንደሆነ ፈጽሞ አይሰማቸውም። ትዕቢት የሚያመጣው አደጋ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ የምንረዳው በናቡከደናጾር ሕይወት ውስጥ የደረሰውን አደጋ ስናስብ ነው። ንጉሡ ናቡከደነፆር አንድ ቀን በሰገነቱ ሲመላለስ የባቢሎንን ከተማ ተመልክቶ ራሱን እያደነቀ፣ *"ግዛቴ ኃይሌ፤ ለገናናው ክብሬ ንጉሣዊ መኖሪያ ትሆን ዘንድ ያሠራኋት ታላቂቷ ባቢሎን ይህች አይደለችምን? አለ"* (ዳንኤል 4፥30)። ይሁን እንጂ *"ንግግሩን ገና ከአፉ ሳይጨርስ፤ እንዲህ የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ፤ 'ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ! ስለ አንተ የታወጀው ይህ ነው፤ መንግሥትህ ከአንተ ተወስዷል፤ ከሕዝብ መካከል ትሰደዳለህ ከዱር አራዊት ጋርም ትኖራለህ፤ እንደ ከብት ሣር ትበላለህ፤ በሰዎች መንግሥት ሁሉ ላይ ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና እነዚህንም መንግሥታት ለወደደው እንደሚሰጥ እስኪታወቅ ድረስ ሰባት ዓመታት ያልፋሉ"* አለው (ዳንኤል 4፥31-32)። ከዚህ በኋላ የሆነውን ታሪክ እናውቃለን። መንፈሳዊ መሪ፥ ለአገልግሎት የጠራውን አምላክ ደስ ማሰኘት የሚችለው፥ በሾመው ሰዎች ላይ "አለቃ" ሳይሆን፥ አሽከር ወይም አገልጋይ ሲሆን ብቻ ነው።

## 4.2. ከሌሎች መማር አይፈልግም

የክብር ፍለጋ መንፈስ የለውን አዕምሮ ይዘጋል። መንፈሳዊ መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸው ያገኘችው ዕድገት በእነርሱ ብቃት ብቻ የተገኘ እንደሆነ አድርገው የሚያምኑ ከሆነ፣ ከእነርሱ በስተቀር ያንን ቤተ ክርስቲያን መምራት የሚችል ሰው የለም ብለው ያምናሉ። ይህን ዓይነት እምነት ካላቸው፣ የማንንም ምክርና አስተያየት መቀበል አይፈልጉም። የእነርሱን ሀሳብ ሳይጠይቁ "አሜን!" ብለው የማይቀበሉትን፣ "እግዚአብሔር የመረጠውንና የቀባውን አይቀበሉም" በማለት ይገፏቸዋል። እንዲህ ዓይነቶቹ መሪዎች ከሌሎች ለመማር የማይፈልጉ በመሆናቸው፣ በአመራራቸው ሊያገኙት የሚችሉትን ዕርዳታም ሆነ ድጋፍ መግፋታቸው ይሆናል። ንጉሥ አካብ ረቂቅ የሆነ የአስተዳደር ችሎታ የነበረው፣ እንዲሁም ታላቅ የጦር መሪ ነበር። አንድ ድካም ነበረበት። ያም

የመንፈሳዊ ሰዎችን ምክር የማይሰማ መሆኑ ነበር። የይሁዳ ንጉሥ አካብ ሬማት ዘገለዓድን ለመውጋት አሰቦ የይሁዳ ንጉሥ የነበረውን ኢዮሣፍጥ በጦርነቱ እንዲተባበረው ጠየቀው። ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሩ ተስማማ፤ ግን "መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቅ" አለው። አካብ መስማት የሚፈልገውን ነገር የሚነግሩትን አራት መቶ ነብያትን ሰብስቦ "ሬማት ዘገለዓድን ለመውጋት ልሂድን ወይስ ልቅር?" ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም መስማት የሚፈልገውን ነገሩት። *"እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ሂድ ብለው መለሱለት"* (2 ዜና 18፥5)። ንጉሥ ኢዮሣፍጥ 400 ነብያት የሰጡት አሳብ ስላላስደሰተው፤ *"እንጠይቀው ዘንድ ሌላ የእግዚአብሔር ነቢይ እዚህ የለምን?"* ብሎ ጠየቀ (2 ዜና 18፥6)። ንጉሥ አካብም *"መኖርስ አለ፤ ግን ምንጊዜም ቢሆን ስለ እኔ ክፉ እንጂ ደግ ትንቢት ስለማይናገር እጠላዋለሁ..."* ሲል መለሰለት። አካብ እንዳለው ነብዩ ሚካያን አካብ ወደ ጦርነት ቢሄድ በጠላቱ ድል እንደሚሆን እውነቱን ነገረው። አካብ የእግዚአብሔር ሰው የሰጡውን ምክር አልቀበልም በማለት ነብዩ ሚካያን ወህኒ ቤት ጥሎ ወደ ጦርነት ሄደ። አካብ በጦርነቱ ድል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ በዚያ ጦርነት ምክንያት ሕይወቱን አጣ። መሪው ምንም ያህል አዋቂና የተማረ ቢሆን፤ የአዋቂዎችን ምክርና አሳብ የማይቀበል ከሆነ መጨረሻ ላይ ክፉ አወዳደቅ እንደሚወድቅ የታወቀ ነው። መንፈሳዊ መሪ እውነተኛነቱ የሚለካው፤ ከሌሎች ለመማር ፈቃደኛ የሆነ መንፈስ ሲኖረው ነው። ሰለሞን *"ፌዘኛ መታረምን ይጠላል፤ ጠቢባንንም አያማክርም"* (ምሳሌ 15፥12) ያለው፤ በራሱ ዕውቀትና ችሎታ ተማምኖ ሌሎችን አልሰማም፤ ከሌሎች አልማርም የሚለውን አካብን የሚመስሉትን መሪዎች ሲገልጽ ነው።

## 5. መንፈሳዊ መሪዎች ልባቸው በርህራሄ የተሞላ መሆን አለበት

እግዚአብሔር በሕዝቂል እማካኝነት ሰበጎቹ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማያደርጉት እረኞች ብርቱ የሆነ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ እንሰማዋለን። *"...ራሳቸውን ብቻ ለሚንከባከቡ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች መንጋውን ማሰማራት አልነበረባቸውምን? ሥጋውን ትበላላችሁ፤ የሰባውን ዐርዳችሁ፤ ነገር ግን መንጋውን አትንከባከቡትም። ደካማውን አላበረታችሁትም፤ በሽተኛውን አልፈወሳችሁትም፤ የተጎዳውንም አልጠገናችሁትም። የባዘኑትን አልመለሳችሁም፤ የጠፉትንም አልፈለጋችሁም፤ በግፍና በጭካኔ ገዛችኋቸው"* ይላል (ሕዝ. 84፥2-4)። ትዕቢተኛ ልብ ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎች ወደ አገልግሎት የሚገቡት የሚያገኙትን ጥቅም ተምነው እንጂ፤ የደከሙትን ለመደገፍ፤ የወደቁትን ለማንሳት፤ ተስፋ የቆረጡትን በተስፋ ለመሙላት አይደለም። ሁልጊዜ የሚያስቡት ስለ ራሳቸው ክብር፤ ትርፍና ምቾት ብቻ ነው። ለሚመሩት ሕዝብ የሚራራ ልብ ፈጽሞ የላቸውም። የሚመሩት ሕዝብ መከራ፤ ችግርና ጉዳት የማይሰማቸው መሪዎች፤ በራስ ላይ ያተኮረ ሕይወት እንዳላቸው ያሳያል። የሕዝቡን ፍላጎት ችላ ብለው ስማቸውን ሊያስጠራ በሚችል ነገር ላይ ትኩረት የሚሰጡ፤ ለመንፈሳዊ መሪነት ብቃት የሌላቸው ናቸው። ከቤተ ክርስቲያን ምዕመናን መካከል አንዱ የደረሰበትን ጉዳትና



ችግር ሲገልጽ፤ የዚያ ሰው ጉዳት የቤተ ክርስቲያን መጋቢውን ልብ ካልነካው፤ ወይም የእንዱ ሰው መጥፋት ካልቆረቆረው፤ ኃላፊነቱን እንደሚገባው የሚወጣ መሪ እንዳልሆነ በግልጽ ያሳያል። እንዲህ ዓይነቶቹ መሪዎች፤ ሮም በእሳት ስትቃጠል፤ በሙዚቃ ራሱን ያስደሰት እንደነበረው እንደ ኔሮ፤ እንዲሁም በፈረንሳይ የአብዮት እንቅስቃሴ ጊዜ "ሕዝቡ ዳቦ አጣን ብሎ ይጮኻል" ተብሎ ሲነገራት፤ "ዳቦ ካጡ ለምን ብስኩት አይበሉም" ብላ እንዳለችው የፈረንሳይ ንግሥትን መምሰላቸው ነው። ለሕዝባቸው ፍጹም ግድ የሌላቸው፤ ጨካኝ ልብ የነበራቸው መሪዎች መጨረሻቸው የከፋ እንደነበረ ታሪካቸው ይመሰክራል።

በሌላ በኩል ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በርህራሄ የተሞላ መሪ ለሕዝቡ ምን ያህል መራራትና መጠንቀቅ እንዳለበት ይዘረዝራል። በአንድ ወቅት ትልቅ ሁከትና ትርምስ ውስጥ ለነበረችው ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በሁለተኛው መልዕክቱ *"ሌላውን ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚያስጨንቀኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐሳብ ነው። ደካማ ማን ነው እኔስ አብሬ አልደከምምን? በኃጢአት የሚሰናከል ማነው? እኔስ አልቆጭምንን?"* ይላል (2 ቆሮ. 11፥28-29)። እውነተኛ መሪዎች ለሚመሩት ሕዝብ ጥንቃቄ ማድረግ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ምንጊዜም የሚረሱ አይደሉም። ትዕቢት ኃጢአት ስለሆነ፤ ኃጢአት የሚያደርሰውን ጉዳት ያውቃሉ። ትዕቢት ሕይወታቸውን እንዲቆጣጠረው አሳልፈው የሚሰጡ መሪዎች፤ ሁሉን ነገር ያጣሉ። ከሰው ጋር ያላቸው ግንኙነት ይበላሻል፤ ሕዝቡ በእነርሱና በአመራራቸው እምነት ያጣል፤ በመጨረሻም የያዙትን የመሪነት ሥፍራ ያጣሉ። ሰሎሞን *"ትዕቢት ጥፋትን፤ የእብሪት መንፈስም ውድቀትን ትቀድማለች"* (ምሳሌ 1618) በማለት ልባችንን እንድንጠብቅ ያስጠነቅቀናል። ያዕቆብ *"...እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"* ይላል (ያዕ. 4፥6)። ኢየሱስም *"...ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል"* (ሉቃ. 18፥14) በማለት ያስጠነቅቀናል።

## 6. መንፈሳዊ መሪዎች የሰዎችን አድናቆት የሚፈልጉ መሆን የለባቸውም

በሚያገለግላቸው ሰዎች መወደድ የማይፈልግ አገልጋይ ማን ነው? መጠላት ወይም አለመወደድ በረከት አይደለም። ይሁን እንጂ፥ ዝነኛነት አገልጋዩን ትልቅ ዋጋ የማስከፈል ዝንባሌ አለው። "ሰዎች ስለ እናንተ በጎ ሲናገሩ ተጠንቀቁ" በማለት ክርስቶስ ሲያስጠነቅቅ እንሰማዋለን። አንዳንድ እንግዳ የሆኑ ልምምዶችና እምልኮቶች ሊፈጠሩ የቻሉት ቀስ በቀስ ከመጠን ያለፈ "አድናቆትን" ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ባገኙት መንፈሳዊ መሪዎች እንደሆነ የታወቀ ነው። ተከታዮቻቸው መንፈሳዊ መሪው ባለው ጸጋና ችሎታ ከመጠን በላይ ሲደነቁ፥ በአዕምሯቸው እንደማንኛውም መንፈሳዊ መሪ "ሰው" መሆኑን ይረሱና ከማምለክ ደረጃ ይደርሳሉ። የሚያሳዝነው፥ መንፈሳዊ መሪውም ከተከ

ታዮቹ የሚሰጠውን ከመጠን ያለፈ ክብርና ምስጋና ደስ እያሰኘው ቀስ በቀስ እርሱም ራሱ ሰው መሆኑን እየረሳ ይመጣል። ይህን ዓይነቱ ፈተና ሐዋርያትም ነበረባቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ሲወለድ ጀምሮ ሽባ የነበረውን አንድ ሰው፥ በጸሎታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በእግሩ ቆሞ እንዲራመድ ስመሆኑ፥ ሕዝቡ በመደነቅ ሲከቧቸው ጴጥሮስ ***"እስራኤል ሰዎች ሆይ! በዚህ ነገር ስለምን ትደነቃላችሁ? ስለምንስ ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ? እኛ በራሳችን ኃይል ወይም በራሳችን መልካም ሥራ ይህን ሰው እንዲራመድ ያደረግ ነው ይመስላችኋልን?"*** (የሐዋ. 3፥12) በማለት ሕዝቡ ወደ እነርሱ ከመመልከት ይልቅ የፈውስ ምንጭ ወደ ሆነው ጌታ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለከቱ አደረጋቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስም ተመሳሳይ የሆነ ችግር በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አጋጥሞታል። ሕዝቡ የሚያደንቀውን መሪ እየጠራ *"እኔ የጴጥሮስ ነኝ፤ እኔ የአጵሎስ ነኝ... እኔ የጳውሎስ ነኝ..."* እያለ እርስ በርሱ መከፋፈል ጀምሮ ነበረ። አደገኛነቱን የተረዳው ጳውሎስ ይህን ዓይነቱን አቋም ለማስተካከል፥ እነርሱ የሚያደንቋቸውና የሚያሞጋግሷቸው ሰዎች ተራ አገልጋዮች መሆናቸውን፥ ክብር የሚገባው ግን እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን በሚገባቸው ቋንቋ ግልጽ አድርጎ ነገራቸው። ***"እኔ ተከልሁ፤ አጵሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ለሥራው ዋና የሆነው ተክሉ ያሳደገው እግዚአብሔር ነው እንጂ የተከለም ሆነ ውሃ ያጠጣ ምንም አይደለም"*** አላቸው (1 ቆሮ. 3፥6-7)። *መንፈሳዊ መሪዎች ሊወደዱ፥ የሚገባቸውንም* ክብር እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊሰጣቸው ይገባል። ይሁን እንጂ፥ የእግዚአብሔርን ክብር እንዳይሻሙ፥ በጥባቸው እግዚአብሔርን እንዳይጋርዱት ከፍተኛ ጥንቃቄ ካላደረጉ፥ ራሳቸውን መንፈሳዊ አደጋ ውስጥ እንደሚጥሉ የታወቀ ነው። ዮሐንስ መጥምቁ በዘመኑ በሕዝቡ ዘንድ በጣም የተደነቀና የተፈራ የጌታ አገልጋይ ነበር። የራሱ የሆኑ ደቀ መዛሙርት ነበሩት። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ ከሩቅ አይቶ፥ ሕዝቡ እኔን ማክበር ትተው እርሱን ያከብሩታል፥ እኔን መከተል ትተው እርሱን ይከተሉታል ብሎ ሳይፈራ፥ ***"እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይህ ነው! ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይበልጣል፤ ምክንያቱም ከእኔ በፊት ነበረ ያልኋችሁ ይህ ነው"*** (የዮሐ. 1፥29) በማለት ወደ ኢየሱስ እንዲመለከቱ አደረጋቸው። ጥሩ አገልጋይ አልፎ አልፎ ተገቢ የሆነውን ማበረታቻና ምስጋና መስጠት ክፉት የለውም። ይሁን እንጂ፥ ሕዝቡ ሊያመልከው ሲሞክር፣ አገልጋዩ "እምቢ!" ማለት አለበት። "ስቲቨን ኔል" (Stephen Neill) የሥነ መለኮት ምሁር፥ የሥነ መለኮት ተማሪዎቻቸውን፥

*"መንፈሳዊውን ሰው አደጋ ላይ ከሚጥሉት ልዩ ልዩ ምክንያቶች መካከል የበለጠ አደገኛው 'ዝነኛነት' ነው። ታላቅ የሆነ አወዳደቅ ወደሚያስከትልበት 'መንፈሳዊ ኩራት' ስለሚያደርሰው ነው። ዝነኛነት አገልጋዩን ለዓለም አጁን በመስጠት ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍለው ስለሚችል ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት"* አሉ።



የታወቀው ስፐርጀንም (Spurgeon) ይሄን 'የዝነኛነትን' ፈተና እንዳያሰናክለው በመፍራት በሕይወቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርግ ነበር።

*"የዕድል መቃናት' (success) ለሰዎች ግፊት ያጋልጠውና ያገኘውን ድል ወይም መሳካት ሥጋዊ በሆነ መንገድና ዘዴ በመጠቀም፥ አጥብቆ በመያዝ ሕይወቱ ለዚያ እንዲገዛ ፈተና ይሆንበታል። የዕድል መቃናትን ያገኘሁት፥ እግዚአብሔር በእኔ ሕይወት ውስጥ ታላቅ ሥራውን በመሥራቱ እንደሆነ ካልተረዳሁ በቀላሉ ወደ ራሴ ሊወጣ ይችላል። የማንንም ዕርዳት ሳይጠይቅ፥ ብቻውን ሥራውን በእኔ ሕይወት መቀጠል የሚችለው፥ ከሆንኩት በላይ እንዳልሆን፥ ራሴን እንዳውቅ በማድረግ ነው"* አለ።

*ጆርጅ ኋይትፊልድ (George Whitefield)* የታወቁ መንፈሳዊ መሪ የነበሩት፥ አገልግሎታቸውን እንደ ጀመሩ፥ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትንና፥ እንዲሁም ከሰዎች ዘንድ ክብርን ማግኘት እንደ እንጀራ የተራቡ፥ እንደ ውሃ የተጠሙ ሰው ነበሩ። መናቅ፥ አለመፈለግ፥ መባቂያ መሆን፥ ከሞት የባሰ ሞት ነው ብለው ያስቡ ነበር። በአገልግሎቱ ሲጎለምሱና ያገኙትም 'የዕድል መቃናት' ከፍ ሲል ግን፥

***"እስኪሰለቸኝና እስኪያቅለሸልሸኝ ድረስ ዝናንትን ለይቼአለሁ! ጠግቤአለሁ!"*** *አሉ።*

ሰውን እንዲሠራ ከሚገፉትና ከሚቀሰቅሱት ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ፥ 'የመመስገን ፍላጎት' ነው። በሌሎች ለመመስገንና ለመደነቅ መፈለግ የሰው ሁሉ ባሕሪ ነው። የምናደርገውን መልካም ነገር ሰዎች እንዲያውቁልን እንፈልጋለን። የተሻለ ወይም ከዚያ የበለጠ እንድንሠራና የላቀ ውጤት እንድናመጣ ምክንያት ይሆነናል። ጥያቄው ግን የጠበቅነውን ዓይነት ምስጋናና መደነቅን ከሰዎች ዘንድ ያላገኘን እንደሆን ይዞታችን ምን ይሆናል? የሚለው ነው። ያለሰዎች ምስጋና ጥሩ ሥራ ለመሥራት ራሳችንን የምናለማምደው እንዴት ነው?

- *1ኛ/ በዓለም ውስጥ ጎልቶ የሚታዩ ሥራዎች የተሠሩት፥ ከሰዎች ምስጋና በተቀበሉ ሰዎች አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሰዎች ያላዩአቸው፥ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ታላላቅ ሥራዎች ተሠርተዋል። አብዛኛዎቹ ዓለም ያደነቃቸውና ያጨበጨበላቸው ሰዎች አይደሉም። የታላላቅ ሰዎች የሕይወት ታሪክ ጸሀፊ (biographer) የነበረችው "አይዳ ታርቤል" (Ida Tarbell) የምታደንቀው ታላቅ ሰው ማን እንደሆነ ተጠይቃ "ማንነታቸውን ሰው ያላወቃቸው ናቸው" ብላ መልስ ሰጠች።*
- *2ኛ/ በሕይወታቸው ጠቃሚ የሆነ ታላላቅ ሥራዎችን ከሠሩት ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪሄዱ ድረስ የታወቁና የተመሰገኑ አለመሆናቸውን መረዳት ነው። ለሕብረተሰቡ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ ሥራቸው የታወቀው*

*እነርሱ ከሞቱ በኋላ ነው። በ1484 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) አሜሪካንን ያገኘው "ኮሎምበስ" (Columbus) ስላደረገው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያገኘው ከ$320 ዶላር የበለጠ እንዳልሆነ ታሪክ ጸሀፊዎች ይመሰክራሉ።*

- *3ኛ/ ብዙ ጊዜ የሰዎች ምስጋና ውሸትና ሽንገላ እንደሆነ ማወቅ አለብን። እኛም ራሳችን ጠቃሚና ዋጋ ያለው ነገር ምን እንደሆነ የማወቅ ችሎታችን የተወሰነ በመሆኑ፥ ብዙ ጊዜ የማይመለከተውን ስናመሰግን፥ የማይደነቀውን ስናደንቅ እንገኛለን። ብዙ ጊዜ "ምስጋና" ጥልቀት የሌለው ሽንገላ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም።*

የምስጋናን አደገኛነት የተረዳ አንድ ሰው፥ *"ምስጋናን እንደ ሽቶ በአግባቡ መጠቀም አለብን፤ በሽታው እንድንደሰትበት እንጂ፥ እንድንውጠው ወይም እንድንጠጣው አይደለም"* አለ። መንፈሳዊ መሪ፥ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ክብር ብሎ አገልግሎቱን ሲፈጽም፥ በሚያገለግላቸው ሰዎች ሁልጊዜ ላይመሰገን ይችላል። ይሁን እንጂ፥ የሚችለውን ሁሉ ከልቡ በማድረጉ በጌታ ፊት የሚሰማው የእርካታና የደስታ ስሜት ልዩ ነው። በአሁን ጊዜ ለሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ካልተመሰገኑ፥ ካልተጨበጨበላቸው፥ ዓለም በላያቸው ላይ የተደፋባቸው መስሏቸው ተስፋ የሚቆርጡ መንፈሳዊ መሪዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። መረዳት ያለባቸው እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራቸው፥ "ይጨበጨብላችኋል... ይመቻችኋል... ትከበራላችሁ... ባለጸጋ ትሆናላችሁ..." ብሎ ሳይሆን፣ "ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ... ትታሰራላችሁ... ትገደላላችሁ..." ብሎ ነው። የሕዝቤ አለቃ ሁን" ብሎ ሳይሆን፥ "የሕዝቤ አገልጋይ ሁን" ብሎ እንደሆነ መረዳት አለባቸው። እውነተኛ አገልጋይ ትንሽነቱ እንጂ፥ ትልቅነቱ ስለማይታየው የሰዎችን ጭብጨባና ሙገሳ አይናፍቅም።

## 7. መንፈሳዊ መሪዎች ደስታቸውና ሀዘናቸው ሚዛኑን የጠበቀ መሆን አለበት

በእግዚአብሔር አገልግሎት ውስጥ የተሰለፈ ማንኛውም አገልጋይ የራሱ የሆነ የደስታና እንዲሁም የተስፋ መቁረጥ ጊዜ ይኖረዋል። ባለሆነም፥ እነዚህን ሁለቱ ሚዛናቸውን ከለቀቁ፥ ይኸውም ሁልጊዜ ካዘነ፥ ወይም ሁልጊዜ ከፈነደቀ ራሱን ለአደጋ አጋልጦ መስጠቱ ይሆናል። እነዚህን ሁለቱን ሚዛናቸውን እንዳይለቁ ማድረግ ቀላል አይደለም። ኢየሱስ አንድ ጊዜ ሰባዎቹን ወንጌልን እንዲሰብኩ ሁለት ሁለት አድርጎ ልኳቸው፥ ተልኳቸውን ጨርሰው ሲመለሱ "አጋንንት በስምህ ተገዙልን" በማለት እጅግ ደስ ብሏቸው ነበር። ባገኙት ጊዜያዊ ውጤት ተደስተው ሚዛናቸውን መልቀቃቸውን የተረዳው ኢየሱስ *"...መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚያ ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ በሰማይ መዝገብ ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ እንጂ አጋንንት ስለታዘዙላችሁ አትደሰቱ"* (የሉቃ. 10፥20) በማለት ደስታቸው ሚዛኑን የጠበቀ እንዲሆን መከራቸው። መንፈሳዊ መሪ በአገልግሎቱ ጥሩ ውጤት ደስ ሊለው ይገባል። ይሁን እንጂ፥ ከመጠን ያለፈ ደስታው



እንዲታበይ፥ እንዲሁም የድሉ ምክንያት የሆነውን አምላክ እንዳይሸፍንበት ወይም እንዳያስረሳው ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። በአገልግሎት ውስጥ በአገኙት መሳካት ምክንያት ልባቸው በኩራት ተሞልቶ እንኳ እወዳደቅ የወደቁ መንፈሳዊ መሪዎች እንዳሉ የታወቀ ነው።

መንፈሳዊ መሪ በአገልግሎቱ ውስጥ ፈተና፣ ትግልና ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን፣ በጎ ጊዜም ያጋጥመዋል። ለመድረስ ካሰበበት ዓላማ ይደርሳል፤ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በኃይል ይታያል፤ ነፍሳት ይድናሉ፤ ብዙዎች ይባረካሉ። *ሮበርት ሙሬ መክቼይኒ* የተባሉ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከላይ የገለጽነውን ዓይነት መሳካት በአገልግሎታቸው ሲያዩ፣ በርከክ ይሉና ክብሩን ለሚገባው ጌታ "ይኸውልህ" ብለው ያገኙትን ድል ያስረክባሉ። ይህን ዓይነቱ ልማዳቸው፣ በአገልግሎታቸው የሚያገኙትን ስኬት ለጌታ ብቻ የሚገባው መሆኑን ተረድተው ለእርሱ ማስረከባቸው፣ የእግዚአብሔርን ክብር ከመሻማት አዳናቸው። ሳሙኤል ቻድዊክ የተባሉ ጸሀፊ፣

> *"ስኬት' የደስታ ጩኸት ካልጮኸ፣ ሽንፈትም ከፍተኛ ኀዘንና ድምጽ ሊያሰማም"* አሉ።[18]

የሰውን ልጅ በሕይወቱ ከሚያጋጥሙት ችግሮች መካከል አንደኛው "የመንፈስ ጭንቀት" ነው። በዓለም ውስጥ ታላላቅ መሪዎች፣ ዝናን ያተረፉ የፖለቲካ ሰዎች፣ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች፣ ሙዚቀኞች፣ ጸሀፊዎች፣ ወዘተ. *"በመንፈስ ጭንቀት"* ልምምድ ውስጥ አልፈዋል። መንፈሳዊ መሪዎችም ከዚህ ችግር ነጻ አይደሉም። የተሃድሶ እንቅስቃሴ መሪ የነበረው *ማርቲን ሉተር፣ ታላቁ እንግሊዛዊ ሰባኪ ስፐርጀንና* እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች በዚህ ችግር ውስጥ አልፈዋል። በሕይወታቸው አልፎ አልፎ በመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ያለፉ፣ ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች እንዳሉ እናውቃለን። ኢዮብ በሕይወቱ መከራ ላይ በላዩ ሲደራረብበት፣ ሊያጽናኑት ከመጡት ጓደኞቹ ጋር ሲነጋገር ያሰማ የነበረው እሮሮ፣ በመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ያልፍ እንደነበረ ያሳያል። በድፍረቱና በቆራጥነቱ የተደነቀው፣ ማንንም የማይፈራው፣ ንጉሥ ሄሮድስ ፊት ቆሞ በድፍረት "የወንድምህን ሚስት ማግባት የለብህም" ብሎ የተናገረው ዮሐንስ መጥምቁ፣ ወህኒ ቤት በተጣለበት ወቅት የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ በነበረበት ጊዜ፣ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ" በማለት በእምነት ተሞልቶ የተናገረለትን ኢየሱስ መሲህነቱን ተጠራጥሮ፣ *"መሲሁ አንተ ነህ ወይስ ሌላ እንጠብቅ?"* ብሎ መልክተኛ እንደላከበት እናስታውሳለን። ሐዋርያው ጳውሎስም በተለያየ ጊዜ በመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ያልፍ እንደነበረ ከጻፋቸው መልዕክቶች ልንረዳ እንችላለን።

መንፈሳዊ መሪ ደስታ ብቻ ሳይሆን *"ከመጠን ያለፈ ሀዘንም" (የመንፈስ ጭንቀት)* በሕይወቱ ትልቅ ፈተና ሊሆንበት ይችላል። ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ታላቅ እጅ ካየ በኋላ፥ ከተራራው ሲወርድ በመንፈሱ በጣም በመጨነቁ ምክንያት

[18] Samuel Chadwick (London: Hodder & Stoughton, 1934).

ሞትን እንደተመኘ እናስታውሳለን። ኤልያስ ቁጭ ብሎ ለራሱ ማልቀሱን እግዚአብሔር
ስላልወደደ፥ ለተራበው ሥጋው ምግብ፥ ለደከመው መንፈሱ ዕረፍት እንዲያገኝ ካደረገ
በኋላ የተቀረውን አገልግሎቱን እንዲፈጽም ላከው። ኤልያስ ተስፋ የቆረጠበት አጥጋቢ
ምክንያት አልነበረም ባንልም፥ ሞት እስከ መመኘት ግን የሚያደርስ አልነበረም። ሊያጠ
ቁት የፈለጉ ሰዎች ዛቻ፥ በወቅቱ የተሰማው የብቸኝነት መንፈስ፥ በቃርሜሎስ ተራራ ተገ
ልጦ ያየውን የእግዚአብሔርን ኃይልና ታላቅ ክንድ ከእርሱ ጋር መሆኑ እንዳይመለከት
ዓይኖቹን ሸፈኑበት። መንፈሳዊ መሪ በአገልግሎቱ ውስጥ ለማድረግ ያቀደውን ሁሉ
ይፈጽማል ማለት አይደለም፥

*~ ያመናቸውና የወደዳቸው ሰዎች ሊያሳዝኑት ወይም ሊከዱት፥*

*~ "ጥሩ ነው" ብሎ ያቀደው ፕላን ባልጠበቀው ሁኔታ ሊበላሽበት፥*

*~ ልዩ ልዩ ክፉ የሆኑ ነገሮች ድንገት ሊደርስበት፥ እንዲሁም*

*~ ምንም ያህል ጥረት ቢያደርግ አገልግሎቱ የማይጥማቸው አንዳንድ ሰዎች፥
የተቃውሞ ድምጻቸውን ሊያሰሙ፣ ተስፋ ሊያስቆርጡት ይችላሉ።*

በዚህ ወቅት ሰው ነውና በተስፋ መቁረጥ ልቡ ተሞልቶ አገልግሎቱን ትቶ ለመው
ጣት እንደሚፈተን የታወቀ ነው። ከመጠን ያለፈ ሀዘን መንፈሳዊ መሪውን ተስፋ ማስቆ
ረጥ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ኃይል እንዳይታየውም ያደርጋል። ይሁን እንጂ፥ የመ
ንፈሳዊ መሪ ፈተናው ይሄ ብቻ አይደለም። ሁኔታው ተለውጦ፥ ክፉው ጊዜ አልፎ በጎ
ዘመን ይመጣለታል። ከወሰነው ግብ ይደርሳል። ዕቅዱ ሁሉ ይሳካል። ነፍሳት ይድናሉ፤
ክርስቲያኖች ይባረካሉ። እንዲህ ዓይነት የበረከት ጊዜ ሲያጋጥመው፥ የድሉን አክሊል
በራሱ ላይ በመጫን ፈንታ፥ ለሚገባው ጌታ አሳልፎ መስጠት አለበት። ይሄም የእግዚአ
ብሔርን ክብር ከመሻማት ይጠብቀዋል። እግዚአብሔር ከባረካቸውና በአገልግሎታቸው
የብዙ ሰዎችን ሕይወት ከነኩት ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች መካከል አንደኛው ከላይ
ስሙን የጠቀስነው፣ "የሰባኪዎች ቁንጮ" ተብሎ የሚታወቀው እንግሊዛዊው ስፐርጀን
ነው። ይሁን እንጂ፣ ስፐርጀን በሕይወቱ በአዕምሮ ጭንቀት ልምምድ ውስጥ ያለፈ
እንደ ነበረ ታሪኩ ይመሰክራል። ስፐርጀን ስለሁኔታው ሲገልጽ እንዲህ አለ፥

*"ከአንድ ትልቅ የአገልግሎት ድል (መሳካት) በኋላ "የጠለቀ መከፋት" (depress-
ion) ውስጥ ማለፍ በጣም የተለመደ ነው። ...ለንደን ከተማ ውስጥ ለመጀመሪያ
ጊዜ መጋቢ ሆኜ ሳገለግል በዚህ ልምምድ ውስጥ አልፌአለሁ። በወቅቱ ያገኘሁት
መልካም ውጤት አስደነገጠኝ። የተከፈተልኝ የአገልግሎት በር በጣም አስፈንድ
ቆኝ መጨረሻ ላይ ከጠለቀው አዘቅት ውስጥ ወርውሮ ጣለኝ፤ ከመከራዬና ከጭን
ቀቴ የተነሳ "ክብር ይሁን ለኃያሉ ጌታ" ለማለት የሚያስችል አቅም አጣሁ። "ይህ
ንን ታላቅ (ብዙ) ሕዝብ መምራት የምችል እኔ ማን ነኝ?' እንዳልታይ ወደ መጣሁ
ባት ትንሽ መንደር ልወሰድ፤ ወይም ወደ አሜሪካ ተሰድጄ፣ እዚያ ካለ ጫካ
ውስጥ ሆኜ ከእኔ የሚጠበቀውን ነገር ለማድረግ ብቃት እስከማገኝበት ጊዜ ድረስ*



*ልቀመጥ። በዚህ ጊዜ በሕይወቴ ሙሉ የሠራሁት ሥራ ሽፋኑ የተገለጸው፤ ምን
ላይ ይሆን ብዬ በጣም ፈራሁ። አምነተቢስ እንዳልሆንኩ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር
ግን በፍርሃትና በዋጋቢስነት ስሜት ተሞላሁ... እግዚአብሔር ለትልቅ አገልግሎት
ሲያዘጋጀኝ ይህን ዓይነቱ "የጠለቀ መከፋት" ይደርስብኛል።"*[19]

የመንፈስ ጭንቀት ብዙ ጊዜ ግልጽ በሆነ፣ በተለያየ ምክንያት በሰው ላይ ሊደርስ
ይችላል። ኤልያስ የመንፈስ ጭንቀት እንዲሰማው የሆነበት የራሱ ምክንያት ነበረው።
*"እኔ ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቼአለሁ፤ እስራኤላውያን ኪዳንህን ትተ
ዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና። የቀረሁት እኔ
ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ አለ"* (1 ነገሥት 19፥10)። እግዚአብሔር
ቀናተኛ አምላክ መሆኑን የተረዳው ኤልያስ (ዘጸ. 34፥14) ለእግዚአብሔር ሲል ቢቀና፣
"ልክ አይደለህም" ብሎ የሚፈርድበት ሰው ይኖር ይሆን? ዛሬም መንፈሳዊ መሪዎች የሕ
ዝቡ ልብ ከእግዚአብሔር መሸሹን፣ ኃጢአት በዓለምም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ
መብዛቱን፣ ክርስቲያኖች ቅድስና በጎደለው ሕይወት ውስጥ መመላለሳቸው ግድ ብሏ
ቸው ውስጣቸው ቢጨነቅባቸው የሚፈርድባቸው ሰው ይኖር ይሆን? በዚህ ዓይነት ምክ
ንያት መንፈሳቸው ለሚጨነቅባቸው ሰዎች ኢየሱስ *"የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽና
ናትን ያገኛሉና"* ይላቸዋል (ማቴ. 5፥4)። መንፈሳዊ መሪዎች በአገልግሎታቸው እግዚአ
ብሔር እንዲከብር እውነተኛ ጥማት ኖሯቸው የጠበቁትን ውጤት ማየት ቢያቅታቸውና
የመንፈስ ጭንቀት ቢሰማቸው፣ ከላይ ያነበብነው ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ በተና
ገረው ቃል ሊጽናኑ ይገባል። ውስጣዊ ጥማታቸው የራሳቸውን ስምና ዝና ከፍ ለማድረግ
ከሆነ፣ በአገልግሎት ስም የሚያደርጉት ትግልና ሩጫ የጠበቁትን ዓይነት ውጤት ላያስገ
ኝላቸው ይችላል። ያኔ ኢጋኝ የሌለው የመንፈስ ጭንቀት ሊደርስባቸው ይችላል። ይህን
ዓይነቱ የመንፈስ ጭንቀት፣ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ገፍቶ የሚያስወጣቸው ብቻ ሳይ
ሆን፣ የዕለት ኑሯቸውን መኖር እያስችላቸውም። የሕዝቡ ጣዖት አምላኪነት፣ ቅድስና
የሌለው ሕይወታቸውና ኑሯቸው፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን ችላ ማለታቸው ኤልያ
ስን አሳዝኖት የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ እንደከተተው ከላይ ተመልክተናል። ለእውነ
ትና ለቅድስና መቆም (መቅናት) አንዳንድ ጊዜ መስመሩን ሲለቅ፣ በኃጢአት ውስጥ
የሚኖሩትን ሰዎች ለማውገዝ ጥቃቅኑ የሰው ድካም በመብራት መፈለግ፣ እንዲሁም
ሠማ አጥባቂ ወደ መሆን ይመራል። መንፈሳዊ መሪ እንዲህ ዓይነት አቋም ሲኖረው፣
የሚያገለግላቸውን ሰዎች መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱም ደስታ የሸሸው፣ በመንፈስ ጭን
ቀት የተሞላ ይሆናል።

19 J. Oswald Sanders

## ምዕራፍ ፩

# ሎሌዊነት

"እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤ እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል" (1 ቆሮ. 4፥5)።

"ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት የተነሣ እንዳችሁ ለእንዳችሁ ተገዙ" (ኤፌ. 5፥21)።

"አሽከር...ገረድ...ባርያ...ጌቶች...እመቤት..." እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ቃላት ስንሰማቸው ስላደግን፣ ለብዙዎቻችን አዲስ አይደሉም። "ጌቶች...እመቤት..." ተብለው የሚጠሩትን ስናከብር፣ "አሽከር...ገረድ...ባርያ..." የተባሉትን ደግሞ ስንንቅ ኖረናል። ይህን ዓይነቱ ልዩነት በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በሐዋርያት ዘመንም የነበረ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ያዕቆብ ጌታውን አክብረን ድሃውን እንዳንንቅ፣ አድልዎ እንዳናደርግ የሚያስጠነቅቀን (ያዕ. 2፥1-9)። ልጆች "ሲታድጉ ምን መሆን ትፈልጋላችሁ?" ተብለው ሲጠየቁ፥ "አሽከር...ገረድ...ባሪያ...መንገድ ጠራጊ... ኩሊ... መሆን እፈልጋለሁ" የሚል የለም። ክብር ያለበትን ሥራ መርጠው "ዶክተር... መሃንዲስ... ወዘተ. መሆን እፈልጋለሁ" ይሉናል። በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ፕሬዚደንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር፣ የካብኔ አባሎች ሲኖሩ፣ በወታደር ሥርዓት ውስጥ ደግሞ "ጄኔራል፣ ኮሬኔል፣ ሻለቃ፣ ሙቶ አለቃ ወዘተ." በማለት በማዕረግና በደረጃ የተከፋፈሉ ናቸው። በስፖርት ዓለም ደግሞ ዋና፣ ምክትል አሰልጣኝ፣ ዋና ተጫዋች (ተወዳዳሪ) እንዲሁም ተጠባባቂ፥ በኩባንያ ዓለም የኮርፖሬሽኑ ዋና ፕሬዚደንት (CEO)፣ የተለያዩ የቅርንጫፍ



ማኔጀሮች፣ ተቆጣጣሪዎችና ሰፊው ወዝ አደር (ተራ ሠራተኛ) በደረጃና በሥልጣን የተከፋፈሉ ናቸው።

## 1. ሰው በኃይል የሚገዛውን ሳይሆን፥ በትህትና የሚመራውን ይፈልጋል

በምድራዊው ዓለም ውስጥ ከላይ በገለጽነው ዓይነት የሥልጣንና የደረጃ ልዩነት እንዳለው ዓይነት ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ይኖር ይሆን? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ሥጋ የለበሰ ሰው ሁሉ ማዕረግና ሥልጣን የሚያስገኝለትን ከፍ ያለውን እንጂ፣ ዝቅ ያለውን ደረጃ የሚፈልግ የለም። በዓለም ውስጥ ያለውን የሥልጣን ትግልና ሽሚያ የሚያውቀው ጌታ ኢየሱስ፣ በደቀ መዛሙርቱ መካከል ይህን ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይፈጠር ሲያስጠነቅቃቸው፥ "የአሕዛብ ገዦዎች በሕዝቦቻቸው ላይ ጌቶች እንደሚሆኑ ባለ ሥልጣኖቻቸውም በኃይል እንደሚገዟቸው ታውቃላችሁ፤ በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የቤታች ይሁን" (የማቴ. 20፥23-27) አላቸው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ አገልግሎት ሲጠራቸው "ኑና ጌቶች... ባለሥልጣኖች... በኃይል የምትመሩ ሁኑ" ብሎ ሳይሆን፣ "ኑና አሽከሮች...ገረዶች...አገልጋዮች ሁኑ" ብሎ ነው። ደቀ መዛሙርቱ የወንጌል ተልዕኮ ኃላፊነትን ከጌታ የተቀበሉት በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሆነው ለማገልገል ነው። ዛሬ እኔና እናንተን ጌታ ኢየሱስ የሚጠራን "አሽከር...ገረድ" ሆነን፣ ዝቅ ብለን፣ የእርሱን አርአያ ተከትለን ሌሎችን እንድናገለግል እንጂ "ጌቶች...ባለሥልጣኖች... ገዦዎች"እንድንሆን አይደለም።

"ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን" የሚለው የክርስቶስ ትእዛዝ በዚህ በእኛ ዘመን የተረሳ ወይም ተቀባይነት የሌለው፣ ከጊዜው ጋር የማይሄድ፣ ወይም ጊዜ ያለፈበት አባባል ይመስለን ይሆን? በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለው ራስ (ዋና) አንድ ብቻ ነው። ያም ራስ (ዋና) ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ጳውሎስ "እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር የበላይነት ይኖረው ዘንድ እርሱ የመጀመሪያ ከሙታን መካከልም በኩር ነው" ይላል (ቆለ. 1፥18)። ይህን ራሥ የሚለውን ሥልጣን (ሥፍራ) ሥጋ የለበሰ ሰው ለመያዝ ችሎታም ሆነ ኃይል ያለው ማንም የለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአማኞች መካከል ችግር የሚፈጠረው፣ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ "የማዕዘን ራሥ (ዋና) እኔ ልሁን" ሲል ነው። በሐዋርያት ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋና ለመሆን ከሞከሩት ውስጥ አንደኛው ዲዮጥራጢስ ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ እርሱ ሲጽፍ፣ "ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጽፌ ነበር፤ ነገር ግን መሪ መሆን የሚወደው ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም፤ ስለዚህ እኔ ከመጣሁ እርሱ በክፉ ቃላት ስማችንን ለማጥፋት የሚያደርገውን ሁሉ ይፋ

*አመጣለሁ፤ ይህም አልበቃ ብሎት ወንድሞችን አይቀበልም ሊቀበሏቸው የሚፈልጉትን ይከለክላቸዋል፤ ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣቸዋል"*(3 ዮሐ. 9-10) ይላል። በሐዋርያት ዘመን በዲዮጥራጢስ ምክንያት በምዕመናን መካከል የተፈጠረው አለመግባባትና ግጭት ቤተ ክርስቲያንን በጣም እንደጎዳት እንገምታለን። በእኛ ዘመን እንደ ዲዮጥራጢስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዋና መሆን የሚፈልጉ ሰዎች ለመሆኑ እነማን ይሆኑ? የቤተ ክርስቲያን አለቃ መሆን የሚፈልገው ሰው መጋቢ (ፓስተር)፣ የሽማግሌዎች ሊቀ መንበር፣ "ቤተ ክርስቲያኗን የጀመርኩት እኔ ነኝ" የሚለው ሰው፣ በአጠቃላይ "እምባገነን" የመሆን ጥማት ያለው ማንኛውም ምዕመን ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ *"ዋና አለቃ"* የመሆን ምኞት ያላቸው ሰዎች፣ ይሄ ጥማታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያስከትሰውን ችግር ከዲያጥራጢስ ታሪክ ይማራሉ ብለን እናምናለን። ሐዋርያው ጳውሎስ *"...ከውጪ ጠብ፣ ከውስጥ ደግሞ ፍርሃት ነበረብን..."* (2 ቆሮ. 7፥5) በማለት የጻፈውን መልዕክት ስናይ፣ በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ በሐዋርያት ዘመንም በአማኞች መካከል የእርስ በርስ ጦርነት (ግጭት) እንደነበረ እንረዳለን።

*መጽሐፍ ቅዱስ ራሳችንን ከሆንነው በላይ ከፍ አድርገን እንዳንመለከት፣ ራሳችንን* ከሌሎች እንደተሻልን አድርገን እንዳንቆጥር በግልጽ ቢናገርም፣ ብዙዎቻችን እንደ ቃሉ አንኖርም። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው በመጀመሪያው መልዕክቱ ስለ ራሱ ሲገልጽ፣ *"ወንድሞች ሆይ! ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ የእግዚአብሔርን ምስጢር በረቀቀ የንግግር ችሎታ ወይም በላቀ ጥበብ ልገልጥላችሁ አልመጣሁም። በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና። ወደ እናንተ የመጣሁት በድካምና በፍርሃት፣ እንዲሁም በብዙ መንቀጥቀጥ ነበር"* (1 ቆሮ. 2፥1-3) ይላል። ሌሎችም ስለ እርሱ የሰጡትን አስተያየት ሲጠቅስ *"...መልእክቶቹ ከብድና ጠንካራ ናቸው፤ ነገር ግን በአካል ሲታይ ደካማ፣ ንግግሩም የተናቀ ነው ይላሉ"*(2 ቆሮ. 10፥10) አለ። ከላይ እንዳየነው ጳውሎስ ስለ ራሱ የሰጠው ገለጻ፣ ትሁት ለመምሰል ከሆነው በታች ራሱን ዝቅ አድርጎ ማቅረቡ ሳይሆን፣ የሆነውን መግለጹ ነው። ሌሎችም ስለ እርሱ የሰጡት አስተያየት እርሱ ስለ ራሱ ከሰጠው አስተያየት በጣም የተለየ አልነበረም። እርግጥ ነው ጳውሎስ ሁሉም ነገር ተሟልቶ የተሰጠው፣ ፍጹምነት ያለው ሰው አልነበረም። ይህን እውነት መደበቅ አልፈለገም። ለዚህ ነው ስለ ራሱ ማንነት በትክክል የገለጸው። በቆሮንቶስ አማኞች በፊት በቆመበት ወቅት በፍርሃት እንደተንቀጠቀጠ፤ ደካማና ፈሪ እንደነበረ አልደበቃቸውም። ለመሆኑ ጳውሎስ ስለነበረው ቁመና ሌሎች ምን ይሉ ይሆን? የታወቁት አሜሪካዊ ሰባኪ፣ ቸክ ስዊንዶል ጳውሎስ የነበረውን ቁመና ሲገልጹ፥



*"መለስተኛ ቁመና ያለው...በጣም አጭር የሆነ ጥቅልል ጸጉር ያለው፣ ጠማማ እግር... ወደ ውጪ ያፈነገጡ ዓይኖች፣ የተሸራረበ ቅንድብ፣ ትልቅ አፍንጫ፣ ወፍራም ከንፈር ያለው ሰው ነበር"* ይላሉ።[20]

ይህን ዓይነቱን መግለጫ ግን ከየት እንዳገኙት ራሳቸውም የማያውቁ መሆናቸውን ገልጸዋል። ትህትና ማለት ራሳችንን ከሆንነው በታች አሳንሰን ማቅረብ ማለት አይደለም። ጳውሎስ ምንም ሳይደብቅ፣ ምንም ሳይጨምርና ሳይቀንስ ልክ እንዳለው የራሱን አቋም የገለጸ ሰው ነው። ራሱን ሥጋ ለባሽ እንጂ ከላይ ከሰማይ የወረደ ልዩ ፍጥረት እንደሆነ፣ ምንም ዓይነት እንከን እንደማይገኝበት ሰው አድርጎ አላቀረበም። ጳውሎስ ትህትናው እውነተኛ እንጂ የፈጠራ ወይም የማስመሰል አልነበረም። *"ቃሌም ስብከቴም የመንፈስን ኃይል በመግለጥ እንጂ፣ በሚያባብል የጥበብ ቃል አልነበረም፤ ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሠረት ነው"* ይላል (1 ቆሮ. 2፥4-5)። ራሱን ዝቅ፣ ጌታውን ግን ከፍ አድርጎ በማሳየቱ፣ አጠገቡ ሆነው ከእርሱ የተማሩት ሁሉ የሚያደንቁት፣ ጳውሎስን ሳይሆን ጥበብንና ማስተዋልን የሰጠውን ክርስቶስን እንደነበረ እርግጠኞች ነን። ሰዎች ዓይናቸውን በክርስቶስ ላይ በማሳረፍ ፊንታ ጎልቶ በሚታየው መሪ ላይ ትኩረት ሲያደርጉ፣ ሥጋ ለባሽ የሆነውን፣ ክብር ለማይገባው ሰው ክብርን ሲሰጡ፣ ሰውን "የማዕዘን ራሥ" ማድረጋቸው መሆኑን የሚገነዘቡት አይመስለንም።

አዳም በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ በዓለም ውስጥ፣ በተለያዩ ሁለት አቋሞች (እምነቶች) መካከል የሚካሄድ ከፍተኛ ጦርነት አለ። አንደኛው የዓለም ሲሆን፣ ሁለተኛው የክርስትና እምነት አቋም ነው። ዓለም *"ሁልጊዜ ራስህን አስቀድም፤ የራስህን ፍላጎት አሟላ፤ ፍላጎትህን ለማሟላት በምታደርገው ትግል ሌላው ምን ይል ይሆን? ብለህ በማሰብ አትጨነቅ"* ይላል። የክርስትና እምነት ግን ራስህን ለእግዚአብሔር ሥልጣን አስገዛ፤ "አሽከር...ገረድ ወይም አገልጋይ ሁን" ይላል። ሁለተኛውን አቋም ለመያዝ ምርጫውን ያደረገ ማንኛውም አማኝ አስቀድሞ ማወቅ ያለበት እውነት ቢኖር፣ አንዳንድ ጊዜ መርጦ በያዘው አቋም ምክንያት በሌሎች መረገጥና መገፋት ሊደርስበት የሚችል መሆኑን ነው። ሉሲፋር የመጀመሪያውን ፍልስፍና በመምረጡና ራሱን ከፍ ለማድረግ በመሞከሩ፣ የእግዚአብሔር ጠላት ሆነ። ኢየሱስ ግን ሁለተኛውን በመምረጡ፣ የተሰቃየ የእግዚአብሔር በግ ሆነ፤ ዛሬ ግን የንጉሦች ንጉሥ ሆኖ ከብሯል።

ለአንድ አገር ወይም ሕብረተሰብ በጎነት፣ ባለሥልጣን መኖሩ ጠቃሚ ነው። መሪ ከሌለ ሕዝቡ በሥርዓት መሄድ አይችልም። ስለዚህ በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ዓለም መሪ አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ፣ መሪ እንዲሆንለት የሚፈልገው በው በኃይል

[20] Swindoll R. Charles. Improving Your Serve, World Publishing, Dallas, TX 1981.

የሚገዛውን ሳይሆን በትህትና የሚመራውን ነው። በየትኛውም ዓለም የአገልጋይ (የአሽከር) ልብ ያለውን መሪ መከተል የሚከብደው ሰው የለም። መሪውን ይከተላል በንል፣ የመሪው ባርያ ይሆናል ማለት እንዳልሆነ አንዳንድ በመሪነት ሥፍራ የተቀመጡ ሰዎች የተረዱት አይመስለንም። ተመሪው በፈቃደኝነት ራሱን ለመሪው ያስገዛል እንጂ፣ መሪው በኃይልና በሥልጣን አይገዛውም። ይህንንም ማድረግ የሚያስችለው ፍርሃት ሳይሆን ፍቅር ነው። በፍቅር ራሳቸውን ለጌታ ሙሉ በሙሉ የሰጡ ክርስቲያኖች፣ ግለኝነታቸውን (individuality) እያዳበሩ እግዚአብሔር እንዲሆኑ የሚፈልገውን ዓይነት ሰዎች ይሆናሉ። ለእግዚአብሔር ሥልጣን ራሳቸውን ተገዢ ማድረግን *"እምቢ!"* ያሉት ግን፣ ምን እንደሚሆኑና እንዲሁም እግዚአብሔር ምን እንዲሆኑ እንደሚፈልግ የተረዱ አይደሉም። በዓለም ዓይን ምንም ያህል ትልልቆችና አሸናፊዎች መስለው ቢታዩም፣ ራሳቸውን ካላስተካከሉ፣ በእግዚአብሔር ዓይን ሲታዩ እንደ ደካማዎች እንጂ እንደ ብርቱዎች ሆነው አይታዩም።

ዓለም የምትከተለው የአመራር ፍልስፍና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መግባት ሲጀምር፣ መንፈሳዊ መሪዎች እንደ ዓለማውያን ሥልጣናቸውን ያለአግባብ መጠቀም ይጀምራሉ። ከላይ የገለጽነው ዲዮጥራጢስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆንን ይችላል። የዲዮጥራጢስ መንፈስ በመካከላችን ሲፈጠር፣ አንድነታችን የተጠናከረ በመሆን ፈንታ የተከፋፈልን እንሆናለን። ቤተ ክርስቲያን መልካም ፍሬ የሚወጣባት በመሆን ፈንታ የጦር ሜዳ ትሆናለች። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጊዜያቸውን ፍሬ ባለው አገልግሎት ላይ በማዋል ፈንታ፣ ሥልጣናቸውን ለማስከበር ሲታገሉ፣ ለበጎ ነገር ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ኃይል ያለአግባብ ሲያባክኑት ይታያሉ። እርሱ በፈቀደው ዓይነት እንዲጠቀምብን ራሳችንን በትህትና ለጌታ ሙሉ በሙሉ ስንሰጥ፣ እርሱ በሚፈልገን ሥፍራ ሆነን ለማገልገል፣ እንዲሁም የአገልግሎትን ሸክም ለመሸከም አንፈራም፤ በሰወደፊቱም አንጨነቅም። ጳውሎስ በምን ዓይነት ሁኔታ ማገልገል እንዳለብን ሲገልጽ *"አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ፣ ለማንም ዕንቅፋት መሆን አንፈልግም። ይሁን እንጂ፣ በምናደርገው ነገር ሁሉ ራሳችንን እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች እናቀርባለን። የምናቀርበውም...በንጽህና፣ በዕውቀት፣ በትዕግስት፣ በቸርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ በእውነተኛ ፍቅር..."* ተሞልተን መሆን አለበት ይላል (2 ቆሮ. 6፥3-4፥ 6)። ራስን ለክርስቶስ ማስገዛት ማለት፣ እንድናገለግለው አደራ በሰጠን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንሰለጥንበታለን ማለት አይደለም። ጳውሎስ *"እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፤ እኛም ራሳችን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል"* (2 ቆሮ. 4፥5) በማለት አገልጋይ ምን ዓይነት አቋም ሊኖረው እንደሚገባ በግልጽ ይናገራል። የሚያሳዝነው አንዳንዶቻችን በክርስትና እምነት ብዙ ዘመን ብንኖርም፣ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ውብ የሚያደርገው "ትህትና" የማይታይብን መሆናችን ነው።



በትህትና ራስን ዝቅ ማድረግ የእውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ምልክት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆንን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ትህትና ሲጽፍ *"እንደ ሰው ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ."* አለ (ፊልጵ. 2፥8)። ኢየሱስ አምላክ ሆኖ *"ራሱን ባዶ አድርጎ እንደ ሰው ሥጋ ለብሶ በመካከላችን አደረ"* የሚለው ቃል፣ ኢየሱስ ምን ያህል ራሱን ዝቅ እንዳደረገ ያሳየን ይሆን? እኔና እናንተ ሰዎች ሆነን *"የውሻን አካል ይዛችሁ ውሻ ሁኑ"* ብንባል፣ ውሻ ዝቅተኛ እንስሳ መሆኑን ስለምናውቅ ውሻ ለመሆን ፈቃደኞች አንሆንም። "መልአክ ሁኑ" ብንባል ግን፣ ትልቅነት ስለሆነ፣ ደስታውን አንችለውም። ኢየሱስ ግን በማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ሆኖ፣ በሰማይ ያለውን ዙፋኑን ትቶ እንደ እኛ ሥጋ የለበሰ ሰው ሆኖ በመካከላችን መኖሩ፣ ምን ያህል ራሱን ዝቅ እንዳደረገ በመጠኑም ቢሆን መረዳት እንችላለን።

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት መካከል በጣም ያቀርባቸው የነበሩት፥ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ዘንድ አንድ ቀን አንድ ልመና ቀርቦለት ነበር። ***"መምህር ሆይ የምንለምንህን እንድታደርግልን እንፈልጋለን...በመንግሥትህ ክብር አንዳችን በቀኝህ፥ አንዳችን በግራህ እንድንቀመጥ ፍቀድልን አሉት"*** (የማር. 10፥35-37)። ፍላጎታቸው ኢየሱስ በመንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛውን የማዕረግ መቀመጫ ወይም ሥፍራ እንዲሰጣቸው ነበር። በሰው ግምት ዮሐንስና ያዕቅብ ጥያቄያቸውን ያቀረቡት በትክክለኛው ጊዜ ነበር። ይኸውም፥ ኢየሱስ የመጨረሻውን የመስቀል ሞት ለመሞት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በወሰነበት ጊዜ ነበር (የማር. 10፥32)። ዮሐንስና ያዕቆብ "የኢየሱስ መንግሥት መምጫ" እንደተቃረበ፥ የመስቀሉን የሞት ጽዋ ለመቅመስ የቆረጠ መሆኑን ተረድተዋል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ነገር ማብቃቱን የተገነዘቡ ይመስላሉ። ኢየሱስን እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ሲጠይቁት፣ የተቀሩት ደቀ መዛሙርት "ሳይቀድሙን እንቅደማቸው" በማለት አስበው ይሆናል። መጀመሪያ ላይ የሚፈልጉትን ሳይናገሩ *"መምህር ሆይ! የምንለምንህን እንድታደርግልን እንፈልጋለን"* ያሉት ለምን ይሆን? ጥያቄያቸውን በግልጽ ለማቅረብ አፍረው ይሆን? ሌሎች ደቀ መዛሙርት ይቀየሙ ይሆናል ብለው አስበው ይሆን? የዮሐንስና የያዕቅብ ሁኔታ ያስደንቀን እንጂ፥ ከሌሎች ሁሉ በልጦ መታየት፣ ሥልጣን መፈለግ የሰው ሁሉ ፍላጎት እንደሆነ የታወቀ ነው። ሰው መቅደም እንጂ መቀደም፥ አንደኛ መሆን እንጂ ሁለተኛ መሆን፣ መብለጥ እንጂ መበለጥ ማንም አይፈልግም። እርግጥ ነው እንደ ዮሐንስና ያዕቆብ "የክብር ወንበር እፈልጋለሁ" በማለት ፊት ለፊት የልቡን ገልጸ አይናገርም ይሆናል። ዮሐንስና ያዕቆብ የራሳቸውን ፍላጎት እንጂ፥ ጥያቄያቸው የተቀሩትን አሥሩን ደቀ መዛሙርት ያስቆጣ ወይም ያስቀይም ይሆናል ብለው ያሰቡበት አይመስለንም። ይሁን እንጂ፥ የዮሐንስና የያዕቅብ ጥያቄ የተቀሩትን ደቀ መዛሙርት በጣም እንዳስቆጣቸውና እንዳስቀየማቸው እናውቃለን (ማር. 10፥41)።

ኢየሱስ "ሐዋርያ" የሚለውን ቃል የተጠቀመበት፥ እርሱን እንዲወክሉት ለሰዎች ሥልጣን መስጠቱን የሚያሳይ ነው። ኢየሱስ *"...ቤቱን ለአገልጋዮቹ ትቶ ኢያንዳንዱን*

*አገልጋይ በሥራ ድርሻው ላይ አሰማርቶ በረኛው ነቅቶ እንዲጠብቅ አዝዞ የሄደውን ሰው ይመስላል"* (የማር. 13፥34) አለ። ደቀ መዛሙርቱን ሲልካቸው እንዲሁ ሳይሆን ኃይልና ሥልጣንን ሰጥቷቸው ነው (የሉቃ. 9፥11)። ስለ ታላቁ ተልኮም ኢየሱስ ሲናገር፥ *"...ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤ ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው፤ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ"* ይላል (የማቴ. 28፥18-20)። ጳውሎስም ሥልጣን ለምን እንደተሰጠው ምክንያቱ ሲገልጽ፣ *"ጌታ ስለ ሰጠን ሥልጣን በጣም ብመካም አላፍርበትም፥ ምክንያቱም ይህ ሥልጣን የተሰጠን እናንተን ለማነጽ እንጂ ለማፍረስ አይደለም"* ይላል (2 ቆሮ. 10፥8)። ጳውሎስ ቲቶን *"...በሙሉ ሥልጣንም ምከር፥ ገሥጽም፥ ማንም አይናቅህ"* ይለዋል (ቲቶ 2፥15)። የዕብራውያንን መጽሐፍ የጻፈው ጸሐፊም፥ *"ለመሪዎቻችሁ ታዘዙ፤ በሥልጣናቸውም ሥር ሁኑ፤ ምክንያቱም እነርሱ የሚጠየቁበት ኃላፊነት ስላለባቸው ስለ ነፍሳችሁ ጉዳይ ይተጋሉ፤ እናንተ ብትታዘዙአቸው፥ እነርሱ ሥራቸውን በደስታ ያከናውናሉ፤ ያለበለዚያ ሥራቸውን በሀዘን ይሠራሉ፤ ይህም እናንተን የሚጠቅም አይሆንም"* ይላል (ዕብ. 13፥17)።

በሁሉም ነገር ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የለም። ጲላጦስ ኢየሱስን *"...እኔ ልፈታህ ወይም ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን?"* (የዮሐ. 19፥10) ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጠው፥ *"ከእግዚአብሔር ሥልጣን ባይሰጥህ ኖሮ በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልኖረህ ነበር..."* አለው (የዮሐ. 19፥11)። መንፈሳዊ መሪ ሕዝቡን ለመምራት ሥልጣንን ያገኘው በራሱ ኃይልና ችሎታ ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር የተቀበለው ነው (የሐዋ. 1፥7-8)። መሪ ሕዝቡን እንዲመራ ኃላፊነት ተሰጥቶት፣ ሥልጣን ግን ባይኖረው ሕዝቡን እንደሚገባው መምራት አይችልም። እንዲሁም ኃላፊነት ሳይሰጠው ሥልጣን ብቻ ቢኖረው አገልግሎቱን እንደሚገባው መፈጸም አይችልም። ይሁን እንጂ፣ መንፈሳዊ መሪ እንዳይታበይ፣ የመሪነቱን ኃላፊነትና ሥልጣን ያገኘው በራሱ ጥበብና ችሎታ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መሆኑን ሁልጊዜ ማስታወስ አለበት። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎታቸው ዓይነት የተለያየ ይሁን እንጂ አማኞች ሁሉ በጌታ ፊት እኩል ናቸው። አማኞች ሁሉ እኩል ከሆኑ፣ መንፈሳዊ መሪዎች "ሥልጣን አላቸው" የሚለውን አሳብ መቀበል የሚያቅታቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እርግጥ ነው ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት እኩል ናቸው፤ ሁሉም አንድ ዓይነት አገልግሎት፣ እንዲሁም እኩል የሆነ ሥልጣን ግን የላቸውም። ሥልጣን አገልግሎቱን መፈጸም እንዲችል ለመንፈሳዊ መሪ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ነው። ከጌታ የተሰጠውን ሥልጣን በአግባቡ ካልተጠቀመበት፥ ኃላፊነቱን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዓይነት መወጣት አይችልም። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ መሪ ሥልጣን ሲሰጠው ከኃላፊነት ወይም ከተጠያቂነት ጋር ነው። ከእግዚአብሔር ከፍተኛ ሥልጣን



የተሰጣቸው መንፈሳዊ መሪዎች፥ በዚያው ልክ ትልቅ ኃላፊነት (ተጠያቂነት) ስላለባቸው አገልግሎታቸውን በጥንቃቄ መፈጸም አለባቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመንፈሳዊ መሪ ሥልጣን የሚሰጠው፣ እንዲከበርበት፣ የደሞዝ ጭማሪ እንዲያገኝበት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በጥሩ ሁኔታ መምራት እንዲያስችለው ነው። ከሚመራው ሕዝብ የሚሰጠውም አክብሮት፣ ሥልጣኑን እንደ ሹመት አይተው ሳይሆን፥ በሚሰጠው የጠራ አገልግሎትና ሕዝቡን እንዲመራ ከጌታ ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ ነው። ጳውሎስ *"ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚተጉ ሽማግሌዎች ዕጥፍ ክብር ይገባቸዋል"* ይላል (1 ጢሞ. 5፥17)።

## 2. "አገልጋይ-መሪነት" (Servant Leadership) ምንድነው?

*"አገልጋይ-መሪነት"* እነዚህ ሁለት ቃላት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በቀጥታ የተተረጎሙ በመሆናቸው፥ ሀሳቡን በደንብ ለመረዳት ትንሽ ያስቸግራል። በእንግሊዝኛ ቋንቋም ቢሆን እነዚህ ተቃራኒ የሆኑ ሁለት ቃላት አብረው ስለማይሄዱ፥ ትርጉሙ ብዙዎቻችንን ግራ እንደሚያጋባን ግልጽ ነው። *"መሪነት"* የሚለውን ቃል ስንሰማ ወደ አዕምሯችን ቶሎ የሚመጣው፥ በመሪነት ስፍራ የተቀመጠው ሰው ያለው ሥልጣን፥ ደረጃ፥ ትልቅነት፥ ተሰሚነት፥ የማዘዝ ችሎታውና እንዲሁም ያለው ኃይል ነው። "አገልጋይ" የሚለውን ቃል ስንሰማ ደግሞ፥ የሰውየውን ትልቅነት ሳይሆን ዝቅተኛነቱን ነው። መንፈሳዊ መሪ በአመራሩ የተሳካ ውጤት ለማግኘት ከላይ የዘረዘርናቸው ነገሮች ሁሉ ያስፈልጉታል ብለን እናምናለን። በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ መሪ ሁለት ዓይነት መልክ እንዳለው እናያለን። ይኸውም፥ "መሪ" እንዲሁም "አሽከር" መሆኑ ነው። መንፈሳዊው መሪ ከሌሎች የሚለይበት አንደኛው ይሄ ነው። ለመምራት ዝቅ ብሎ ማገልገል አለበት። መንፈሳዊ መሪ በሰዎች መካከል ወዳጅነት እንዲፈጠር፥ ሰዎች እርስ በርሳቸው ቅርበት እንዲኖራቸው፥ እንዲሁም ከሚመራው ሕዝብ መካከል ሰቶ የተገኘውን ፊት ለፊት በድፍረት መናገር የሚያስችል ባሕሪ ሊኖረው ይገባል። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ወይም መጋቢ ከላይ የገለጽነውን ማድረግ የሚችለው፥ "ዝቅ ብሎ እንደ አሽከር በማገልገል" እንጂ "ትልቅነቱን" በማሳየት አደለም። *"አገልጋይ-መሪ"* (Servant-Leader) ስንል፥ መንፈሳዊ መሪ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም ማለት አይደለም።

*"አገልጋይ-መሪ"* የሆነው ሰው ችሎታና ብስለት ብቻ ሳይሆን፥ "የአገልጋይነት" ባሕሪም ሊኖረው ይገባል። ችሎታና ብሰለት ኖሮት ዝቅ ብሎ እንደ አሽከር ማገልገል ካልቻለ፥ በበጎች ሕይወት ውስጥ የሚያመጣው መንፈሳዊ ለውጥ (ዕድገት) በጣም አነስተኛ ይሆናል። መጋቢ፥ ፍሬያማነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚለካው፥ በሚፈጽመው ወይም በሚያከናውነው ድርጊት ሳይሆን፥ በታማኝነቱ፣ በክርስቲያን ባሕሪውና በመንፈሳዊ ብስለቱ ነው። ከሰው ጋር ያለው ጥሩ ግንኙነት፥ ሥልጣኑን በአግባቡ ከመጠቀም ጋር አብሮ

መሄድ አለበት። ከሰዎች ጋር የሚኖረው ጥሩ ግንኙነት መሠረቱ፥ የሚመራቸውን ሰዎች፥ ክርስቶስ ራሱን በመስጠት እንዳገለገለው ሁሉ፥ እርሱም በእውነተኛ ልብ ሕዝቡን ማገልገል ሲችል ነው። መንፈሳዊ መሪ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትልቅ ኃላፊነት ለመወጣት፣ ከሕዝቡ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። የተቀራረበ ግንኙነትም ከሕዝቡ ጋር ሊኖረው የሚችለው፣ ክርስቶስ የራሱን ደቀ መዛሙርት ዝቅ ብሎ እንዳገለገላቸው፣ እርሱም ሕዝቡን በትህትና መንፈስ ማገልገል ሲችል ነው። ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ጎንበስ ብሎ ማጠብ፣ መንፈሳዊ መሪ የሚያገለግለውን ሕዝብ በምን ዓይነት ሁኔታ ማገልገል እንዳለበት ጥሩ መመሪያ ወይም ምሳሌ ይሆንለታል።

በዓለማዊ ድርጅት ውስጥ፣ ሠራተኛው በኃላፊነት የተሰጠውን ሥራ በጥራትና በትጋት መሥራቱን ለሚመለከታቸው ወይም ለአለቆቹ ማሳየት አለበት። መንፈሳዊ መሪ ግን ትልቅነቱ የሚለካው ተልቆ በመታየት "ይህን ሠራሁ... ይህን አደረግሁ" በማለት ሳይሆን፥ ዝቅ ብሎ እንደ አሽከር በማገልገል ነው። ማወቅ ያለብን እውነት ቢኖር፣ እግዚአብሔር ትኩረት የሚሰጠው ዝቅ ብለው የሚያገለግሉትን እንጂ፥ ለሰው ዓይን ጎልተው የሚታዩትን አለመሆኑ ነው። መንፈሳዊ መሪ አገልግሎቱን ፍሬያማ ማድረግ የሚችለው፥ በቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ ሲይዝ ሳይሆን፥ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለመንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ ነው። ማንኛውም መንፈሳዊ አገልጋይ የአገልግሎቱን ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚጥረው ለምንድን ነው? እግዚአብሔርን ለማክበር ነው? ወይስ ለራሱ ስምና ዝና ሲል ነው? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ልቡን በጥንቃቄ መመርመር አለበት። በመንፈሳዊ አገልግሎት እጅግ በጣም ጥሩ አገልግሎት መስጠት፥ በቤተ ክርስቲያን ወይም በመንፈሳዊ ድርጅት ውስጥ በአመራር ሥልጣን ውስጥ ከፍ ወዳለው ደረጃ ማደግ ሳይሆን፥ አገልጋይ (አሽከር) ሆኖ ወደ ታች ዝቅ በማለት ነው። "መሪ መሆ ንና" እንዲሁም እንደ አሽከር ሆኖ ማገልገልም እንዴት ይቻላል? በአንድ ጊዜ መሪና እንዲሁም አገልጋይ (አሽከር) መሆን፥ መንፈስ ቅዱስ ካላስቻለ በስተቀር ቀላል አይደለም።

## 3. "አገልጋይ-መሪ" ሊኖረው የሚገባ ባሕሪ

ኢየሱስ ለሦስት ዓመት ተኩል በቃልም ሆነ በምሳሌነት ያስተማራቸው አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ነበሩት። ዓላማውም ከእርሱ የተማሩትን ለሌሎች እንዲያስተምሩ ነበር። እነዚህ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሁሉም የራሳቸው የሆነ የተለያየ ባሕሪ ነበራቸው። አንዳንዶቹ በጣም አስቸጋሪ የተፈጥሮ ባሕሪ ነበራቸው። ከነዚህ ውስጥ በጣም ጎልቶ የሚታየው ጴጥሮስ ነው። ጴጥሮስ ብርቱ ጎን ነበረው። በሰው ዓይን ሲታይ ጴጥሮስ ለአገልግሎቱ ደከመኝ የማይል፥ ንቃት ያለው፥ ምንም ዓይነት ሥራ ቢሰጠው ኃላፊነቱን እስከ መጨረሻው ድረስ የሚፈጽም፥ በብዙ ነገር ዘላቂና ታማኝ፥ የማሰብ ችሎታው



ከፍተኛ የሆነ፥ መልካም አስተሳሰብ የነበረው፥ ተምሮ ማደግ የሚችል፥ ራዕይ ያለው፥ ላመነበት የተሰጠ፥ የመሪነት ተሰጦ የነበረው ታላቅ ሰው ነበር። ጴጥሮስ ብርታት ብቻ ሳይሆን ብዙ ድካሞችም ነበሩበት። ሲበዛ ትምክህተኛነት ያጠቃው ነበር። ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፥ "ከሌሎች ደቀ መዛሙርት የተሻልኩ ነኝ" ብሎ የሚያስብ ሰው ይመስላል። ሌላው ቀርቶ የክርስቶስ አሳብ ከእርሱ አሳብ ጋር የማይሄድ ሆኖ ሲያገኘው፥ ኢየሱስን እንኳን ለማረም ወይም ለማስተካከል ድፍረት የነበረው ሰው ነበር። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ስለሚደርስበት መከራና ሞት ለደቀ መዛሙርቱ ሲነግራቸው፥ ጴጥሮስ "***ጴጥሮስ ለብቻው ገለል አድርጎት 'እንዲህ አትበል' ሲል ገሠጸው***" (የማር. 8፥32)። ጴጥሮስ ራሱን ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርቱ የተሻለ አድርጎ የሚያይና የሚያሳይ ሰው እንደነበረ የምንገነዘበው ደግሞ፣ ኢየሱስ "***ሁላችሁም ትክዱኛላችሁ፤ ትታችሁኝም ትሸሻላችሁ***" (የማር. 14፥27) ሲል፥ ጴጥሮስ "***...ሌሎች ሁሉ እንኳ ቢክዱህ እኔ ከቶ አልክድህም***" (የማር. 14፥29) ሲል ጴጥሮስ በትምክህት ተሞልቶ የተናገረውን ስንሰማ ነው። ኢየሱስ እንደ ጴጥሮስ ዓይነቱን ሰው ይይዝ የነበረው በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር? ጌታ ኢየሱስ የጴጥሮስን ድካም ብቻ ሳይሆን፣ የልቡን ቅንነትና እውነተኛነትንም ያውቅ ነበር።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጴጥሮስን ዓይነት አስቸጋሪ ባሕሪ ያላቸው ሰዎች ሞልተዋል። በሥራ ቅልጥፍናቸው እንከን የማይወጣላቸው ናቸው። የሚሰጣቸውን ኃላፊነት የሚወጡት ወይም የሚሠሩት ከሚጠበቅባቸው በላይ እጅግ በጣም ጥሩ አድርገው ነው። በብዙ መንገድ እምነት የሚጣልባቸው ናቸው። አዲስ ነገር ለመማር ጊዜ አይፈጅባቸውም። የሚሰጣቸውን አገልግሎት ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ይሰጣሉ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ባለው ራዕይ የሚያምኑና የሚተባበሩ ናቸው። ሌሎችን የመሳብ ኃይል፥ እንዲሁም መሪ የመሆን ብቃት ያላቸው ናቸው። በሌላ ወገን ግን፥ ጎልቶ የሚታይ ችግር ያለባቸው ናቸው። በራሳቸው በጣም የሚታመኑ በመሆናቸው፥ መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) የተሳሳተ ከመሰላቸው ፊት ለፊት የሚቃወሙ ናቸው። የአገልግሎት ባልደረቦቻቸውን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል የሚፈልጉ፥ የአለቅነት ስሜት ያላቸው፥ በሁሉ ነገር ቀደም ቀደም የሚሉ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚጠቅመውን ሳይሆን፥ የእነርሱን አሳብና ፍላጎት ብቻ እንዲሟላ የሚፈልጉ፥ ስሁተት ሲሠሩ መታረም የማይፈልጉ አስቸጋሪ የተፈጥሮ ባሕሪ ያላቸው ምዕመናን አሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ቤተ ክርስቲያንን በሽምግልና፥ በድቁና ወይም በልዩ ልዩ አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ሊሆኑ ይችላሉ። መንፈሳዊ መሪው (መጋቢው) እንደ እነዚህ ዓይነቶቹን መያዝ ያለበት በምን ዓይነት ሁኔታ ነው? ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ቢሆኑም፣ ከመሪው ለመማርም ሆነ መመሪያ ለመቀበል ፈቃደኞች ስላልሆኑ፣ በምን ዓይነት ሁኔታ ሊይዛቸው ይገባል? ሌሎች ደግሞ የራሳቸውን አሳብ ብቻ እየተከተሉ፣ ሁልጊዜ የመሪውን አሳብ የሚቃረን አሳብ የሚለነዝሩትን ምን ያህል ጊዜ ሊታገሳቸው ይገባል? "ችላ ብዬ ባልፋቸው ሁኔታ

ቸው ይለወጣል" በማለት ይተዋቸው? ንቆ ቢተዋቸው ሁኔታቸው በእርግጥ ይለወጣል? ከያዙት አገልግሎ ያስወጣቸው? ወይስ ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ማገልገል አልችልም ብሎ መንፈሳዊ መሪነቱን (መጋቢነቱን) ይተው?

ለማንኛውም ነገር ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ለአገልግሎት ከሚያዘጋጃቸው ደቀ መዛሙርት መካከል በችኩልነቱ ምክንያት አስቸጋሪ የሆነው ሰው ጴጥሮስ ነበረ። እኔና እናንተ ብንሆን ጴጥሮስን ወዲያው እናባርረው ነበር፤ ወይም ለእርሱ ስንል አገልግሎታችንን ትተን እንወጣ ነበር። ስለ "አገልጋይ-መሪነት" ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን፥ ክርስቶስ ነው። እውነተኛ ትህትና ምን እንደሆነ በተግባር ሊያስተምረው የፈለገው ክርስቶስ፣ የጴጥሮስን እግር ለማጠብ ሳህን ይዞ ከእግሩ ሥር ተንበረከከ። ይሁን እንጂ ሌሎች ደቀ መዛሙርት ሁሉ "እሺ!" ብለው ሲታጠቡ ጴጥሮስ ብቻ "እምቢ! አንተ የእኔን እግር አታጥብም" አለው (የዮሐ. 13፥1-17)። በዚህ ዓይነት እምቢተኛነቱ ለማሳየት የሞከረው፣ እግራቸውን ኢየሱስ እንዲያጥባቸው ያደረጉት ደቀ መዛሙርት ትክክለኛ አለመሆናቸውን ለማሳየት የሞከረ ይመስላል። ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ የነበረው ስሜት ለመሆኑ ምን ዓይነት ነበረ? ከዚህ ውስጥ ምን እንማራለን? ኢየሱስ ለጴጥሮስ የነበረው ስሜት፥ እኛ "አስቸጋሪ ናቸው" ለምንላቸው ሰዎች ከሚኖረን ስሜት በምን ይለያል? ከተለየ ምክንያቱ ምን ይሆን? ስሜታችን መለወጥ ካለበት፥ እንዴት መለወጥ እንችላለን? ኢየሱስ የጴጥሮስን ሕይወት ለመለወጥ የወሰደው እርምጃ ምንድነው? ኢየሱስ ካደረገው ውስጥ "አመራራችን" ውጤታማ እንዲሆን ምን ዓይነት ትምህርት እናገኛለን? ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር እንዳጠበው፥ መንፈሳዊ መሪ የሚያገለግላቸውን ሰዎች እግር ማጠብ አለበት የሚለውን አሳብ እንዴት እንቀበለዋለን? በምን ዓይነት ሁኔታ ነው መሪው ማገልገል የሚችለው? እንዲሁም በምን ዓይነት ሁኔታ ነው "አሽከር የሆነው አገልጋይ" መምራት የሚችለው? ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መልስ እንፈልጋለን።

ኢየሱስ "መሪ፥ ጌታ፥ አለቃ" ቢሆንም የጴጥሮስን እግር ጎንበስ ብሎ አጠበ። ልክ እንደዚሁ መንፈሳዊ መሪ፥ ሕይወቱ በኃጢአት የቆሸሸበትን አስቸጋሪ ሰው፥ ከኃጢአቱ ነጽቶ አገልግሎቱን መቀጠል እንዲችል በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዲነጻ ጥረት ማድረግ አለበት። ቃሉን የሚጠቀምበት ሰውየው ተለውጦ እርሱን እንዲመቸው፥ አስቸጋሪ እንዳይሆንበት ሳይሆን፥ ጌታውን በንጹህ ልብ ማገልገል እንዲችል ለማድረግ መሆን አለበት። "አገልጋይ-መሪ" የሚያገለግላቸው ሰዎች የቆሸሸው እግራቸው ነጽቶ ከክርስቶስ ጋር በነጻነት መራመድ እንዲችሉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት። ጴጥሮስ ኢየሱስን "አንተ አታጥበኝም" እንዳለው፥ አሁንም አንዳንድ ምዕመናን፥ "መታጠብ፥ መንጻት አልፈልግም" በማለት የሚያስቸግሩ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። እንዲህ ዓይነት "አስቸጋሪ ባሕሪ" ያላቸውን ሰዎች "አገልጋይ-መሪ" ሊረዳቸው የሚችለው በምን ዓይነት ሁኔታ ነው?



## 3.1. "አገልጋይ-መሪ" በፍቅር ተሞልቶ ያገልግል

ኢየሱስ ወደ መስቀል ሞት የሚሄድበት ጊዜ በተቃረበበት በመጨረሻዋ ጊዜ እንኳን ለደቀ መዛሙርቱ ያለውን ፍቅር፣ በሚገባቸው ቋንቋ ይገልጽላቸው ነበር። ይሄ የኢየሱስ ፍቅር የማይለወጥ መሆኑን ዮሐንስ ሲገልጽ፣ *"...በዚህ ዓለም ያሉትን የራሱን ወገኖች ሁልጊዜ ወድዶአቸው ነበር፤ እስከ መጨረሻም ወደዳቸው"* (የዮሐ. 13፥1) ይላል። ኢየሱስ እንደሚታሠር፥ እንደሚገረፍ፥ እንደሚፈረድበት፥ በመጨረሻም እንደሚሰቀል ቢያውቅም፣ በራሱ መከራና ጭንቀት ላይ በማተኮር ፈንታ፣ ትቷቸው ስለሚሄደው ደቀ መዛሙርቱ በጣም ያስብና ይጨነቅ ነበር። በዚህም ኢየሱስ የራሱ የሆኑትን እስከ መጨረሻ ይወድዳቸው እንደነበረ መረዳት እንችላለን። በጣም ስለ ወደዳቸው፣ ዓለምን የፈጠረ ታላቅ ጌታ ቢሆንም፣ ለደቀ መዛሙርቱ ፍቅሩን ለመግለጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደ አሽከር እግሮቻቸውን አጠበ። በኢየሱስ ሕይወት የተፈጸሙት ነገሮች ሁሉ በፍቅሩ ምክንያት የደረሱ ናቸው። ደቀ መዛሙርቱ ከምንጊዜውም የበለጠ በሚያስፈልጉት አስጨናቂ ጊዜ ጥለውት እንደሚሸሹና አንዳንዶችም እንደሚክዱት ቢያውቅም፥ ለእነርሱ የነበረው ፍቅር አልተለወጠም ነበር። የክርስቶስን የእግር ማጠብ አርአያ የተከተሉ "አገልጋይ-መሪዎች" ክርስቶስ እነርሱን እንደወደዳቸው፣ ዝቅ ብሎ እነርሱን በማገልገል ፍቅሩን እንደገለጠላቸው፣ እነርሱም የሚያገለግሏቸውን ሰዎች ትህትና በተሞላው አገልግሎታቸው ፍቅራቸውን መግለጽ አለባቸው። የአገልግሎታቸውም ውጤት የሚለካው፣ ክርስቶስ እንደወደዳቸው፣ እነርሱም ለሚያገለግሏቸው ሰዎች በሚያሳዩት የፍቅር መግለጫ ነው።

## 3.2. "አገልጋይ-መሪ" የሚያገለግላቸውን ሰዎች ዝቅ ብሎ ያገልግል

ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ትልቅ ትምህርት ሊያስተምራቸው ፈልጎ፣ የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ተነሳ።

የእግዚአብሔርን ክብር ያልተሻሙ አገልጋዮች አሉ። ኢየሱስ ከሁሉም የሚበልጥ ጥሩ ምሳሌያችን ነው። ፍጹም ራሱን ለአባቱ ሰጠ። ራሱን ባዶ አደረገ። የሚያደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር አደረገ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በ3 ዓመት ተኩል የአገልግሎት ዘመኑ ብዙ ነገር አስተምሯቸው ነበር። የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፥ መሲህነቱን፥ አስደናቂ ኃይል እንዳለው ያስተማራቸውን ሁሉ አውቀዋል። የመጣበትን ዓላማ ጨርሶ ሊመለስ ጥቂት ሲቀረው ደቀ መዛሙርቱ አንድ በደንብ ያልገባቸው ትልቅ ነገር እንዳለ ተረዳ። ያም የመጣው ጌታ ለመሆን፥ ሥልጣን ለመያዝ፥ በሰዎች ላይ ለመሰልጠን፥ የክብር ጥማት ኖሮበት እንዳልሆነ በደንብ የገባቸው አልመሰለውም። ይህ እውነት ቢገባቸው ኖሮ እርሱን ለመምሰል ይሞክሩ ነበር። "እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሁት ነኝ.." ይላል። እነርሱ ግን "ከእኛ መካከል ትልቁ ማን ነው?" እያሉ እርስ በርሳቸው

ይከራከሩና ይጋጩ ነበር። ይህን ትልቅ ትምህርት በንግግር ብቻ ከማስተማር በተግባር ለማሳየት በለፈለገ *"የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብና በታጠቀበት ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ..."* ይላል (የዮሐ. 13፥1-5)። ኢየሱስ ይህን ሲያደርግ በዚያን ዘመን የነበረውን ደንብና ሥርዓት መጣሱ ነበር። በአይሁድ ባህል፣ በፋሲካ እራት ላይ እንግዳ የሆነ ሰው፣ ለመገልገል ከተቀመጠበት መነሳት የለበትም። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በዚያን ወቅት እንግዶች ስለነበሩ፣ ተቀምጠው መገልገል እንጂ፣ ማገልገል አልነበረባቸውም። የፋሲካ እራት አዘጋጅቶ ማቅረብ፥ በአምልኮት መምራት፥ የፋሲካ እራት ምን እንደሆነ ተጋባዦቹ እንዲያውቁት ማድረግ የቤቱ ባለቤት፥ ወይም ግብዣውን ያዘጋጀው ሰው ኃላፊነት ነበር። ኢየሱስ ግን በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነውን ትምህርት እንዲማሩ ስለፈለገ፣ ከባህሉ ውጪ የሆነ ነገር አደረገ። የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ከተቀመጠበት ተነሳ።

በአይሁድ ባህል የእግር ማጠብ ሥራ የሚሰጠው ከቤቱ ውስጥ ዝቅተኛ ለሆነው ሰው ነው። ይኸውም፣ ለአሽከር፥ ለገረድ ወይም ለባሪያ ነው። ከሌለ የመጨረሻው ዝቅተኛ ነው የተባለው ሰው የሚሠራው ሥራ ነው። ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ትንሹ ማን ነው? እግር ማጠብ ያለበት ከእነርሱ መካከል ማን ይሆን? ጴጥሮስ፥ ዮሐንስ፥ ያዕቆብ.. ለክርስቶስ ቅርብ ስለሆኑ አንጋፋዎች ናቸው። ይሁዳ እስቆሮቱም እንኳ ትልቅ ኃላፊነት ነበረው። ስው ከጠፋ ኢየሱስ መልእክትን መጥራትና ማሳጠብ ይችል ነበር። አሽከሮችና ባሮችን መቅጠር ይችል ነበር። ትልቅነት የሚገኘው ዝቅ ብሎ ትልልቆችን በማገልገል ሳይሆን ትናንሾችን በማገልገን እንዲሚገኝ ሊያስተምራቸው ፈልጎ ነው ራሱ እግር ለማጠብ ከተቀመጠበት የተነሳው። በማር. 10፥44 ላይ *"ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ ሁሉ ባሪያ ይሁን..."* ብሎ በቃል ያስተማራቸውን በተግባር ለማሳየት ነው። የእግዚአብሔርን ክብር ካልተሻሙት ሰዎች መካከል ሌላው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። ብዙ ሊያበመካው የሚችል ነገር ቢኖረውም፥ "ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ የምመካበት ነገር የለኝም" አለ። በአገልግሎት ውስጥ ፍሬ ቢስ የሚያደርገን አንደኛውን ትልቁ ምክንያት የእግዚአብሔርን ክብር የምንሻማ ስንሆን ነው። የተሰቀለ የግል ሕይወት ከሌለን፣ ትንባኤ ያገኘ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር አንችልም። ትንባኤ ያላገኘ ሕይወት ይዞ የሚያገለግል አገልጋይ፥ ፍሬ ቢስ ነው። እግዚአብሔርን ብቻ የሚያከብር፥ ለራሱ ፍላጎት፥ ለራሱ ክብር የሞተ ነው። ለራሱ ፍላጎትና ክብር የሞተ ሰው፣ ለጥቅሙ ሲል ከማንም ጋር አይጋጭም።

እኔና እናንተ ከወንጌሉ ውስጥ የሚቆረቁረን፥ የማይታኘከልን፥ እንዲሁም የማይዋጥልን፥ በተግባር ማዋል ያቃተን፥ በልባችን ውስጥ ሥፍራ ያልሰጠነው መልዕክት ቢኖር *"ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ ሁሉ ባሪያ ይሁን..."* (ማር. 10፥44) የሚለው ቃል ነው። በሚያስደንቅ ጥበብና ኃይል ተሞልተን የእግዚአብሔርን ቃል በሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ ልብን የሚያንቃንቅ ስብከት ብንሰብክ፥ ውብ በሆነው ድምጻችን እንደ



መላእክት በመዘመር ብዙዎችን ወደ ጌታ ዙፋን ማቅረብ ብንችል፥ ጉልበታችን መጅ እስኪያወጣ ድረስ ተንበርክከን ብንጸልይ፥ በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ንብተን ቀንና ሌሊት ያለመታከት ብንለፋ፥ የለበስነውን እውልቀን እስከ መስጠት ድረስ ለጋስች ብንሆን፥ ትሁት መንፈስ፥ የተዋረደና የተሰበረ ልብ ከሌለን፥ ድርጊታችን የእግዚአብሔርን ክብር የሚሸፍን፥ ራሳችንን የምናስቀድም ከሆነ ፍጹም ዋጋ የለንም። ሰው እርስ በርሱ የሚጋጭበት ዋናውና ትልቁ ምክንያት፥ *"እኔ ያልኩት ትክክል ነው፥ የእኔ አሳብ ከሁሉም ይበልጣል፥ ወይም ይሻላል"* በማለት ነው። ባልና ሚስትም እልፍ እልፍ የሚጋጩበት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት ሁለቱም *"እኔ ያደረግሁት፥ እኔ ያሰብኩት ትክክል ነው። የእኔ አሳብ፥ የእኔ መንገድ፥ የእኔ ምርጫ ይበልጣል"* ብለው ስለሚያስቡ ነው። ልጆችም ከወላጆቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግጭት አንደኛው ምክንያት ይሄው ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን "ልክ አይደላችሁም...ተሳስታችኋል" ሲሏቸው፥ ልጆች ደግሞ ወላጆቻቸውን የዘመኑን ወይም የጊዜውን ነገር እናንተ አታውቁትም፤ እኛ ነን የምናውቀው" ይሏቸዋል። ሁሉም የራሱን ፍላጎትና ፈቃድ ስለሚያስቀድም በሰዎች መካከል ግጭት ይፈጠራል። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ስንወጣም፣ በግልጽ አንናገረው እንጂ የምናስተላልፈው መልዕክት፣ "እግዚአብሔር ሆይ! ስለ ግል ሕይወቴ ከአንተ የበለጠ እኔ አውቃለሁ" ማለታችን ነው። ለመሆኑ በዚህ አቅጣጫ እግዚአብሔር ለሰው ያለው ፈቃድና ዓላማ ምንድነው? ነብዩ ሚልክያስ ምን እንደሆነ ሲገልጽ፥ *"እግዚአብሔር ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድርነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ፥ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?"* ይላል። ዛሬ ብዙዎቻችን የጎደለን፣ ከአምላካችን ጋር በትህትና መራመድ፣ በእኛ ኃላፊነት ሥር ያለውን ሰው በትህትና የማገልገል ልብ ነው።

ብዙዎቻችን መቅደም እንጂ መቀደም፣ አንደኛ እንጂ ሁለተኛ፣ ዋና እንጂ ምክትል መሆን አንፈልግም። ሁልጊዜ የበላይ መሆን ስለምንፈልግ ም/ፕሬዚዳንት፥ ም/ድሬክተር ሥልጣኑ ከፍተኛ ቢሆንም፥ በምክትልነት ደረጃ ደስ ብሎን መቀጠል አንፈልግም። በስፖርት ዓለምም ቢሆን ዋና ተጫዋች እንጂ፥ ተጠባባቂ መሆን አንፈልግም። ማናችንም ብንሆን ተልቀን እንጂ አንሰን፥ አንደኛ ሆነን እንጂ ሁለተኛ ሆነን መታየት አንፈልግም። የሚያሳዝነው፥ መሆን የምንፈልገውን መሆን ሲያቅተን፥ ያልሆንነውን ሆነን ለመታየት፥ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን ስንዋሽ ትንሽም ቅር አይለንም። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር እንዲያየን፥ እንዲጠቀምብን "ትልቅ" መሆን አያስፈልገንም። መዘመር የሚችሉ፥ ጥሩ ዜማ የሚወጣቸው ትናናሽ ወፎች እንደሆኑ ታውቃላችሁ? በድምጻቸው የሚያስደስቱን ኢግል፥ (ንስር) ወይም ሰጎን የተባሉት ታላላቅ ወፎች አይደሉም። በመንፈሳዊ ሕይወትም "ማን እንደኛ አለ!" የሚሉ፥ ትልቅነታቸውን የሚያውጁ አይደሉም። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ትልቅነታቸውን የሚያውጁ ጥሩ መንፈሳዊ ዜማ የሚወጣቸው፥ መልካም የሕይወት ሽታ ያላቸው አይደሉም። ጥሩ መንፈሳዊ ዜማ (መዝሙር) የሚወጣቸው፥ ራሳቸውን አንደኛ ያደረጉ፥ ያልሆኑትን "ሆንን" ያላደረጉትን "አደረግን" የሚሉ፥

ምክንያት ፈልገው ስለራሳቸው የሚያወሩና የሚያስወሩ፥ ለመቅደም የሚታገሉ፥ ሲያቅ ታቸው የሚጠልፉ ሳይሆኑ፥ የሆኑትን ሆነው የተገኙ ብቻ ናቸው። ዲ. ኤል ሙዲ፥

> *"ክርስቲያን እያደገ መሆኑን የማውቅበት መንገድ አለኝ። ይኸውም፥ ጸጋ እየበዛለት ሲመጣ፥ ጌታውን ከፍ ከፍ ያደርጋል። ስለሠራው ሥራ ማውራቱ ይቀንሳል፤ ራሱንም እያሳነሰ ይመጣል። እንደ ጥዋት ኮከብ (morning star) ይሆናል። ማለትም፥ ኮከብ ጸሀይ መውጣት ሲጀምር፥ ብርሃኗ እየተደበቀ (እየደበዘዘ) ይመጣል" አለ።*

ከብዙ ዓመት በፊት ጆን ኒውተን የተባለ አንድ እንግሊዛዊ ሰው ነበር። ባሪያዎችን በሰንሰለት እያሠረ የሚሸጥ፥ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን በዎች እንደ ዕቃ የሚገዛና የሚለውጥ ክፉ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ፥ ሰው ስለ እርሱ መልካም ነገር የማያወራለትን፤ በሰው ዘንድ መመረጥ የማይችለውን ጆን ኒውተንን አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ አገኘውና እውነተኛ የሕይወት ለውጥ ሰጠው። እንዲሁም፥ ታላቅ ሰባኪና የታወቀ የኪነ ጥበብ ምሁር ለመሆን በቃ። ዘመኑን ጨርሾ ለመሄድ በሞት አልጋ ላይ በነበረበት ወቅት፥ አንድ ወጣት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረ ሰው ሊጠይቀው መጥቶ እንዲህ አለው። "አንተን የመሰለ ታላቅ መንፈሳዊ መሪ፥ ጠቃሚ አገልጋይ ማጣት ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ ጉዳት ነው" አለው። ጆን ኒውተንም ሲመልስለት፥ *"እርግጥ ነው ከአንተ ቀድሜ መሄዴ ነው። አንተም እኔ ከምሄድበት ሥፍራ መምጣትህ አይቀርም። ስትመጣም፥ ባለን መቀራረብ የተነሳ የት እንዳለሁ እንደምትፈልገኝ እርግጠኛ ነኝ። የምታገኘኝም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ተቀምጬ ሳይሆን፥ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ ከነበረው ወንበዴ እግር ሥር ተቀምጬ ነው"* አለው። ጆን ኒውተን ይህን ማለት የቻለው፥ ራሱን እንደ ታላቅ አገልጋይ ሳይሆን ከወንበዴዎች ሁሉ ያነሰ፥ በክርስቶስ ጸጋ ብቻ የዳነ መሆኑን በመረዳቱ ነው። ኤፍ. ቢ. ማየር የተባለ ክርስቲያን ጸሐፊ፥

> *"የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ስጦታዎች መደርደሪያ ላይ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርቦ የተቀመጠ፥ ወደ ላይ ባደግን ቁጥር በቀላሉ የምንደርስባቸው ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ስጦታዎች ወደ ላይ በመቆለል የተቀመጡ ሳይሆን፥ ዝቅ ብለው የተደረደሩ ስለሆኑ፥ ዝቅ ባልን ቁጥር እነዚህን ስጦታዎች የበለጠ ማግኘት እንደምንችል ተረዳሁ" አለ።*

"እግዚአብሔር እንዲጠቀምብን ከፈለግን ልንተልቅበትም ሆነ ልናንስበት አንችልም። ውስጣችንን መርምሮ፤ እውነተኛውን ማንነታችንን አውቆ ለክብሩ ይጠቀምብናል። አይሁዳውያን ባለሥልጣኖች ከኢየሩሳሌም ካህናትና ሌዋውያንን ወደ ዮሐንስ ልከው *"አንተ ማን ነህ?"* ብለው ጠየቁት። *"መሲሁ ነህ?"* አሉት። *"እኔ መሲሁ አይደለሁም"* አላቸው። *"ኤልያስ ነህ?"* አሉት። *"አይደለሁም"* አላቸው። *"ከነቢያቶች መካከል አንዱ ነህ?"* ብለው ጠየቁት። *"...እኔ በበረሓ የሚጮኽ ድምጽ ነኝ"* አላቸው። *"ድምጽ"* መልክና ቅርጽ የለውም፤ *"ድምጽ"* ለዐይን ደምቆና ጎልቶ አይታይም። ድምጽ አይጨበጨብለትም፤ ድምጽ መዳልያ አይደረግለትም። መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ራሱ ይህን ሲል፥ *"የማልታይ፥ ከፍተኛ ቦታ ሊሰጠኝ የማልገባ ሰው ነኝ"* ማለቱ ነው። ራሱን ዝቅ፤ ጌታውን ከፍ ለማድረግ ***"...እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፤ እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው አላቸው"*** (ዮሐ. 1፥26-27)። *"የአግሩን ጫማ ማሰር የማልችለውን እኔን ሳይሆን፥ ከእኔ የሚበልጠውን፥ በእሳት የሚያጠምቀውን ታላቁን መሲህ ብቻ ተመልከቱ፤ እርሱን ብቻ አድንቁ"* ማለቱ ነበር።



መሪም–አገልጋይም ከነበሩት መንፈሳዊ አባቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ ዮሐንስ መጥምቁ ነው። በተፈጥሮ ባህሪው፥ በቅድስና ሕይወቱ ተደናቂነት ያተረፈ ቢሆንም፥ ትልቅነቱን አላወጀም። የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ እንዲል፥ ጎልቶ እንዲታይ ዮሐንስ መጥምቁ፥ ዝቅ ማለት እንዳለበት የተገነዘበ ሰው ነበር። ለዚህ ነው ***"እርሱ ከፍ ከፍ እንዲል እኔም ዝቅ ዝቅ እንድል ያስፈልጋል"*** ያለው (የዮሐ. 3፥30)። ዮሐንስ መጥምቁ ከራሱ የተላቀቀ እንጂ በራስ ላይ ያተኮረ ሕይወት የነበረው ሰው አልነበረም። "የእኔ ነው" የሚለው ሀብት፥ ንብረትና ቤት አልነበረውም፤ በምድረ በዳ የሚኖር፥ ልብሱ ከግመል ጠጉር የተሠራ፥ ምግቡ አንበጣና የበረሓ ማር ነበር። ለተጠራበት አገልግሎት ራሱን የሰጠ፥ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን መልዕክት በቀጥታና ማንንም ሳይፈራ ፊት ለፊት የሚናገር መልዕክተኛ ነበር። ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት በማግባቱ፥ ወህኒ ቤት ሊጥለው፥ በሰይፍ ሊያርደው እንደሚችል እያወቀ፥ ሄሮድስን ፊት ለፊት "የወንድምህን ሚስት ማግባትህ ልክ አይደለም" ብሎ የተናገረ ደፋር ሰው ነበር። ዮሐንስ እውነተኛ ማንነቱን የተረዳ፥ ወደዚህ ዓለም ለምን እንደ መጣ ያወቀ ሰው ነበር። "እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች" እያለ በመስበክ የሕዝቡን ልብ ለመሲሁ ለማዘጋጀት ብቻ እንደተላከ የተረዳ ሰው ነበር። ዮሐንስ መጥምቁ ታዋቂ የሆነው በራሱ ኃይልና ዝና ሳይሆን፥ እውነተኛውን መሲህ ከራሱ የበለጠ ከፍ አድርጎ ለዓለም በማሳየቱ ብቻ ነው። ኢየሱስም ስለ ዮሐንስ መጥምቁ ትልቅነት ሲመሰክር፥ ***"በምድር ላይ ከተወለዱት ሰዎች ሁሉ ከዮሐንስ የሚበልጥ ከቶ ማንም የለም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ ያነሰ ይበልጠዋል"*** አለ (የሉቃ. 7፥28)።

ብዙዎቻችን ትልቁ ችግራችን፥ ትክክለኛውን ማንነታችንን አለማወቃችን ነው። በጸጋው ብቻ የዳንን ኃጢአተኞች መሆናችንን እንዘነጋለን። ብዙዎቻችን ራሳችንን በትክክል ማየት አንችልም። የሌላው ጉድፍ እንጂ የራሳችን ጉድፍ አይታየንም። የሌሎች ድካም እንጂ የራሳችን ድካም አይታየንም። የሌሎች ውድቀት እንጂ የእኛ የሕይወታችን መሻገት አይታየንም። አንዳንዶቻችን ራሳችንን ብናይም፥ የምናየው አጉልቶ በሚ

ያሳይ መነጽር ስለሆነ፥ የሚታየን ቁመታችን ረጃጅም ሆኖ፥ ከሁሉም ልቀን (በልጠን) ነው። የቤተ ክርስቲያን ምሰሶዎች የሆንን መስሎ ይታየናል። ቤተ ክርስቲያን ያለ እኛ የምትቆም አይመስለንም። ያልሆንነውን "ነን"፥ ያላደረግነውን "አደረግን" ያልሰማነውን "ሰማን"፥ ያልታየንን "ታየን" በማለት ራሳችንን፥ ሌሎችንና እንዲሁም እግዚአብሔርን ስንዋሽ እንገኛለን። የመንፈሳዊ ሕይወት ሽንፈት እንደኘውና ትልቁ ምክንያት "በራስ መሞላት" ነው። ስለዚህ የተሰቀለ የግል ሕይወት ከሌለን፥ ትንሳኤ ያገኘ መንፈሳዊ ሕይወት አይኖረንም። "ራስን በማተለቅ" መንፈስ የተሞላ ሕይወት፥ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላ መሆን አይችልም። "ራስን የማተለቅ" መንፈስ ከውስጣችን ተሟጦ ካልፈሰሰ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊሞላን አይችልም።

## 3.3. እግዚአብሔር እንደሚያየው አውቆ ያገልግል

የእግዚአብሔር ዓይን ከቶውንም ሆነ በኅ የሆነውን ሁሉ ያያል። ከእርሱ የሚደበቅ ምንም ነገር የለም። ላይ ላዩን ብቻ ሳይሆን ወደ ውስጥ ዘለቅ ብሎ በመግባት የሰውን ልብ ያያል። የእግዚአብሔር ዓይን የሚያየው በጥራት ነው። ሚዛኑም እንደ ሰው ሚዛን አይሳሳትም፤ አይለዋወጥም። እግዚአብሔር የሰውን ድርጊት፥ ከአፉ የሚወጣውን ቃል ብቻ ሳይሆን፥ ገና በተግባር ላይ ያላዋለውን አሳቡን፥ ፍላጎቱን፥ ምርጫውን ይመዝናል። ሰው ሌላውን ሰው ማታለል እንደሚችለው እግዚአብሔርን ማታለል አይችልም። *"የሰው መንገድ ሁሉ በዓይኑ ፊት የቀናች ትመስለዋለች፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ይመዝናል"* (ምሳ. 21፥2)። ዓለም እንድትታይ፣ እንድትመረጥ፣ *"ራስህን ከፍ ከፍ አድርገህ አሳይ፤ ራስህን አዋድ፤ "እለሁ! አለሁ" በል። የሠራኸውን ተናገር"* ይላል። የእግዚአብሔር ቃል ግን *"ቢታየውም ያይሃል...ሠራሁ ብለህ ባታውጅም፣ ሥራህን ጌታ ያውቃል"* ይላል። የዓለም ሕግ *"ባለህበት ሕብረተሰብ ውስጥ ሥፍራ ለማግኘት ራስህን አሳይ፤ ራስህን ጨርሶ አትጣል"* ሲል፥ የእግዚአብሔር ሕግ ግን *"ራስህን ዝቅ ዝቅ አድርግ፤ ምንም ዓይነት ነገር ለታይታ ስትል አታድርግ"* ይላል። ዓለም የወፈረውን፥ የተለቀውን፥ የተማረውን፥ ለሰው ዓይን ጎልቶ የሚታየውን መርጦ ሲያገለግል፣ ከፍ ከፍ ሲያደርግ፥ እግዚአብሔር ግን የኮሰሰውን፥ ተራውን፥ ያልተማረውን፥ ድሃውን፣ በሰው ዓይን ጎልቶ የማይታየውን ያያል። ለትልልቆች ብቻ ሳይሆን ለትንንሾችም የወንጌሉ ብርሃን እንዲበራላቸው፣ ሙሉ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይፈልጋል። የእግዚአብሔር ዓይን ሁሉን ማየት እንደሚችል የገባው አገልጋይ፥ እግዚአብሔር እንዲያየው ራሱንና አገልግሎቱን አተልቆና አጋኖ "እያችሁ ልኝ ወይ?" ብሎ ማወጅ እንደማያስፈልገው ያውቃል። በሚሠራው ሥራ ሁሉ ጌታውን ብቻ ያከብራል። በመጨረሻው ቀን በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም እውነተኛውን አገልግሎታችንን የሚመዝነው ጌታ ዋጋችንን በትክክል ተምኖ ይሰጠናል።



## 4. የምንሰጠው አገልግሎት ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ይዋል

የእግዚአብሔር ዕቅድና ዓላማ በሕይወታችን ምን እንደሆነ ከገባን፥ ለሰው ጎልቶ የማይታይ አገልግሎት ቢኖረን፥ ደስ ብሎንና ሳይቆረቁረን ማገልገል እንችላለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል እንደኛው፥ ክርስቲያኖች በመዋረድ ፈንታ ለመከበር፥ ዝቅ ስማለት ፈንታ ከፍ ለማለት፥ እግር በማጠብ ፈንታ እግር ለማሳጠብ የምናደርገው ትግልና እሽቅድምድም ነው። *"እኔ ካልሰበክሁ፥ እኔ ካልዘመርኩ፥ እኔ ካልመራሁ፥ እኔ ሽማግሌ ካልሆንኩ፥ እኔ ዲያቆን ካልሆን"* በማለት እርስ በርሳችን ስለምንሻኮት ነው። ክብሩ ለእግዚአብሔር ከሆነ፥ ከእኛ ሌላ ማንም ቢሰብክ፥ ማንም ቢዘምር፥ ማንም ቢመራ፥ ማንም ቢያስተዳድር በመሠረቱ ግድ ሊኖረን አይገባም ነበር። ፍላጎቱ ጌታን ማክበር የሆነ አማኝ፥ ክብርን ለሚገባው ጌታ ይሰጣል። "ይህን ሠርቷል" ተብሎ እንዲታወጅለት አይፈልግም። ወይም "ይህን ሠርቻለሁ" ብሎ ገድሉን በማውራት አይታበይም። ምስጋና ሲቀርብለት፥ ምስጋናውን ወደሚመለከተው ጌታ ያስተላልፋል። ፍላጎቱ ጌታን ማክበር የሆነ አማኝ ሌሎች ሲመሰገኑ፥ ሌሎች ሲታወቁ ደስ ይለዋል እንጂ፥ አይከፋውም። ሌሎችን ማመስገንና ማድነቅ አይከብደውም። ብዙዎቻችን ምስጋና እንደ ውሃ የጠማን ነን። ዲ. ኤል ሙዲ፥

> *"የትልቅነት መጀመሪያ ትንሽነት ነው፤ ትልቅ ዕድገት የሚገኘው ዝቅ በማለት ነው። እውነተኛው ትልቅነት፥ ምንም አለመሆንን ወይም ባዶነትን መረዳት ነው"* አለ።

ታላቅ አገልጋይ መሆን ማለት የምናገለግላቸው ሰዎች ባሪያ መሆን ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በቅርብ ወይም ጎን ለጎን መራመድ የሚችሉት ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ የሚችሉ ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር ያከበራቸው ሁሉ የራሳቸውን ትንሽነት የተረዱ ናቸው፥

- *ያዕቆብ፥ "...ያልኸኝ እግዚአብሔር ሆይ! ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ እንኳ የማይገባኝ ነኝ፤ በትሬን ብቻ ይዤ ይህን ዮር ዳኖስን ተሻግሬ ነበርና፤ አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ"* (ዘፍ. 32፥10)። ዳዊትም፥ በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጦ *"ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እስከ ዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው?" አለ (2 ሳሙ. 7፥18)።*
- *ሠለሞን፥ "አቤቱ አምላኬ ሆይ! እኔን ባሪያህን በአባቴ በዳዊት ፋንታ አንግሠኸ ኛል፤ እኔም መውጫንና መግቢያን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ። ባርያህም ያለው አንተ በመረጥኸው ሕዝብህ ስለ ብዛቱም ይቆጠርና ይመጠን ዘንድ በማ ይችል ታላቅ ሕዝብ መካከል ነው"* አለ (1 ነገ. 3፥7-8)።

እግዚአብሔር በሕይወታችን ከመሥራቱ በፊት፤ ፍጹም ሊያስጎነብሰን ይፈል ጋል። በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ማዋረድ ስንጀምር፤ እግዚአብሔር በሕይ ወታችን መሥራት ይጀምራል። ሐዋርያው ጳውሎስ የራሱን አቋም ሲገልጽ፣

- *"እኛ የምንሰብከው ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እንጂ ራሳችንን አይደለምና፣ እኛም ራሳችንን ስለ ኢየሱስ ስንል የእናንተ አገልጋዮች ሆነናል"* (2 ቆሮ. 4፥5) አለ።

የደህንነታችንም ሆነ የአገልግሎታችን ዋና ዓላማ፤ ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ለእግዚአ ብሔር ክብር እንዲሆን ነው። ጳውሎስ ስለዚሁ ሲናገር፤

- *"ይህንንም ያደረገው በተወደደው ልጁ አማካይነት በነፃ የሰጠን ክቡር ጸጋ እንዲመሰገን ነው"* (ኤፌ. 1፥6)
- *"...በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት አስቀድመን ስለ ተወሰንን፤ አሁንም በክርስ ቶስ አማካይነት ተመረጥን። ይህም የሆነው በመጀመሪያ በክርስቶስ ተስፋ ባደ ረግነው በእኛ ምክንያት ለእግዚአብሔር ክብርን ምስጋና እንዲሆን ነው"* (ኤፌ. 1፥12)።
- *"ለክብሩ ምስጋና እንዲሆን እግዚአብሔር የራሱ የሆኑትን በሙሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህ መንፈስ የርስታችን መያዣ ነው"* (ኤፌ. 1፥14)።
- *"...ማናቸውንም ስታደርጉ፤ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ"* (1 ቆሮ 10፥31)።

በአገልግሎት ስም የምናደርገው ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ካልዋለ፤ ተራ የሃ ይማኖት እንቅስቃሴ እንጂ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው አገልግሎት አይሆ ንም። ለምሳሌ፣ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች በተለያየ ምክንያት ዕርዳታ እንሰጥ ይሆናል። ይሁን እንጂ፤ ድብቅ ዓላማችን የራሳችንን ስም ለማስጠራት ከሆነ፣ ምንም ያህል ብንለፋና ብዙ ሰዎችን ብንረዳ፣ አገልግሎታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። "አገልጋይ" እንምሰል እንጂ፣ እውነተኛ አገልጋዮች አይደለንም። ለም ሳሌ እውነተኛ ያልሆነ (counterfeit) የውሸት ብር፣ እውነተኛ መስሎ ሳይታወቅ ገበያ ውስጥ ሰዎች ሲገዙበትና ሊሸጡበት ይችላሉ። መጨረሻ ላይ ባንክ ሲገባ ግን፤ እውነተኛ ብር ስላልሆነ፤ በባንኩ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኝም። እኛም የምንሰጠው አገልግሎት፤ የምንሠራው መንፈሳዊ ሥራ ለእግዚአብሔር ክብር መሆን፤ አለመሆኑ፣ ወይም እውነተ ኛነቱ በምን ይታወቃል? አገልጋዩ የሚያገለግላቸው ሰዎች ወደ አገልጋዩ እንዲመለከቱ በማድረግ ፈንታ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለከቱ የሚያደርጋቸው ከሆነ፣ በእነዚያ ሰዎች ምክንያት እግዚአብሔር ይከብራል። አገልጋዩ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ወደ ራሱ የሚስብ ከሆነ፣ የሚከብረው እግዚአብሔር ሳይሆን፣ አገልጋዩ በመሆን የዚያ ሰው



አገልግሎት ዋጋ የለውም። እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ፣ እርሱን እንዲያደንቁትና እንዲያከብሩት የሚያደርግ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን በጥላው እየሸፈነው መሆኑን ማወቅ አለበት።

በመልካም ሥራችን ማክበር ያለብን ራሳችንን ሳይሆን፣ የሰማዩ አባታችንን መሆን አለበት። ኢየሱስ *"ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁ እንዲያመሰ ግኑት (እንዲያከብሩት) የእናንተም ብርሃን በሰው ፊት ይብራ"* (የማቴ. 5፥16) ይለናል። አገልግሎታችንን መፈጸም ያለብን ሰዎች የምናደርገውን መልካም ሥራ አይተው እኛን እንዲያመሰግኑን ሳይሆን፣ ጌታን ብቻ እንዲያመሰግኑ መሆን አለበት። እኔና እናንተ በአገልግሎት ውስጥ የምንለፋበት ምክንያት ታዋቂና ዝነኛ ሰው ለመሆን ነው? ወይስ እግዚአብሔርን ለማክበር? ራሳችንን ለማስተዋወቅና ስማችንን ለማስጠራት ነው? ምር ጫው የራሳችን ነው። ለግል ጥቅም፣ ለሥልጣንና ስማቸውን ለማስጠራት ሲሉ ብቻ ወደ አገልግሎት የሚመጡ ካሉ፣ በሕይወታቸው ትልቅ ስህተት እየሠሩ መሆናቸውን ማወቅ አለባቸው። ኤ. ደብልዩ. ቶዘር የተባለው የታወቀ አገልጋይ፣ መታበይ የሚያስከትለውን አደጋ ስለሚያውቅ አንድ ቀን ለመስበክ መድረኩ ላይ ከመውጣቱ በፊት የስብሰባ መሪው በጣም እያደነቀ ካስተዋወቀው በኋላ ቶዘር፤

> *"ጌታ ሆይ! ስለ እኔ ሊጋኖ በመናገሩ ይህንን ሰው ይቅር በለው፤ እኔም ስለ እኔ በሰማሁት የአድናቆት ቃል ደስ በመሰኘቴ፤ ሁለታችንንም ይቅር በለን"* አለ።

እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ መሆኑን፤ እንዲሁም ማንም ክብሩን እንዲካፈልበት የማይፈልግ መሆኑን በግልጽ ይናገራል። በኢሳያስ አማካኝነት *"አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ብቻ ነኝ፤ የእኔንም ክብር የሚጋራ ሌላ አምላክ የለም"* (ኢሳ 42፥6) አለ። እግዚአብሔር በሕይወታችንና በአገልግሎታችን እንዴት ሊከብር እንደሚችል በማስ ብና ሕይወታችንን በጥንቃቄ በመምራት ፈንታ "ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን?" በማለት ስለ ራሳችን የምንጨነቅ ከሆነ፤ ስለ እግዚአብሔር ክብር ግድ የሌለን መሆናችን ነው። በአገልግሎታችን እውነተኛ ፍሬ ማፍራት ስንችል የምንከብረው እኛ ሳንሆን እግዚአብ ሔር ነው። በአገልግሎት ውስጥ ፍሬና ውጤት አንድ ዓይነት አይደለም። አንዳንድ ፎርሙላ ተከትለን ጥሩ ውጤት ማምጣት እንችላለን። ብዙ ሕዝብ የሚይዝ የቤተ ክር ስቲያን ሕንጻ ማሠራት፣ በቤተ ክርስቲያናችን የተለያዩ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ ብዙ ብር ሰብስበን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ማቋቋም እንችላለን። ይሄ ሁሉ ጥሩ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ የሥራ ውጤት እንጂ፣ ፍሬ አይደለም። ፍሬ በምንኖረው እውነተኛ ሕይወት የሚገኝ የአገልግሎታችን ውጤት ነው።

የእግዚአብሔርን ክብር ከመሻማት ራሳቸውን ከጠበቁ ሰዎች መካከል ጳውሎስና በርናባስ ይገኙበታል። በልስጥራ ውስጥ ከተወለደ ቀን ጀምሮ ሽባ የነበረ፣ በእግሩ ፈጽሞ ሄዶ የማያውቅ አንድ ሰው አጋጥሟቸው፣ ጳውሎስ ለውየው ለመዳን የሚያስችል እም

ነት እንዳለው አይቶ "ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም!" አለው። ሰውየውም ወዲያም ብድግ ብሎ መራመድ ጀመረ (የሐዋ. 14፥8-13)። ይህንን ያየ ሕዝብ "አማልክት በሰው አም ሳል ሆነው ወደ እኛ ወርደዋል በማለት በሊቃኦንያ ቋንቋ ተናገሩ። ለጳውሎስና ለባርናባስ "ድያ፥ ሄርሜን" ብለው ስም አወጡላቸው። ያ ብቻ አልበቀቃም። ኮርማዎችንና የአበባ ጉንጉኖችን ወደ ከተማው በር አምጥቶ ከሕዝቡ ጋር በመተባበር፥ ለጳውሎስና ለበርናባስ መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው ፈለጉ። ጳውሎስና በርናባስ ይህን ዓይነት መደነቅና መከበር ሲያገኙ በልባቸው ውስጥ ምን ዓይነት ስሜት ተሰምቷቸው ይሆን? "መከበርና መደነቅን" የሚጠላ ሰው የለም። ጳውሎስና በርናባስ የተሰጣቸውን ታላቅ ክብር መቀበል የእግዚአብ ሔርን ክብር መንጠቅ ወይም መሻማት እንደሆነ ስለተረዱ፥ "በርቱ! ቀጥሉ" በማለት ፈንታ በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ። እየጮኹ ወደ ሕዝቡ ሮጡና *"እናንተ ሰዎች ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? እኛ እዚህ የመጣነው እናንተ ከዚህ ከከንቱ ነገር ሁሉ ርቃችሁ ሰማይና፥ ምድርን ባሕርንና በውስጣቸው የሚገኙትን ሁሉ ወደ ፈጠረው ወደ ሕያው አምላክ እንድትመለሱ መልካም ዜና ልናበስራችሁ ነው"* (የሐዋ. 14፥15) አሏቸው።

አንድ እውነተኛ አገልጋይ ሊፈራ የሚገባው ነገር ቢኖር ተቃዋሚዎች የሚወረው ሩበትን ድንጋይ፥ የሚሰነዝሩበትን ነቀፌታ ሳይሆን፥ እያደነቁ ክብር የሚመቱለትን፥ አበባ የሚያስታቅፉትን፥ የአበባ ምንጣፍ የሚያንጥፉለትን ነው። ዛሬ ምንም በሌለበት፥ ምንም ዓይነት ተአምር ባልታየበት አገልግሎት ውስጥ የክርስቶስን ድንቅ ሥራ የሚና ገሩ፣ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ አስመስለው የራሳቸውን ታሪክ የሚዘረዝሩ አገልጋ ዮች የበዙበት ዘመን ነው። አገልጋዩን ችግር ላይ የሚጥሉት በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ክበር መቺዎች ናቸው። ዳዊትንና ንጉሥ ሳኦልን ያጋጩት በዘመኑ የነበሩ ክበር መቺዎች ናቸው። "ሳኦል ሺ ገደለ፤ ዳዊት እልፍ ገደለ" በማለት ክበሮ እየመቱ ዘፈናቸውን አቀለ ጡት። ክበር መቺዎች ሲያጋንኑ ነው እንጂ፥ ሳኦል ሺ፣ ዳዊትም እልፍ አልገደሉም። ዛሬም በዘመናችን ብዙ ክበሮ መቺዎች አሉ። አገልጋዮቹም ሞቅ ሲላቸው ያላደረጉትን "አደረጉ" በማለት ገድላቸውን እንዲያውጁላቸው ይፈልጋሉ። ለማስመሰል ሲሉ ብቻ "ይህን ሁሉ የምንገራችሁ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን ነው" ይላሉ። ይበሉ እንጂ፥ አዕምሯቸውን የሚጠቀሙ ክርስቲያኖች "...ሞኝህን ፈልግ..." ይሏቸዋል።

የልስጥራ ሕዝብ እንደ አምላክ ሊሰግዱላቸው፣ መስዋዕት ሊያቀርቡላቸው ሲያ ሰቡ፣ ጳውሎስ እየጮኸ "እኛም እኮ እንደ እናንተ ሰዎች ነን" በማለት ከለከላቸው። ከእነርሱ በላይ ኃያል የሆነ አምላክ ያለ መሆኑን፥ የተደረገውም ተአምር በእነርሱ ኃይል የተደረገ እንዳልሆነ፥ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት በግልጽ ተናገሩ። ጳውሎስና በርናባስ "እኛም እንደ እናንተ ሰዎች ነን" ብለው ባይናገሩ ኖሮ ብዙ ችግር ይፈጠር ነበር። ይኸውም፣ ሥልጣናቸውና ኃይላቸው ወሰን የሌለው እንደሆነ ስመገመት ብዙ ሕዝብ ሊያያቸው ይሰበሰብ ነበር። እንዲፈውሱ፥ ተአምር እንዲሠሩ፥ መለኮታዊ መገለጥ እንዲያሳዩ ይጠበቅባቸው ነበር። ሕዝቡ የጠበቀባቸውን ያህል ሆነው ካላገኛቸው፥



*"ተአምር አሳዩን... አለበለዚያ...."* በማለት ቴዎዳስን እንደ ገደሉት፥ እነርሱንም ይገድሏቸው ነበር (የሐዋ. 5፥36)። የዘመኑ አገልጋዮች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው በመቅረብ ፋንታ፥ ተአምር ሠሪዎች፥ የፈውስ ስጦታ ያላቸው፥ እነርሱን የመሰለ አገል ጋይ በዓለም ላይ እንደሌለ አድርገው ያቀርባሉ። "እንዳልነው ሆነን ካልተገኘን ሕዝቡ አይቀበለንም" ብለው ስለሚያስቡ፥ ብዙ የተጭበረበረ ነገር ማድረግ ይጀምራሉ። ያልተፈወሰውን "ተፈወሰ" ያልዳነውን "ዳነ" ብለው እግዚአብሔርን በውሸት ለማክበር ይታገላሉ። አገልጋይ ሰው መሆኑን በግልጽ ሲያሳውቅ፥ "ሰው ነኝ፥ መሳሳት፥ መውደቅ፥ ማጥፋት እችላለሁ" ማለቱ ነው። ይሄም ራሱን "መለበተኛ የሆነ እግዚአብሔር" አድርጎ እንዳያቀርብ ይረዳዋል። ጳውሎስና በርናባስ ራሳቸውን እንደ "አማልክት" አድርገው ቢያቀርቡ ኖሮ፥ ስለ ሕያውና ታላቁ እግዚአብሔር መመስከር ባልቻሉም ነበር። ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ሲገልጹ፥ ወደ ጌታ ለማመልከት ነጻ ሆኑ።

## 5. የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ አገልጋይ እንዴት ዓይነት ነው?

### 5.1. ስለ ራሱ ብዙ ይናገራል

ራሱን ከፍ የማድረግ ዝንባሌ ያለው መንፈሳዊ መሪ የሠራውን፥ ያደረገውን፥ ያገኘ ውን፥ አሳምሮና ከሆነው በላይ አተልቆ ያወራል። ምን ያህል ሰዎች እርሱ ጸልዮላቸው እንደተፈወሱ፥ እርሱ ሰብኮላቸው ምን ያህል ሰዎች ደህንነትን እንዳገኙ ያወራል። ስለ ራሱ ምክንያትና መንገድ ፈልጎ ያልሆነውን "ነኝ" ብሎ ይናገራል። ዲ. ኤል ሙዲ፤

> *"አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ብዙ ርቆ እንደሄደ ማወቅ የሚቻለው ስለ ራሱና እንዲሁም ስለ ጥሩነቱ ብዙ የተናገረ እንደሆነ ነው"* አለ።

የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ አገልጋይ በራሱ ፍቅር የተሞላ ነው። ስለሆነም፣ ምክንያት ፈልጎ ብዙ ጊዜ የሚያወራው ስለ ራሱ ነው። *"ይህን አድርጌ፥ ያን አድርጌ.. እዚህ ገባቼ፣ እዚያ ወጣቼ"* በማለት የአገልግሎቱን ስፋት ያወራል። አገልጋይ በሕይወቱ ሙሉ "በኩራትና በትህትና መንፈስ" መካከል በሚፈጠረው ትግልና ግብግብ ውስጥ ይኖራል። እውነተኛ ትህትና ለእውነተኛ አገልጋይ አስፈላጊ መሆኑን የሚያውቀው ሰይጣን ያልሆነውን "ነህ" በማለት ራሱን አተልቆ እንዲያይ ያደርገዋል።

### 5.2. ከሌሎች ተሽሎ መታየት ይፈልጋል

ራሱን በማተለቅ የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ ሰው፣ ሁልጊዜ ከሌሎች ተሽሎ መታየት ይፈልጋል። ከሌሎች ተሽሎና በልጦ ለመታየት ሲል ብቻ ምንም ዓይነት ዋጋ ይከፍላል። ተልቆና በልጦ ለመታየት ሲል ብቻ ከአቅሙ በላይ ለመኖር ይሞክራል።

በዚህ ዓይነት ቤተሰባቸውን የሚጎዱ ብዙዎች ናቸው። ቤተሰቡን አስርቦ፣ ያለአቅሙ ቤቱን ለማስጌጥ ልዩ ልዩ ዕቃ ይገዛል። ያልሆነውን ሆኖ ለመታየት ሲል ብቻ በገቢው መጠን አይኖርም። ሁልጊዜ ራሱን እያስጨነቀ ይኖራል። ሠለሞን *"ሀብታም መስሎ በችግር ከሚኖር ሰው ይልቅ፥ ተራ ሰው መስሎ እየሠራ ኑሮውን የሚያሸንፍ ይሻላል"* ይላል (ምሳሌ 12፥9)። የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ ሰው ከሌሎች ተሽሎ መታየት ስለሚፈልግ ሁልጊዜ ራሱን እያታለለ ይኖራል። አንድ ጸሀፊ፣

> *"ከውሸት ሁሉ አሳፋሪው በምላሳችን የምንናገረው ውሸት ሳይሆን፥ የምንኖረው የውሸት ኑሮ ነው"* አለ።

ከሌሎች ተሽሎ ለመታየት ስለሚፈልግ ከአቅሙ በላይ ለመኖር በመሞከሩ በቀላሉ የተጭበረበረ፥ ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ ኑሮ መኖር ይጀምራል።

## 5.3. ስህተቱን ማየት አይችልም

ራሱን በማተለቅ የእግዚአብሔርን ክብር የሚሻማ ሰው፣ መሳሳቱን በግልጽ ቢያይና ቢያውቅም ፈጽሞ ተሳስቻለሁ፥ ልክ አይደለሁም ማለት አይችልም። አለማወቁን ወይም ስህተቱን የሚሸፍንበትን መንገድ ይፈልጋል። አለማወቁ፥ መሳሳቱ በሰው ዘንድ ከታወቀበት ሰው የሚሸሸው መስሎ ይሰማዋል። ስለዚህ ሁልጊዜ በሥጋትና በፍርሃት ይኖራል። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ማረም፥ መምከርና ማስተካከል አይቻልም። ሠለሞን *"ትዕቢተኛን ሰው ብታርመው ስድብን ታተርፋለህ"* ይላል (ምሳሌ 9፥7)። የታወቀው ጸሀፊ ፕሉተርክ፥

> *"ሁሉን ማድረግ አለመቻል ነውር የለበትም፤ ማድረግ የማንችለውን እንደምንችል አድርገን ማስመሰል ግን አለነዋሪና አሳፋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ችግርም ውስጥ ይከታል"* አለ።

በሰው ፊት ተከብሮ፥ ተደንቆ፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ቀልሎ ሊገኝ ይችላል። እግዚአብሔር የሰውን ዓላማ፥ የሰውን ሀሳብ፣ ከአፉ የሚወጣውን ቃልና እንዲሁም ድርጊቱን ይመዝናል። ሰው ሌላውን መዋሸት ይቻል እንጂ፥ እግዚአብሔርን መዋሸት አይችልም። እግዚአብሔር ከላይ ያለውን ብቻ ሳይሆን ውስጣችንንም ያያል፤ ሁሉን ይረዳል፤ ሁሉን ያውቃል፤ ጽድቃችንን ብቻ ሳይሆን፥ ድካማችንንም ያያል።

# 6. የእግዚአብሔርን ክብር የማይሻማ አገልጋይ "ትሁት" ነው

ክብር የሚገኘው የእግዚአብሔርን ክብር በመንጠቅ አይደለም። ሠለሞን፥ "ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤ መንፈሱን የሚያዋርድ ግን ክብርን ይቀበላል" ይላል (ምሳሌ 29፥23)።



## 6.1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቁ ችግር የራስን ክብር መፈለግ ነው

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል ዋናው "ዝቅ ሲሉ ከፍ፥ ከፍ ሲሉ ዝቅ..." የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ መረዳት ካለመቻል የሚመጣ ነው። ክርስቲያኖች በመዋረድ ፈንታ ለመከበር፥ ዝቅ በማለት ፈንታ ከፍ፥ እግር ለማጠብ በመጎንበስ ፈንታ፥ እግር ለማሳጠብ እርስ በርሳችን ትግልና እሽቅድምድም በእግዚአብሔር ቤት ስለምናሳይ ነው። *"እኔ ካልሰበኩ፥ እኔ ካልዘመርኩ፥ እኔ ካልመራሁ፥ እኔ ሽማግሌ ካልሆንኩ፥ እኔ ዲያቆን ካልሆንኩ"* በማለት እርስ በርሳችን ስለምንሻኮት ነው። ክብሩ ለእግዚአብሔር ከሆነ፥ ከእኛ ሌላ ማንም ቢሰብክ፥ ማንም ቢዘምር፥ ማንም ቢመራ፥ ማንም ቢያስተዳድር በመሠረቱ ግድ ሊኖረን አይገባም ነበር። እኔና እናንተ እንድ ያላወቅነው ነገር አለ። ይኸውም ሌሎችን ገፍትረን፥ ጠልፈንና ጥለን በምንሰጠው አገልግሎት እግዚአብሔር ምን ጊዜም የማይከብር መሆኑ ነው። ይህን ዓይነቱ ችግር በደቀ መዛሙርቱም ዘመን ነበር። *"በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን?" ብለው ሲከራከሩ ሕጻን በመካከላቸው አቁሞ "እንደዚህ ሕጻን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው"* አላቸው (የማቴ. 18፥1-3)። *ጆን ፍሌቮል* የተባለው ጸሀፊ፥

> *"እግዚአብሔርን እንደሚገባው የሚያውቁት፥ ትሁት ይሆናሉ፤ ራሳቸውን እንደሚገባው ለይተው ያወቁ፥ ምንጊዜም ኩሩ መሆን አይችሉም"* አለ።
>
> *ቶማስ ኬምፐ "እግዚአብሔር ከትሁቶች ጋር አብሮ ይሄዳል፤ ራሳቸውን ዝቅ ለሚያደርጉ፥ ራሱን ይገልጽላቸዋል፤ ለትዕቢተኞች ግን ጸጋውን ይሸሽጋል"* አለ።

## 6.2. ትሁት አገልጋይ በራስ ላይ ያተኮረ ሕይወት የለውም

ትሁት አገልጋይ የራሱ ዋጋቢስነት፥ የእግዚአብሔር ታላቅነት፣ ደግነትና በፊ የሆነው ጸጋው ይሰማዋል። ትሁት የሆነ አገልጋይ በለ ራሱ ትልቅነት በማሰብ ፈንታ፣ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፍቅር፥ ደግነትና እንዲሁም በፊ በሆነው ጸጋው ይደነቃል። ለሚደረግለት በጎ ነገር ሁሉ *"ለእንደኔ ዓይነቱ ሰው ተገቢ ነው፤ እግዚአብሔር የእኔ ዕዳ አለበት"* በማለት ፈንታ፣ *"ምንም ለማይገባኝ ለእንደ እኔ ዓይነቱ ብዙ ተደረገልኝ"* በማለት ልቡ በምስጋና የተሞላ ይሆናል። ትሁት አገልጋይ *"እኔ ብቁ ነኝ፤ ከሌሎች ሁሉ እበልጣለሁ"* በማለት ሥልጣን ለመያዝ ከማንም ጋር አይታገልም። አዳም ክላርክ፥ የጆን ዌስሊ የአገልግሎት ባልደረባ 20 ቋንቋ የሚችሉ፥ ጌታ በጣም የተጠቀመባቸው ሰው ነበሩ። ስምንት ቮልዩም የያዘውን ኮሜንተሪ በ27 ዓመት ውስጥ ጽፈው የጨረሱ ሰው ናቸው። ጆን ዌስሊ ከሞቱ በኋላ የሜቶዲስት ቤተ እምነት ጠቅላላ ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት እንዲመሩ ሲመረጡ፥ "እምቢ!" በማለታቸው ተሸከመው በግድ ወንበሩ ላይ እንዳስቀመጧቸው ታሪክ ይመሰክራል።

በትህትና የተሞላ አገልጋይ "ይህን ሠርቷል" ወይም "ይህን ሠርቻለሁ" ብሎ በማወጅ አይታበይም፤ የእግዚአብሔርንም ክብር አይሻማም። ምስጋና ሲቀርብለት፥ ምስጋናውን ቶሎ ወደሚመለከተው ጌታ ያስተላልፋል። በትህትና የተሞላ አገልጋይ፥ ሌሎች ሲመሰገኑ፥ ሌሎች ሲታወቁ ደስ ይለዋል እንጂ ይህን ያህል አይቆረቆረውም። ሌሎችን ማመስገንና ማድነቅ አይከብደውም።

## ፳ኛ ምዕራፍ ፲ ፫ኛ

# የፍቅር አገልግሎት

*"ልጆቼ ሆይ! ፍቅራችን እውነተኛና በሥራ የሚገለጥ ይሁን እንጂ በቃል ወይም በንግግር ብቻ አይሁን።"*
*(1 ዮሐ. 3፥18)*

በጣም የታወቁት ስኮትላንዳዊው ሰባኪ፣ *አንድሪው ቦናር* አንድ ቀን ከአንድ ትልቅ ስብሰባ ላይ ተገኝተው በዘመኑ ተደናቂ የነበሩትን ታላቅ ሰባኪ ስብከት ካዳመጡ በኋላ፣ ሰባኪው ስብከታቸውን ጨርሰው ከመድረክ ሲወርዱ ጠጋ ብለው፥ *"መስበክ ትወዳለህ! አይደለም?"* ብለው ጠየቋቸው። እኛም ታዋቂ ሰባኪ *"አዎን! መስበክ በጣም እወዳለሁ"* የሚል መልስ ሰጧቸው። *አንድሪው ቦናርም* በመቀጠል፣ *"የሰበክህላቸውንስ ሰዎች ለመሆኑ ትወዳቸዋለህ?"* ብለው ጠየቋቸው። *የአንድሪው ቦናር* ጥያቄ ይህን ያህል ከመስመር የወጣ ጥያቄ አልነበረም። በመሪነት ደረጃ ላይ ሆነው ማገልገል የሚወዱ፣ የሚያገለግሉትን ሕዝብ ግን እንደሚገባው የማይወዱ ብዙ አገልጋዮች አሉ። እረኛው በጎቹን ከመውደዱ በፊት የበጎቹን ባለቤት መውደድ እንዳለበት ግልጽ ነው። የበጎቹን ባለቤት ሳይወድ በጎቹን መውደድ አስቸጋሪ ይሆንበታል። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ለበጎቹ እረኛ እንዲሆን ሊያስማራው የጠራውን ጴጥሮስ "በጎቼን ትወዳቸዋለህን?" ብሎ በመጠየቅ ፈንታ "ትወደኛለህ?"